# መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፡ ሱቱኤል ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩፤ አገራችን ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በጠፋች ፡ በሠላሳ ፡
ዘመን ፡ ዕዝራ ፡ እባል ፡ የነበርኩ ፡ እኔ ፡ ሱቱ
ኤል ፡ በባቢሎን ፡ ነበርኩ ፡ በምኝታዬም ፡ እኔ ፡
ተኝቼ ፡ ነበር ፡ ፊቴ ፡ ግን ፡ ተገልጦ ፡ ነበር ፡ በል
ቡናዬም ፡ አሳብ ፡ ይወጣ ፡ ይወርድ ፡ ነበር ።
፪፤ የኢየሩሳሌምን ፡ ጥፋቷን ፡ አይቻለሁና ፡ በባቢ
ሎን ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎችን ፡ ተድላ ፡ ደስታንም ፡
አይቻለሁና ።
፫፤ ፈጽማ ፡ ሰውነቴ ፡ ታወከች ፡ የሚያስፈራ ፡ ነገር
ንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ እናገር ፡ ጀመርኩ ።
፬፤ አቤቱ ፡ ስናገር ፡ እንዲህ ፡ አልኩ ፡ አስቀድሞ ፡
ምድርን ፡ በፈጠርከት ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ እንዲህ ፡
ያልክ ፡ አይደለምን ፡ አዳምን ፡ በፈራሽ ፡ ሥጋ ፡
ታስገኘው ፡ ዘንድ ፡ ይኽንን ፡ ብቻህን ፡ መሬ
ትን ፡ ያዘዝካት ፡ አይደለምን ።
፭፤ አዳምም ፡ የሥልጣንህ ፡ ፍጥረት ፡ ነው ፡ ነባ
ቢት ፡ ነፍስን ፡ አዋህደህ ፡ ፈጠርከው ፡ በነባ
ቢት ፡ ነፍስም ፡ በፊትህ ፡ ደህነኛ ፡ ሆኖ ፡ ኖረ ።
፮፤ ምድር ፡ ተፈጥራ ፡ ሳትጸና ፡ ሥልጣንህ ፡ ወደ
ፈጠረቻት ፡ ወደ ፡ ገነትም ፡ አገባኸው ።
፯፤ ዕፀ ፡ በለስን ፡ አትብላ ፡ ብለህ ፡ አዘዝከው ፡ እሱ ፡
ግን ፡ ትእዛዝክን ፡ አፈረሰ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሱ ፡
በልጆቹ ፡ በልጅ ፡ ልጆቹም ፡ ላይ ፡ ሞትን ፡ አመ
ጣህ ፡ አሕዛብም ፡ ሕዝቡም ፡ ነገደ ፡ ያፌት ፡ ነገደ ፡
ሴምም ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡ መንደር ፡ መንድ
ረው ፡ የሚኖሩትም ፡ ከሱ ፡ ተወለዱ ።

አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ በሥራቸው ፡ ፀንተው ፡ ኖሩ ። ፰፤
በፊትህ ፡ በደሉ ፡ አንተንም ፡ ካዱ ፡ አንተ ፡ ግን ፡
አልከለከልካቸውም ።
ዳግመኛም ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ፱፤
በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ላይና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የጥ
ፋት ፡ ውሀን ፡ አመጣህ ፡ አጠፋሃቸው ።
ቅጣታቸውም ፡ የተካከለ ፡ ሆነ ፡ በአዳም ፡ ላይ ፡ ፲፤
ሞትን ፡ እንዳመጣህ ፡ እንደዚሁ ፡ በእሊህም ፡
ላይ ፡ የጥፋት ፡ ውሀን ፡ አመጣህ ።
ከነሳቸውም ፡ ስሙ ፡ ኖኅ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ፲፩፤
ሰውን ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ጋራ ፡ አስቀረህ ፡ ከሱም ፡
ኃጥአንና ፡ ጻድቃን ፡ ሁሉ ፡ ተወለዱ ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይበዙ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ፲፪፤
የሚኖሩትም ፡ ምድርንም ፡ ይመሏት ፡ ዘንድ ፡
በጀመሩ ፡ ጊዜ ፡ ልጆቻቸውም ፡ በበዙ ፡ ጊዜ ፡
ከነሳቸው ፡ ብዙ ፡ የሚሆኑ ፡ ሕዝቡም ፡ አሕዛ
ቡም ፡ በተወለዱ ፡ ጊዜ ፡ ከቀደመው ፡ በደል ፡
ይልቅ ፡ ዳግመኛ ፡ እጅግ ፡ ይበድሉ ፡ ጀመሩ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በፊትህም ፡ በበደሉ ፡ ጊዜ ፡ ከነ ፲፫፤
ሳቸው ፡ ስሙ ፡ አብርሃም ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡
ሰው ፡ መረጥህ ።
ወደድኸው ፡ የዘመኑንም ፡ መጨረሻ ፡ ለብቻው ፡ ፲፬፤
በሌሊት ፡ አሳየኸው ።
ልጆቹን ፡ ዓለም ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ፈጽ ፲፭፤
መህ ፡ እንዳታጠፋቸው ፡ ለዘላለሙ ፡ መሐላ
ውን ፡ አጸናህለት ።
ከግብፅ ፡ የወጡ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲናም ፡ የወሰ ፲፮፤
ድካቸውን ።

፲፯፡ ሰማያትን ፡ ዝቅ ፡ ያደረግህላቸውን ፡ ምድርንም ፡
ያንቀጠቀጥህላቸውን ፡ ግብፅንም ፡ ያጠፋህላቸ
ውን ፡ ጥልቅ ፡ ውሀውንም ፡ ያንቀጠቀጥህላቸውን ፡
በሕሩንም ፡ ያንቀጠቀጥህላቸውን ፡ ልጆችን ፡
ዓለም ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ፈጽመህ ፡ እንዳያ
ጠፉቸው ፡ ለዘላለሙ ፡ መሐላውን ፡ አጸናህላ
ቸው ፡፡
፲፰፡ ለእስራኤል ፡ ወገንና ፡ ለያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ እያ
ምልክንና ፡ ዘጠኙን ፡ ሕጊጋት ፡ ትሰጣቸው ፡
ዘንድ ፡ ንውጽውጽታና ፡ እሳት ፡ በረድና ፡
ነፋስ ፡ የሚሆኑ ፡ አራቱ ፡ የጌትነትህ ፡ ታምራ
ቶችህ ፡ ተደረጉ ፡፡
፲፱፡ ነገር ፡ ግን ፡ የቀደመ ፡ ሰው ፡ አዳም ፡ ፈታዊ ፡
ልቡናን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጎ ፡ ነበርና ፡ በነሱ ፡
የሕግህ ፡ ሥራ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ከነሱ ፡ ክፉ ፡
አሳብን ፡ አላራቅህም ፡፡
፳፡ ድል ፡ ተነሣ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከሱ ፡ የተወለዱ ፡ ልጆ
ችም ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ ተነሡ ፡ እንጂ ፡ ድል ፡ የተ
ነሣ ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡፡
፳፩፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሕግህ ፡ ጋራ ፡ ያቺ ፡ ኃጢአት ፡
ከሰነ ፡ ክህደት ፡ ጋራ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ልቡና ፡
ፀንታ ፡ ኖረች ፡ እውነት ፡ ነገርም ፡ ጠፋች ፡
ሐሰት ፡ ግን ፡ ፀንታ ፡ ኖረች ፡፡
፳፪፡ ዘመን ፡ አበው ፡ አለፈ ፡ ዘመን ፡ መሳፍንትም ፡
ተጨረሰ ፡ ስሙ ፡ ዳዊት ፡ የሚባል ፡ አገልጋይ
ህን ፡ ለመንግሥት ፡ አስነሣህ ፡፡
፳፫፡ ስምህ ፡ ሊመሰገንበት ፡ መሥዋዕትህን ፡ ሊሠ
ዋበት ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ሥራ ፡
አልከው ፡፡
፳፬፡ ዘመነ ፡ ነገሥት ፡ ብዙ ፡ ሆነ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሚ
ሠሩት ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ቢያኖር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ በደሉ ፡፡
፳፭፡ ፈታዊ ፡ ልቡናን ፡ ገንዘብ ፡ አድርገውታልና ፡
አዳም ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሠራ ፡ ልጆቹም ፡
ሁሉ ፡ በደሉ ፡፡
፳፮፡ አገርህ ፡ ኢየሩሳሌምንም ፡ በጠላቶችህ ፡ በባቢ
ሎን ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ አሳልፈህ ፡ ሰጠህ ፡፡
፳፯፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በልቡናዬ ፡ ጸዮን ፡ የምትባል ፡
ሀገርን ፡ እጅ ፡ ያደረጋት ፡ ዘንድ ፡ በባቢሎን ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ እውነት ፡ ሥራን ፡ በመሥ
ራት ፡ በውኑ ፡ ይበልጡናልን ፡ አልኩ ፡፡
፳፰፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባቢሎን ፡ በደረስሁ ፡ ጊዜ ፡
ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ብዙ ፡ ኃጢአት ፡ ሲሠራ ፡
አየሁ ፡ ሰውነቴም ፡ ብዙ ፡ የሆኑ ፡ ከዓተኞችን ፡
አየች ፡ እነሆ ፡ ኃጢአቱም ፡ ሲሠራ ፡ ሠላሳ ፡
ዘመን ፡ ነው ፡ ኃጢአቱም ፡ በመሠራቱ ፡ ልቡ
ናዬ ፡ አደነቀ ፡፡
፳፱፡ የባቢሎንን ፡ ሰዎች ፡ እንድትታገሳቸው ፡ አይቼ ፡
ሕግንም ፡ የዘነጉትን ፡ ሰዎች ፡ እንድትራራላ
ቸው ፡ ወገኖችህን ፡ ትተህ ፡ ጠላቶችህን ፡ እን
ድትጠብቅ ፡ አይቼ ፡ ልቡናዬ ፡ አደነቀ ፡፡
፴፡ የማንንም ፡ ኃጢአት ፡ አልተመለከትህም ፡
የዚች ፡ ሥራ ፡ ፍጻሜዋ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ እው
ነት ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ባቢ
ሎን ፡ የምትበልጠው ፡ መብሰጥ ፡ አለን ፡፡
ከእስራኤል ፡ ሌላ ፡ ወገን ፡ ያወቀህ ፡ አለን ፡ ፴፩፡
ወይስ ፡ በሕግህ ፡ እንደ ፡ ያዕቆብ ፡ የታመነ ፡
ሌላ ፡ ወገን ፡ አለን ፡፡
ዋጋው ፡ ያልተገለጸ ፡ ድካሙ ፡ ዋጋውን ፡ ያላ ፴፪፡
ሰጠው ፡ እንደ ፡ ያዕቆብ ፡ ሌላ ፡ ወገን ፡ አለን ፡
ወደ ፡ አሕዛብም ፡ በሄድሁ ፡ ጊዜ ፡ ሕግህን ፡ ትእ
ዛዝህን ፡ ሳይሠሩ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ አገኘኋ
ቸው ፡፡
አሁንም ፡ በባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ ኃጢአት ፡ ዘንድ ፡ ፴፫፡
የኛ ፡ ኃጢአት ፡ የሚዛን ፡ ውልብልቢትን ፡ የም
ትመስል ፡ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ያህል ፡ በልጦ ፡
ይገኝ ፡ እንደሁ ፡ በባቢሎን ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡
ኃጢአትና ፡ የኛን ፡ ኃጢአት ፡ በሚዛን ፡ መዝን ፡፡
ወዲያው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ፴፬፡
በፊትህ ፡ ያልበደሉ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ሕግ
ህን ፡ እንደዚህ ፡ የጠበቀ ፡ ወገን ፡ ማነው ፡፡
ሕግህን ፡ ፈጽሞ ፡ የጠበቀ ፡ ወገንስ ፡ በዚህ ፡ ፴፭፡
ዓለም ፡ አይገኝም ፡፡

## ምዕራፍ ፡ ፬ ፡፡

ስሙ ፡ ዑርኤል ፡ የሚባል ፡ መልአክ ፡ ወደኔ ፡ ፩፡
የተላከ ፡ ይህ ፡ መልአክ ፡ መለሰልኝ ፡፡
የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የጌትነቱን ፡ ፍርድ ፡ ፪፡
መርምረህ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ልቡናህ ፡ አደነ
ቀን ፡፡
እዎን ፡ ጌታዬ ፡ አልሁት ፡ ሦስቱን ፡ ሥራዎች ፡ ፫፡
እገልጥልህ ፡ ዘንድ ፡ ሦስቱንም ፡ ምሳሌዎች ፡
በፊትህ ፡ አኖር ፡ ዘንድ ፡ ተላከሁ ፡ አለኝ ፡፡
ከሦስቱ ፡ ምሳሌ ፡ አንዲቱ ፡ የነገርኸኝ ፡ እንደ ፡ ፬፡
ሆነ ፡ እኔም ፡ ታውቀው ፡ ዘንድ ፡ የምትወዳትን ፡
ይህችን ፡ ሥራ ፡ እነግርሃለሁ ፡ ይህ ፡ ፈታዊ ፡
ልቡና ፡ ስለምንም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስተምርሃለሁ ፡፡
አቤቱ ፡ በል ፡ ተናገር ፡ አልሁት ፡ እሳቱን ፡ በሚ ፭፡
ዛን ፡ መዝነህ ፡ ነፋሱንም ፡ በላዳን ፡ ሰፍረህ ፡ አሳ
የኝ ፡ ( በባሕርያቸው ፡ አይስፈሩምና ፡ ) ትላ
ንት ፡ ያለፈችውንም ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ አድር
ገህ ፡ አሳየኝ ፡ አለኝ ፡፡
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እኔን ፡ እንደ ፡ ጠየቅኸኝ ፡ ይህን ፡ ፮፡
ነገር ፡ ማድረግ ፡ የሚችለው ፡ ከሴቶች ፡ የተወ
ለደ ፡ ሰው ፡ ማነው ፡ አልሁት ፡፡
በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ቤቶች ፡ አሉ ፡ ፯፡
ብዬ ፡ ጠይቄህስ ፡ ቢሆን ፡ በጥልቅ ፡ ባሕርኑ ፡
ውስጥ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ፈሳሾች ፡ አሉ ፡ በሰማ
ይስ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጎዳና ፡ አለ ፡ የሲኦልስ ፡ ጎዳና ፡
በየት ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ የገነት ፡ ጎዳና ፡ በየት ፡ ነው ፡
ብዬ ፡ ጠይቄህስ ፡ ቢሆን ፡፡
ወደ ፡ ጥልቅ ፡ ባሕር ፡ አልወረድሁም ፡ ወደ ፡ ፰፡
ሲኦልም ፡ ፈጽሜ ፡ አልወረድሁም ፡ ወደ ፡ ሰማ
ይም ፡ አልመጣሁም ፡ ብትለኝ ፡ የተገባ ፡ ነበር ፡፡
የእሳትና ፡ የነፋስን ፡ ያለፈችውን ፡ ቀን ፡ ነገር ፡ ፱፡
ጠየቅሁህ ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ አል
ጠየቅሁህም ፡ እነሆ ፡ ማወቅን ፡ አትችልም ፡
የነዚህን ፡ ነገር ፡ የመለስክልኝ ፡ የለም ፡ አለኝ ፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



አለ ።
፲፤ በባሕርይህ ፡ ያለውን ፡ ማወቅ ፡ አልተቻለህ ።
፲፩፤ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍርዱ ፡ በለመመር
መር ፡ ተወስኗልና ፡ የእግዚአብሔር ፡ የፍርዱን ፡
ምሥጢር ፡ ማወቅ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይቻልሃል ፡
የምትፈርስ ፡ የምትበሰብስ ፡ አንተ ፡ የማይፈ
ርስ ፡ የማይበሰብስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፍርዱን ፡
ማወቅ ፡ አትችልም ።
፲፪፤ ይህን ፡ በሰማሁም ፡ ጊዜ ፡ በግምባሬ ፡ ፍግም ፡
ብዬ ፡ ወደቅሁ ፡ ስንፈጠር ፡ ተፈጥረን ፡ በኃጢ
አት ፡ ስንኖር ፡ መከራ ፡ ስንቀብል ፡ ባልተፈጠ
ርን ፡ ባልተሻለን ፡ ነበር ፡ መከራ ፡ እንድንቀበል ፡
እናውቅም ፡ አልሁ ።
፲፫፤ ታላላቁ ፡ ታናናሹም ፡ ዛፍ ፡ ሄደው ፡ ምክርን ፡
ተማከሩ ።
፲፬፤ ከፊታችን ፡ እናርቃት ፡ ዘንድ ፡ ኑ ፡ ሂደን ፡ ባሕ
ርን ፡ እንውጋት ፡ ባሕርን ፡ ወግተን ፡ ለዛፎነታ
ችን ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ እናቅና ፡ አሉ ።
፲፭፤ እንደ ፡ ዕፀው ፡ የባሕር ፡ ማዕበላትም ፡ ምክርን ፡
መከሩ ፡ ለማዕበልነታችን ፡ ሌላ ፡ ሀገር ፡ እና
ቀና ፡ ዘንድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ያለ ፡ ዛፍን ፡ እን
ወጋው ፡ ዘንድ ፡ ኑ ፡ እንገዘመት ፡ አሉ ።
፲፮፤ እሳት ፡ ወጥታ ፡ በልታቸዋለችና ፡ የዛፍ ፡ ምክሩ ፡
ከንቱ ፡ ሆነ ።]
፲፯፤ አሸዋው ፡ ገድብ ፡ ይዟታልና ፡ የባሕር ፡ ማዕበ
ልም ፡ ምክሩ ፡ እንደ ፡ ዛፍ ፡ ምክር ፡ ከንቱ ፡ ሆነ ።
፲፰፤ ፍርድ ፡ የምታውቅ ፡ ከሆነ ፡ ከነዚህ ፡ ማንን ፡
እውነተኛ ፡ ማንን ፡ ሐሰተኛ ፡ ታደርጋለህ ፡
አለኝ ።
፲፱፤ የብስ ፡ ለዛፍ ፡ ባሕር ፡ ለማዕበል ፡ ተሰጥታለችና ፡
ሁለቱም ፡ ፈራሽ ፡ ነገር ፡ አሰቡ ፡ አልሁት ።
፳፤ እውነት ፡ ነገር ፡ ፈርደህ ፡ እንደዚህ ፡ ለራስህ ፡
ለምን ፡ አትፈርድ ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ።
፳፩፤ የብስ ፡ ለዛፍ ፡ ባሕር ፡ ለማዕበል ፡ እንደ ፡ ተሰ
ጠች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎችም ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚደረገውን ፡ ምሥጢር ፡
ማወቅ ፡ ይችላሉ ፡ እንጂ ፡ የመላእክትን ፡ ምሥ
ጢር ፡ የእግዚአብሔር ፡ የጌትነቱን ፡ ፍርድ ፡
ማወቅ ፡ አይችሉም ፡ አለኝ ።
፳፪፤ አቤቱ ፡ እጠይቅሃለሁ ፡ ማወቅ ፡ የማይገባን ፡
ከሆነ ፡ በምናውቀው ፡ ገንዘብ ፡ እንግዲያ ፡ ልብ ፡
ለምን ፡ ተሰጠን ፡ ብዬ ፡ መለስኩለት ።
፳፫፤ እስራኤል ፡ ለአሕዛብ ፡ ተሰጥቷልና ፡ የወደድ
ከውም ፡ ወገን ፡ ለኃጢአተኞች ፡ ወገን ፡ ተሰ
ጥቷልና ፡ ያባቶቻችንም ፡ ኦሪት ፡ ጠፍታለ
ችና ፡ በውስጧም ፡ የተጻፈ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
የለምና ፡ ሁልጊዜ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ የሚመጣውን ፡
መከራ ፡ እመረምር ፡ ዘንድ ፡ ወደድሁ ፡ እንጂ ፡
እኔ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ እመረ
ምር ፡ ዘንድ ፡ አልወደድሁም ።
፳፬፤ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ አንበጣ ፡ ፈጥነን ፡ እን
ሄዳለንና ፡ እነዋወራችንም ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡
ነውና ፡ ሁልጊዜ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ የሚመጣውን ፡
መከራ ፡ እመረምር ፡ ዘንድ ፡ ወደድሁ ፡ እንጂ ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ፍርድ ፡ እመረምር ፡ ዘንድ ፡
አልወደድሁም ፡ እንዳናውቅ ፡ እናውቃለንና ፡
በሕሪውን ፡ አትመርምሩ ፡ ብለው ፡ ሊያስተም
ሩን ፡ አይገባም ።
ነገር ፡ ግን ፡ በኛ ፡ ስለ ፡ ተጠራ ፡ ስለ ፡ ክቡር ፡ ፳፭፤
ስሙ ፡ ምን ፡ እናደርጋለን ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ጠየ
ቅሁህ ፡ አልሁት ።
መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ በትምት ፡ ታየዋ ፳፮፤
ለህ ፡ በሕይወት ፡ ብትኖር ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡
ታውቀዋለህ ።
ጭንቅን ፡ ደዌን ፡ የተመላ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ የጻ ፳፯፤
ድቃንን ፡ ዋጋ ፡ ማስቀረት ፡ የማይቻለው ፡ ስለ
ሆነ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ያልፍ ፡ ዘንድ ፡ ይቻኩላልና ።
ስለሷ ፡ የጠየቅኸኝ ፡ ኃጢአት ፡ በዓለም ፡ ተዘር ፳፰፤
ታለችና ፡ መከራዋ ፡ ምጽዓትም ፡ አልደረሰምና ።
በርሻው ፡ ውስጥ ፡ የተዘራው ፡ መከር ፡ ካልታ ፳፱፤
ጨደ ፡ አገመራው ፡ ካልተነሣ ፡ የተዘራበት ፡
በታው ፡ ርቆ ፡ እንዳይታይ ፡ ኃጢአት ፡ የተሠ
ራችበት ፡ ይህ ፡ ዓለምም ፡ ካላለፈ ፡ ኃጢአት ፡
ከሰው ፡ ርቆ ፡ አይታይም ።
ጥንቱን ፡ ኃጢአት ፡ በአዳም ፡ ልቡና ፡ ተሠርቶ ፡ ፴፤
ነበርና ፡ የኃጢአት ፡ ፍሬ ፡ ፍዳም ፡ በዝቷልና ፡
ይህ ፡ ኃጢአቱም ፡ ሲሠራ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡
ደርሷልና ፡ መከሩም ፡ ምጽዓትም ፡ እስኪደረስ ፡
ድረስ ፡ ሰውም ፡ ሲወለድ ፡ ኃጢአቱም ፡ ሲሠራ ፡
ይኖራልና ፡ አንተ ፡ ራስህ ፡ እስኪ ፡ አስበው ።
ቀድሞ ፡ ጥቂት ፡ ኃጢአት ፡ ቢሠራ ፡ ይህን ፡ ፴፩፤
ያህል ፡ የኃጢአት ፡ ፍዳ ፡ የበዛች ።
ጥቂት ፡ በጎ ፡ ሥራስ ፡ ቢሠራ ፡ ፍጻሜ ፡ የሌ ፴፪፤
ለው ፡ ብዙ ፡ ዋጋ ፡ እንዴት ፡ በተገኘ ፡ ነበር ።
የዚህ ፡ ዓለም ፡ ዘመኑ ፡ ክፉ ፡ ነውና ፡ ጥቂት ፡ ፴፫፤
ነውና ፡ ይህ ፡ ደገኛ ፡ ዓለም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡
አለመሰጠቱ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡
መለስሁለት ።
ከእግዚአብሔር ፡ ይልቅ ፡ አንተ ፡ እጅግ ፡ የምት ፴፬፤
ቸኩል ፡ አይደለም ፡ አንተስ ፡ ስለ ፡ ራስህ ፡ ትቸ
ኩላለህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ብዙዎች ፡
ጻድቃን ፡ ይቸኩላል ።
የመንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ነገር ፡ የጻድቃን ፡ ነፍ ፴፭፤
ሳት ፡ በማደሪያቸው ፡ ሁነው ፡ ጠየቁ ፡ በዚህ ፡
እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ እንኖራለን ፡ የምግባራች
ንስ ፡ ዋጋ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚሰጠን ፡
እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ነው ።
መልአኩ ፡ ኢይሩማኤል ፡ እንደናንተ ፡ ያሉ ፡ ፴፮፤
ጻድቃን ፡ ቍጥራቸው ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡
ብሎ ፡ መለሰላቸው ።
ይህ ፡ ዓለም ፡ በሚዛን ፡ ተመዝኗልና ፡ ባሕር ፴፯፤
ንም ፡ በላዳን ፡ ሰፍሮታልና ፡ ( ዘመኑን ፡ በ፯ ፡
ሺህ ፡ ወስኖታልና ፡ ) የተሰጠው ፡ ዘመኑም ፡ እስ
ኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ዝም ፡ ይላል ፡ አያልፍም ።
አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ እነሆ ፡ እኛ ፡ ሁላችን ፡ ኃጢአ ፴፰፤
ትን ፡ የተመላን ፡ ነንና ።
የወዳጆቹን ፡ የጻድቃን ፡ የምግባራቸው ፡ ዋጋ ፡ ፴፱፤
መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ የሚከለከል ፡ ስለ ፡ ኃጢ

፲፯፡ ሰማያትን ፡ ዝቅ ፡ ያደረግሀላቸውን ፡ ምድርንም ፡
ያንዋወጥሀላቸውን ፡ ግብፅንም ፡ ያጠፋሀላቸ
ውን ፡ ጥልቅ ፡ ውሀውንም ፡ ያንዋወጥሀላቸውን ፡
በሕሩንም ፡ ያንዋወጥሀላቸውን ፡ ልጆችን ፡
ዓለም ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ፈጽመህ ፡ እንዳታ
ጠፋቸው ፡ ለዘላለሙ ፡ መሐላውን ፡ አጸናሀላ
ቸው ።
፲፰፡ ለእስራኤል ፡ ወገንና ፡ ለያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ አታ
ምልክንና ፡ ዘጠኙን ፡ ሕጊጋት ፡ ትሰጣቸው ፡
ዘንድ ፡ ንውጽውጽታና ፡ እሳት ፡ በረድና ፡
ነፋስ ፡ የሚሆኑ ፡ አራቱ ፡ የጌትነትህ ፡ ታምራ
ቶችህ ፡ ተደረጉ ።
፲፱፡ ነገር ፡ ግን ፡ የቀደመ ፡ ሰው ፡ አዳም ፡ ፈታዊ ፡
ልቡናን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጎ ፡ ነበርና ፡ በነሱ ፡
የሕግህ ፡ ሥራ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ክነሱ ፡ ክፉ ፡
አሳብን ፡ አላራቅህም ።
፳፡ ድል ፡ ተነሣ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከሱ ፡ የተወለዱ ፡ ልጆ
ችም ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ ተነሡ ፡ እንጂ ፡ ድል ፡ የተ
ነሣ ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።
፳፩፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሕግህ ፡ ጋራ ፡ ያቺ ፡ ኃጢአት ፡
ከሰኑ ፡ ክህደት ፡ ጋራ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ልቡና ፡
ፀንታ ፡ ኖረች ፡ እውነት ፡ ነገርም ፡ ጠፋች ፡
ሐሰት ፡ ግን ፡ ፀንታ ፡ ኖረች ።
፳፪፡ ዘመን ፡ አበው ፡ አለፈ ፡ ዘመን ፡ መሳፍንትም ፡
ተጨረሰ ፡ ስሙ ፡ ዳዊት ፡ የሚባል ፡ አገልጋይ
ህን ፡ ለመንግሥት ፡ አስነሣህ ።
፳፫፡ ስምህ ፡ ሊመስገንበት ፡ መሥዋዕትህን ፡ ሊሠ
ዋበት ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ሥራ ፡
አልክው ።
፳፬፡ ዘመን ፡ ነገሥት ፡ ብዙ ፡ ሆነ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሚ
ሠሩት ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ባይኖር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ በደሉ ።
፳፭፡ ፈታዊ ፡ ልቡናን ፡ ገንዘብ ፡ አድርገውታልና ፡
አዳም ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሠራ ፡ ልጆቹም ፡
ሁሉ ፡ በደሉ ።
፳፮፡ አገርህ ፡ ኢየሩሳሌምንም ፡ በጠላቶችህ ፡ በባቢ
ሎን ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ አሳልፈህ ፡ ሰጠህ ።
፳፯፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በልቡናዬ ፡ ጽዮን ፡ የምትባል ፡
ሀገርን ፡ እጅ ፡ ያደረጓት ፡ ዘንድ ፡ በባቢሎን ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ እውነት ፡ ሥራን ፡ በመሥ
ራት ፡ በውኑ ፡ ይበልጡናልን ፡ አልኩ ።
፳፰፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባቢሎን ፡ በደረስሁ ፡ ጊዜ ፡
ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ብዙ ፡ ኃጢአት ፡ ሲሠራ ፡
አየሁ ፡ ሰውነቴም ፡ ብዙ ፡ የሆኑ ፡ ከዓተኞችን ፡
አየች ፡ እነሆ ፡ ኃጢአቱም ፡ ሲሠራ ፡ ሠላሳ ፡
ዘመን ፡ ነው ፡ ኃጢአቱም ፡ በመሠራቱ ፡ ልቡ
ናዬ ፡ አደነቀ ።
፳፱፡ የባቢሎንን ፡ ሰዎች ፡ እንድትታገሳቸው ፡ አይቼ ፡
ሕግንም ፡ የዘነጉትን ፡ ሰዎች ፡ እንድትራራላ
ቸው ፡ ወገኖችህን ፡ ትተህ ፡ ጠላቶችህን ፡ እን
ድትጠብቅ ፡ አይቼ ፡ ልቡናዬ ፡ አደነቀ ።
፴፡ የማንንም ፡ ኃጢአት ፡ አልተመለከትህም ፡
የዚች ፡ ሥራ ፡ ፍጻሜዋ ፡ እንደምት ፡ ነው ፡ እው
ነት ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ባቢ
ሎን ፡ የምትበልጠው ፡ ሙብስጥ ፡ አለን ።
ከእስራኤል ፡ ሌላ ፡ ወገን ፡ ያወቀህ ፡ አለን ፡ ፴፩፡
ወይስ ፡ በሕግህ ፡ እንደ ፡ ያዕቆብ ፡ የታመነ ፡
ሌላ ፡ ወገን ፡ አለን ።
ዋጋው ፡ ያልተገለጸ ፡ ድካሙ ፡ ዋጋውን ፡ ያላ ፴፪፡
ሰጠው ፡ እንደ ፡ ያዕቆብ ፡ ሌላ ፡ ወገን ፡ አለን ፡
ወደ ፡ አሕዛብም ፡ በሄድሁ ፡ ጊዜ ፡ ሕግህን ፡ ትእ
ዛዝህን ፡ ሳይሠሩ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ አገኘኋ
ቸው ።
አሁንም ፡ በባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ ኃጢአት ፡ ዘንድ ፡ ፴፫፡
የኛ ፡ ኃጢአት ፡ የሚዛን ፡ ውልብልቢትን ፡ የም
ትመስል ፡ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ያህል ፡ በልጦ ፡
ይገኝ ፡ እንደሁ ፡ በባቢሎን ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡
ኃጢአትና ፡ የኛን ፡ ኃጢአት ፡ በሚዛን ፡ መዝን ።
ወዲያው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ፴፬፡
በፊትህ ፡ ያልበደሉ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ሕግ
ህን ፡ እንደዚህ ፡ የጠበቀ ፡ ወገን ፡ ማነው ።
ሕግህን ፡ ፈጽሞ ፡ የጠበቀ ፡ ወገንስ ፡ በዚህ ፡ ፴፭፡
ዓለም ፡ አይገኝም ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

ስሙ ፡ ዑርኤል ፡ የሚባል ፡ መልአክ ፡ ወደኔ ፡ ፩፡
የተላከ ፡ ይህ ፡ መልአክ ፡ መለሰልኝ ።
የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የጌትነቱን ፡ ፍርድ ፡ ፪፡
መርምረህ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ልቡናህ ፡ አደነ
ቀን ።
አዎን ፡ ጌታዬ ፡ አልሁት ፡ ሦስቱን ፡ ሥራዎች ፡ ፫፡
እገልጥልህ ፡ ዘንድ ፡ ሦስቱንም ፡ ምሳሌዎች ፡
በፊትህ ፡ አኖር ፡ ዘንድ ፡ ተላክሁ ፡ አለኝ ።
ከሦስቱ ፡ ምሳሌ ፡ አንዱቱ ፡ የነገርኸኝ ፡ እንደ ፡ ፬፡
ሆነ ፡ እኔም ፡ ታውቀው ፡ ዘንድ ፡ የምትወዳትን ፡
ይህችን ፡ ሥራ ፡ እነግርሃለሁ ፡ ይህ ፡ ፈታዊ ፡
ልቡና ፡ ስለምንም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስተምርሃለሁ ።
አቤቱ ፡ በል ፡ ተናገር ፡ አልሁት ፡ እሳቱን ፡ በሚ ፭፡
ዛን ፡ መዝነህ ፡ ነፋሱንም ፡ በላዳን ፡ ሰፍረህ ፡ አሳ
የኝ ፡ ( በባሕርያቸው ፡ አይሰፈሩምና ፡ ) ትላ
ንት ፡ ያለፈችውንም ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ አድር
ገህ ፡ አሳየኝ ፡ አለኝ ።
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እኔን ፡ እንደ ፡ ጠየቅኸኝ ፡ ይህን ፡ ፮፡
ነገር ፡ ማድረግ ፡ የሚችለው ፡ ከሴቶች ፡ የተወ
ለደ ፡ ሰው ፡ ማነው ፡ አልሁት ።
በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ቤቶች ፡ አሉ ፡ ፯፡
ብዬ ፡ ጠይቄህስ ፡ ቢሆን ፡ በጥልቅ ፡ ባሕርስ ፡
ውስጥ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ፈሳሾች ፡ አሉ ፡ በሰማ
ይስ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጎዳና ፡ አለ ፡ የሲኦልስ ፡ ጎዳና ፡
በየት ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ የገነት ፡ ጎዳና ፡ በየት ፡ ነው ፡
ብዬ ፡ ጠይቄህስ ፡ ቢሆን ።
ወደ ፡ ጥልቅ ፡ ባሕር ፡ አልወረድሁም ፡ ወደ ፡ ፰፡
ሲኦልም ፡ ፈጽሜ ፡ አልወረድሁም ፡ ወደ ፡ ሰማ
ይም ፡ አልመጣሁም ፡ ብትለኝ ፡ የተገባ ፡ ነበር ።
የእሳትና ፡ የነፋስን ፡ ያለፈችውን ፡ ቀን ፡ ነገር ፡ ፱፡
ጠየቅሁህ ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ አል
ጠየቅሁህም ፡ እነሆ ፡ ማወቅን ፡ አትችልም ፡
የነዚህን ፡ ነገር ፡ የመለስክልኝ ፡ የለም ፡ አለኝ ፡

አለ ።
፲፡ በባሕርይህ፡ ያለውን፡ ማወቅ፡ አልተቻለህ ።
፲፩፡ የልዑል፡ እግዚአብሔር፡ ፍርዱ፡ ባለመመር
መር፡ ተወስኗልና፡ የእግዚአብሔር፡ የፍርዱን፡
ምሥጢር፡ ማወቅ፡ እንደ፡ ምን፡ ይቻልሃል፡
የምትፈርስ፡ የምትበሰብስ፡ አንተ፡ የማይፈ
ርስ፡ የማይበሰብስ፡ የእግዚአብሔርን፡ ፍርዱን፡
ማወቅ፡ አትችልም ።
፲፪፡ ይህን፡ በሰማሁም፡ ጊዜ፡ በግምባሬ፡ ፍግም፡
ብዬ፡ ወደቅሁ፡ ስንፈጠር፡ ተፈጥረን፡ በኃጢ
አት፡ ስንኖር፡ መከራ፡ ስንቀበል፡ ባልተፈጠ
ርን፡ ባልተሻለን፡ ነበር፡ መከራ፡ እንድንቀበል፡
አናውቅም፡ አልሁ ።
፲፫፡ ታላላቁ፡ ታናናሹም፡ ዛፍ፡ ሄደው፡ ምክርን፡
ተማከሩ ።
፲፬፡ ከፊታችን፡ እናርቃት፡ ዘንድ፡ ኑ፡ ሂደን፡ ባሕ
ርን፡ እንውጋት፡ ባሕርን፡ ወግተን፡ ለዛፍነታ
ችን፡ ሌላ፡ አገር፡ እናቅና፡ አሉ ።
፲፭፡ እንደ፡ ዕፀው፡ የባሕር፡ ማዕበላትም፡ ምክርን፡
መከሩ፡ ለማዕበልነታችን፡ ሌላ፡ ሀገር፡ እና
ቅና፡ ዘንድ፡ በምድረ፡ በዳ፡ ያለ፡ ዛፍን፡ እን
ወጋው፡ ዘንድ፡ ኑ፡ እንዝመት፡ አሉ ።
፲፮፡ እሳት፡ ወጥታ፡ በልታቸዋለችና፡ የዛፍ፡ ምክሩ፡
ከንቱ፡ ሆነ ።]
፲፯፡ አሸዋው፡ ገድቦ፡ ይዟታልና፡ የባሕር፡ ማዕበ
ልም፡ ምክሩ፡ እንደ፡ ዛፍ፡ ምክር፡ ከንቱ፡ ሆነ ።
፲፰፡ ፍርድ፡ የምታውቅ፡ ከሆነ፡ ከነዚህ፡ ማንን፡
እውነተኛ፡ ማንን፡ ሐሰተኛ፡ ታደርጋለህ፡
አለኝ ።
፲፱፡ የብስ፡ ለዛፍ፡ ባሕር፡ ለማዕበል፡ ተሰጥታለችና፡
ሁለቱም፡ ፈራሽ፡ ነገር፡ አሰቡ፡ አልሁት ።
፳፡ እውነት፡ ነገር፡ ፈረድህ፡ እንደዚህ፡ ለራስህ፡
ለምን፡ አትፈርድ፡ ብሎ፡ መለሰልኝ ።
፳፩፡ የብስ፡ ለዛፍ፡ ባሕር፡ ለማዕበል፡ እንደ፡ ተሰ
ጠች፡ በዚህ፡ ዓለም፡ የሚኖሩ፡ ሰዎችም፡
በዚህ፡ ዓለም፡ የሚደረገውን፡ ምሥጢር፡
ማወቅ፡ ይችላሉ፡ እንጂ፡ የመላእክትን፡ ምሥ
ጢር፡ የእግዚአብሔር፡ የጌትነቱን፡ ፍርድ፡
ማወቅ፡ አይችሉም፡ አለኝ ።
፳፪፡ አቤቱ፡ እጠይቅሃለሁ፡ ማወቅ፡ የማይገባን፡
ከሆነ፡ በምናውቀው፡ ገንዘብ፡ እንግዳ፡ ያ፡ ልብ፡
ለምን፡ ተሰጠን፡ ብዬ፡ መለስኩለት ።
፳፫፡ እስራኤል፡ ለአሕዛብ፡ ተሰጥቷልና፡ የወደድ
ከውም፡ ወገን፡ ለኃጢአተኞች፡ ወገን፡ ተሰ
ጥቷልና፡ ያባቶቻችንም፡ ኦሪት፡ ጠፍታለ
ችና፡ በውስጧም፡ የተጻፈ፡ ቃል፡ ኪዳን፡
የለምና፡ ሁልጊዜ፡ በኛ፡ ላይ፡ የሚመጣውን፡
መከራ፡ እመረምር፡ ዘንድ፡ ወደድሁ፡ እንጂ፡
እኔ፡ ግን፡ የእግዚአብሔር፡ ፍርድ፡ እመረ
ምር፡ ዘንድ፡ አልወደድሁም ።
፳፬፡ ከዚህ፡ ዓለም፡ እንደ፡ አንበጣ፡ ፈጥነን፡ እን
ሄዳለንና፡ አነዋወራችንም፡ እንደ፡ ጢስ፡
ነውና፡ ሁልጊዜ፡ በኛ፡ ላይ፡ የሚመጣውን፡
መከራ፡ እመረምር፡ ዘንድ፡ ወደድሁ፡ እንጂ፡
የእግዚአብሔርን፡ ፍርድ፡ እመረምር፡ ዘንድ፡
አልወደድሁም፡ እንዳናውቅ፡ እናውቃለንና፡
ባሕሪውን፡ አትመርምሩ፡ ብለው፡ ሊያስተም
ሩን፡ አይገባም ።
ነገር፡ ግን፡ በኛ፡ ስለ፡ ተጠራ፡ ስለ፡ ክቡር፡ ፳፭፡
ስሙ፡ ምን፡ እናደርጋለን፡ ስለዚህ፡ ነገር፡ ጠየ
ቅሁህ፡ አልሁት ።
መለሰልኝ፡ እንዲህ፡ አለኝ፡ በትምት፡ ታየዋ ፳፮፡
ለህ፡ በሕይወት፡ ብትኖር፡ በጊዜው፡ ጊዜ፡
ታውቀዋለህ ።
ጭንቅን፡ ደዌን፡ የተመላ፡ ይህ፡ ዓለም፡ የጻ ፳፯፡
ድቃንን፡ ዋጋ፡ ማስቀረት፡ የማይቻለው፡ ስለ
ሆነ፡ ይህ፡ ዓለም፡ ያልፍ፡ ዘንድ፡ ይቸኩላልና ።
ስለ፡ የጠየቅኸኝ፡ ኃጢአት፡ በዓለም፡ ተዘር ፳፰፡
ታለችና፡ መከራዋ፡ ምጽዓትም፡ አልደረሰምና ።
በርሻው፡ ውስጥ፡ የተዘራው፡ መከር፡ ካልታ ፳፱፡
ጨደ፡ አዝመራው፡ ካልተነሣ፡ የተዘራበት፡
ቦታው፡ ርቆ፡ እንዳይታይ፡ ኃጢአት፡ የተሠ
ራችበት፡ ይህ፡ ዓለምም፡ ካላለፈ፡ ኃጢአት፡
ከሰው፡ ርቆ፡ አይታይም ።
ጥንቱን፡ ኃጢአት፡ በአዳም፡ ልቡና፡ ተሠርቶ፡ ፴፡
ነበርና፡ የኃጢአት፡ ፍሬ፡ ፍዳም፡ በዝቷልና፡
ይህ፡ ኃጢአቱም፡ ሲሠራ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ድረስ፡
ደርሷልና፡ መከሩም፡ ምጽዓትም፡ እስኪደረስ፡
ድረስ፡ ሰውም፡ ሲወለድ፡ ኃጢአቱም፡ ሲሠራ፡
ይኖራልና፡ አንተ፡ ራስህ፡ እስኪ፡ አስበው ።
ቀድሞ፡ ጥቂት፡ ኃጢአት፡ ቢሠራ፡ ይህን፡ ፴፩፡
ያህል፡ የኃጢአት፡ ፍዳ፡ የበዛች ።
ጥቂት፡ በጎ፡ ሥራስ፡ ቢሠራ፡ ፍጻሜ፡ የሌ ፴፪፡
ለው፡ ብዙ፡ ዋጋ፡ እንዴት፡ በተገኘ፡ ነበር ።
የዚህ፡ ዓለም፡ ዘመኑ፡ ክፉ፡ ነውና፡ ጥቂት፡ ፴፫፡
ነውና፡ ይህ፡ ደገኛ፡ ዓለም፡ መንግሥተ፡ ሰማይ፡
አለመሰጠቱ፡ እስከ፡ መቼ፡ ድረስ፡ ነው፡ ብዬ፡
መለስሁለት ።
ከእግዚአብሔር፡ ይልቅ፡ አንተ፡ እጅግ፡ የምት ፴፬፡
ቸኩል፡ አይደለም፡ አንተስ፡ ስለ፡ ራስህ፡ ትቸ
ኩላለህ፡ እግዚአብሔር፡ ግን፡ ስለ፡ ብዙዎች፡
ጻድቃን፡ ይቸኩላል ።
የመንግሥተ፡ ሰማይን፡ ነገር፡ የጻድቃን፡ ነፍ ፴፭፡
ሳት፡ በማደሪያቸው፡ ሁነው፡ ጠየቁ፡ በዚህ፡
እስከ፡ መቼ፡ ድረስ፡ እንኖራለን፡ የምግባራች
ንስ፡ ዋጋ፡ መንግሥተ፡ ሰማያት፡ የሚሰጠን፡
እስከ፡ መቼ፡ ድረስ፡ ነው ።
መልአኩ፡ ኢይሩማኤል፡ እንደናንተ፡ ያሉ፡ ፴፮፡
ጻድቃን፡ ቍጥራቸው፡ በተፈጸመ፡ ጊዜ፡ ነው፡
ብሎ፡ መለሰላቸው ።
ይህ፡ ዓለም፡ በሚዛን፡ ተመዝኗልና፡ ባሕር ፴፯፡
ንም፡ በላዳን፡ ሰፍሮታልና፡ ( ዘመኑን፡ በሺ፡
ሺህ፡ ወስኖታልና፡ ) የተሰጠው፡ ዘመኑም፡ እስ
ኪፈጸም፡ ድረስ፡ ዝም፡ ይላል፡ አያልፍም ።
አቤቱ፡ ጌታዬ፡ እነሆ፡ እኛ፡ ሁላችን፡ ኃጢአ ፴፰፡
ትን፡ የተመላን፡ ነንና ።
የወዳጆቹን፡ የጻድቃን፡ የምግባራቸው፡ ዋጋ፡ ፴፱፡
መንግሥተ፡ ሰማይ፡ የሚከለከል፡ ስለ፡ ኃጢ

አት ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ስለሚ
ኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ኃጢአትን ፡ ነው ፡ አልሁት ።
፵፤ መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ከተ
ፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በሆዷ ፡ ያለውን ፡ ልጅዋን ፡
ማስቀረት ፡ ይቻላት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የፀነሰች ፡
ሴትን ፡ ሂደህ ፡ ጠይቃት ፡ አለኝ ።
፵፩፤ አቤቱ ፡ አልችልም ፡ አልሁት ፡ ሲኦል ፡ መቃ
ብር ፡ አብያተ ፡ ብርሃን ፡ ግንትም ፡ እንደ ፡ ማኅ
ፀን ፡ ናቸው ።
፵፪፤ ማኅፀን ፡ ምጥ ፡ በያዛት ፡ ጊዜ ፡ ለመውለድ ፡
እንድትቸኩል ፡ መቃብርም ፡ ዓለም ፡ ከተፈ
ጠረ ፡ ጀምሮ ፡ የተቀበሩበትን ፡ ሰዎች ፡ ትሰጥ ፡
ዘንድ ፡ ትቸኩላለች ።
፵፫፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ የምትወደውን ፡
ነገር ፡ እነግርሃለሁ ፡ አለኝ ።
፵፬፤ መለስሁለት ፡ እንዲህ ፡ አልሁት ፡ በፊትህ ፡ ባለ
ሟልነትን ፡ ካገኘሁ ፡ ልጠይቅስ ፡ እንዲቻለኝ ፡
ከደረግሽኝ ፡ ይኸንን ፡ ንገረኝ ።
፵፭፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡
ባለፈው ፡ ዘመን ፡ ልክ ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ያለ
ፈው ፡ ዘመን ፡ ይበዛልን ።
፵፮፤ ያለፈውን ፡ ዘመን ፡ አውቀዋለሁና ፡ የሚመጣ
ውን ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ አላውቀውምና ፡ ይህን ፡
ንገረኝ ፡ ብዬ ፡ መለስሁለት ።
፵፯፤ የምሳሌውን ፡ ትርጓሜ ፡ አሳይህ ፡ ዘንድ ፡ በቀኝ ፡
እኩል ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሁነህ ፡ ቁም ፡ አለኝ ።
፵፰፤ ምድጃ ፡ በፊቴ ፡ እየነደደ ፡ ሲሄድ ፡ እነሆ ፡ ቆሜ ፡
አየሁ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እሳቱ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡
እነሆ ፡ ጢሱ ፡ ቆየ ።
፵፱፤ ከጢሱ ፡ በኋላ ፡ ውሀን ፡ የተመላች ፡ ደመና ፡
በፊት ፡ ሄደች ፡ ታላቅ ፡ ብዙ ፡ የሆነ ፡ ዝናምም ፡
ታዘንማለች ፡ ይህ ፡ ታላቁ ፡ ዝናምም ፡ ከዘነመ ፡
በኋላ ፡ ካፊያው ፡ ቀረ ፡ አልሁት ።
፶፤ እንግዲህ ፡ እስኪ ፡ አንተ ፡ አስበው ፡ ከካፊያው ፡
ደገኛው ፡ ዝናም ፡ እንዲበዛ ፡ ከጢሱም ፡ እሳቱ ፡
እንዲበዛ ፡ እንደዚሁ ፡ ያለፈው ፡ ዘመን ፡ ይበ
ዛል ፡ ከዝናም ፡ ካፊያው ፡ ከእሳት ፡ ጢሱ ፡ እን
ዲያንስ ፡ ካለፈውም ፡ ዘመን ፡ የሚመጣው ፡
ዘመን ፡ ያንሳል ፡ አለኝ ።
፶፩፤ እስከነዚያ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ እኖራለሁን ፡ እንጃ ፡
በነዚያስ ፡ ወራቶች ፡ ምን ፡ ይደረጋል ፡ ብዬ ፡
ማለድሁት ።
፶፪፤ መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡— ስለ ፡ ጠየቅሽኝ ፡
ነገር ፡ ምልክት ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ መንገር ፡
ይቻለኛል ፡ የዘመንህን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እነግርህ ፡
ዘንድ ፡ አልተላኩም ፡ እኔም ፡ አላውቀውም ፡
አለኝ ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩፤ ምልክቱስ ፡ እነሆ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ወራት ፡
ይመጣል ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩትንም ፡
ሰዎች ፡ ታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡ ይይዛቸዋል ፡ ምግባር ፡
ትሩፋትም ፡ የሚሠራበት ፡ አገር ፡ ትሠወራለች ፡
ሃይማኖት ፡ የሚፀናበት ፡ አገርም ፡ ትጠፋለች ።
አንተ ፡ ከየኸው ፡ ከሰማኸውም ፡ በደል ፡ የባሰ ፡ ፪፤
በደል ፡ ይሠራል ።
በአዝርዕት ፡ በአትክልት ፡ አምሮ ፡ የምታየው ፡ ፫፤
ይህም ፡ ዓለም ፡ የጠፋ ፡ የፈረሰ ፡ ሆኖ ፡ ያል
ፋል ፡ ምድርም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ትሆናለች ።
እግዚአብሔር ፡ሕይወትን ፡ ከሰጠህ ፡ ከሦስት ፡ ፬፤
ዓመት ፡ በኋላ ፡ ምድርን ፡ በመከራ ፡ ስትታ
ወክ ፡ታያታለህ ፡ ፀሐይም ፡ ድንገት ፡ በሌሊት ፡
ያበራል ፡ ጨረቃም ፡ ድንገት ፡ በቀን ፡ ያበራል ።
ከእንጨቶችም ፡ (በተአምራት ፡ ) ደም ፡ ይፈ ፭፤
ሳል ፡ ደንጊያም ፡ (በተአምራት ፡ ) ትጮሃለች ፡
ሕዝቡም ፡ ይታወከሉ ፡ ከዋክብትም ፡ ይረግ
ፋሉ ።
ይነግሣል ፡ ብለው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ያልጠረጠ ፮፤
ሩት ፡ ሐሣዊ ፡ መሲሕ ፡ ይነግሣል ።
ከሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ወረድሁ ፡ ከድንግል ፡ ማር ፯፤
ያም ፡ ተወለድሁ ፡ ሲል ፡ ሁሉ ፡ ቃሉን ፡ ይሰ
ማል ።
በየሀገሩ ፡ ኸብር ፡ ይሆናል ፡ እሳትም ፡ ከሰማይ ፡ ፰፤
ተጠቅሎ ፡ ይወርዳል ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አውሬ
ዎችም ፡ በታቸውን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡
ይገባሉ ፡ ከሴቶችም ፡ ሽብቶ ፡ ጥርስ ፡ አውጥቶ ፡
ይወለዳል ።
የሚጣፍጠውም ፡ ውሀ ፡ ይመራል ፡ ወዳጆችም ፡ ፱፤
እንደ ፡ ጠላት ፡ ድንገት ፡ እርስበርሳቸው ፡ ይጋደ
ላሉ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጥበብ ፡ ትሠወራለች ፡ ምክርም ፡
ወደ ፡ ማደሪያዋ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትመ
ለሳለች ።
በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ይፈልጓታል ፡ ነገር ፡ ፲፤
ግን ፡ አያገኟትም ፡ በዚህ ፡ ዓለምም ፡ ኃጢአት ፡
ስንፍና ፡ ትበዛለች ።
ከንዲቱ ፡ አገር ፡ አቅራቢያዋን ፡ አንዲቱን ፡ ፲፩፤
ሀገር ፡ በውኑ ፡ አንቺ ፡ ያለፈ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ አለን ፡
ወይስ ፡ እውነት ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ አለን ፡ ብላ ፡
ትጠይቃታለች ፡ ያችም ፡ የለም ፡ ትላታለች ።
በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ሰው ፡ ሞትን ፡ ይመኛል ፡ ፲፪፤
አያገኝም ፡ ሚስት ፡ ያገባል ፡ ፈቃዱ ፡ ተፈጽሞ
ለት ፡ ደስ ፡ አይለውም ፡ በሥራው ፡ ይደክማል ፡
ሥራውንም ፡ ይሠራል ፡ ሥራው ፡ ግን ፡ አይከ
ናወንለትም ።
ይኸን ፡ ምልክት ፡ እነግርህ ፡ ዘንድ ፡ ተላክሁ ፡ ፲፫፤
ዛሬ ፡ እንደ ፡ ጾምህ ፡ ዳግመኛ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡
አልቅሰህ ፡ ብትጸልይ ፡ የሚበልጥ ፡ ዳግመኛ ፡
ከዚህ ፡ የሚበልጥ ፡ ትሰማለህ ።
ከንቅልፌ ፡ ተቀሰቀስሁ ፡ ሰውነቴ ፡ እጅግ ፡ ስቅ ፲፬፤
ጥጥ ፡ ስቅጥጥ ፡ አለብኝ ፡ ሰውነቴም ፡ እስከት
ዝል ፡ ድረስ ፡ ደከመች ።
ወደኔ ፡ የመጣ ፡ የተናገረኝ ፡ ያ ፡ መልአክ ፡ እጄን ፡ ፲፭፤
ያዘኝ ፡ በእግሬም አቁሞ ፡ አፀናኝ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሁለተኛይቱ ፡ ሌሊት ፡ የሕዝቡ ፡ ፲፮፤
ያለቆቻቸው ፡ አለቃ ፡ ፍልስጥያል ፡ ወደኔ ፡
መጣ ፡ አንተ ፡ ወዴት ፡ ነህ ፡ ፊትህስ ፡ ስለምን ፡
አዝኗል ።
እስራኤልን ፡ ባስማረኳቸው ፡ ሀገር ፡ በባቢሎን ፡ ፲፯፤

በእስራኤል ፡ ዘንድ፡ በመምርነት ፡ እንደ ፡ ታመ
ንክ ፡ አታውቅምን ፡ አለኝ ።
፲፰፡ ተነሥተህ ፡ እንግዲህስ ፡ እህል ፡ ቅመስ ፡ እስራ
ኤልን ፡ እንዳትጥላቸው ፡ መንጋዎችን ፡ በክፉ
ዎች ፡ ተኵላት ፡ አፍ ፡ እንደ ፡ ጣለ ፡ እንደ ፡ እረ
ኛም ፡ እንዳትሆን ፡ ወይም ፡ የሆነውን ፡ ተነሥ
ተህ ፡ ቅመስ ፡ አለኝ ።
፲፱፡ ከኔ ፡ ተለይትህ ፡ ሂድ ፡ ዳግመኛም ፡ እስከ ፡
ሰባት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ወደኔ ፡ አትምጣ ፡ ከሰባት ፡
ቀን ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ወደኔ ፡ ና ፡ እኔም ፡ ነገርን ፡
እነግርሃለሁ ፡ አለው ፡ ከኔ ፡ ተለይቶ ፡ ሄደ ።
፳፡ መልአኩ ፡ ዑርኤል ፡ እንዳዘዘኝ ፡ እኔም ፡ አዝኜ ፡
እያለቀስሁ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ጾምሁ ።
፳፩፡ ከሰባት ፡ ቀን ፡ በኋላም ፡ የልቡናየ ፡ አሳብ ፡
እጅግ ፡ አደከመኝ ።
፳፪፡ ጥበብን ፡ የምትገልጽ ፡ ሥልጣንም ፡ ሰውነቴን ፡
አራቀቀቻት ፡ ዳግመኛም ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊትም ፡ እናገር ፡ ጀመርሁ ።
፳፫፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ካሉ ፡ ከታላላቁ ፡
ከተናናሾቹም ፡ እንጨቶች ፡ አንድ ፡ የወይን ፡
ሐረግን ፡ መረጥህ ።
፳፬፡ ከዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ፈሳሾች ፡ ይልቅ ፡ ፩ ፡ ዮርዳኖ
ስን ፡ መረጥህ ።
፳፭፡ ከሀገሮችም ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ የእስራኤል ፡ አገ
ርን ፡ መረጥህ ፡ በሀገሩ ፡ ሁሉ ፡ ከታነጹ ፡ ምኵ
ራቦችም ፡ አንድ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ መረጥህ ።
፳፮፡ ከተፈጠሩ ፡ ወፎችም ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ርግብን ፡
መረጥህ ፡ ከተፈጠሩት ፡ ከመንጋዎቹም ፡ ሁሉ ፡
አንድ ፡ በግን ፡ መረጥህ ።
፳፯፡ ከአሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ ሕግህን ፡ ያስተማርከው ፡
አንድ ፡ እስራኤልን ፡ መረጥህ ፡ ከሁሉ ፡ የወደ
ድከው ፡ ወገን ፡ እስራኤልን ፡ ግን ፡ ለአሕዛብ ፡
አሳልፈህ ፡ ሰጠኸው ።
፳፰፡ አሁንም ፡ አቤቱ ፡ ይህንን ፡ አንድ ፡ እስራኤልን ፡
ለብዙ ፡ አሕዛብ ፡ አሳልፈህ ፡ ለምን ፡ ሰጠኸው ፡
ልዩ ፡ ከሚሆኑ ፡ ከአሕዛብ ፡ ለይተህ ፡ አንድ ፡
ወገን ፡ እስራኤልን ፡ አገልግሎልከው ፡ ወልድየ ፡
ዘበኵርየ ፡ ያልከው ፡ እስራኤልንም ፡ ከአሕ
ዛብ ፡ ለይተህ ፡ በአሕዛብ ፡ አገር ፡ በተንከው ።
፳፱፡ የሕግህ ፡ ባለጋራዎቹ ፡ በሕግህ ፡ የታመኑ ፡ እስ
ራኤልን ፡ አጠፏቸው ።
፴፡ ወገኖችህ ፡ እስራኤልንስ ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ በአሕ
ዛብ ፡ እጅ ፡ ስትጥላቸው ፡ አንተ ፡ በሥልጣንህ ፡
ብታጠፋቸው ፡ ይሻላል ።
፴፩፡ ይኸንንም ፡ ቃል ፡ ታናግሬ ፡ ባለፈችው ፡ በዚ
ያች ፡ ሌሊት ፡ አስቀድሞ ፡ የመጣው ፡ ያ ፡ መል
አክ ፡ ወደኔ ፡ ተላከ ።
፴፪፡ ስማኝ ፡ ልንገርህ ፡ አድምጠኝ ፡ ዳግመኛም ፡
በፊትህ ፡ ልናገር ፡ አለኝ ።
፴፫፡ አቤቱ ፡ በል ፡ ተናገር ፡ አልሁት ፡ ይህ ፡ መከራ ፡
ለእስራኤል ፡ ድንቅ ፡ ነውን ፡ በኃጢአታቸው ፡
የመጣባቸው ፡ አይደለምን ፡ ከፈጣሪው ፡ ይልቅ ፡
ወይስ ፡ እስራኤልን ፡ አንተ ፡ ወደድኸውን ፡
አለኝ ።

አቤቱ ፡ የእስራኤል ፡ መከራ ፡ ስላተጋኝ ፡ ሁል ፴፬፡
ጊዜም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ መርምሬ ፡
አውቅ ፡ ዘንድ ፡ የፍርዱንም ፡ ምሥጢር ፡ መር
ምሬ ፡ አውቅ ፡ ዘንድ ፡ ኵላሊቴን ፡ ስላተጋኝ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ ከፈጣሪያቸው ፡ ይልቅ ፡ እስራኤ
ልን ፡ የምወዳቸው ፡ አይደለሁም ፡ አልሁት ።
የጌትነቱን ፡ ፍርድ ፡ ማወቅ ፡ አትችልም ፡ አለኝ ፡ ፴፭፡
አቤቱ ፡ የጌትነቱን ፡ ፍርድ ፡ አለማወቄ ፡ ስለም
ንድን ፡ ነው ፡ ስለ ፡ ምንስ ፡ ተወለድሁ ፡ የሁለ
ቱን ፡ ነገድ ፡ መከራ ፡ ያሥራንም ፡ ነገድ ፡ መከራ ፡
እንዳላይ ፡ የናቴ ፡ ማኅፀንስ ፡ ስለምን ፡ መቃ
ብር ፡ አልሆነኝም ፡ አልሁት ።
ገና ፡ ያልመጣ ፡ ቀንን ፡ ቍጠር ፡ የተበተነውንም ፡ ፴፮፡
አበባ ፡ ሰብስብልኝ ፡ የደረቀውንም ፡ ሣር ፡ አለ
ምልምልኝ ።
የተዘጉትን ፡ ቤቶች ፡ ክፈቱልኝ ፡ በዚያም ፡ የተ ፴፯፡
ዘጉት ፡ ነፍሳትን ፡ አምጥተህ ፡ ከሞቱ ፡ ጀምሮ ፡
ፊታቸውን ፡ ያላየሁትን ፡ ነፍሳትን ፡ ከሥጋ
ቸው ፡ አዋሕደህ ፡ አሳየኝ ፡ ቃላቸውንም ፡ አሰ
ማኝ ፡ በሚገባ ፡ ያገኛቸውን ፡ መከራ ፡ የዚያን ፡
ጊዜ ፡ እነግርሃለሁ ፡ አለኝ ።
አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ እነዋወሩ ፡ ከሰው ፡ ልዩ ፡ ከሆነ ፡ ፴፰፡
መልአክ ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ ምሥጢር ፡ ማወቅ ፡
የሚችል ፡ ማነው ፡ አልሁት ።
እኔ ፡ ያላዋቂ ፡ የተዋረድሁ ፡ ነኝ ፡ ይህን ፡ የም ፴፱፡
ትጠይቀኝን ፡ ነገር ፡ መናገር ፡ እንዴት ፡ እችላ
ለሁ ።
እኔ ፡ ከምነግርህ ፡ ከሊህ ፡ አንዱን ፡ መናገር ፡ እን ፵፡
ዳትችል ፡ እንደዚሁ ፡ የጌትነቱን ፡ ፍርድ ፡
ማወቅ ፡ አትችልም ፡ ስለ ፡ ወገኖቹ ፡ ስለ ፡ እስራ
ኤል ፡ የምታገሠው ፡ የፍቅሬንም ፡ መጨረሻ ፡
መንግሥት ፡ ሰማይን ፡ መመርመር ፡ አይቻል
ህም ፡ አለኝ ።
አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ እነሆ ፡ አንተ ፡ ስለሳቸው ፡ መን ፵፩፡
ግሥት ፡ ሰማያትን ፡ ከመስጠት ፡ ታገሥህ ፡ ከኛ ፡
አስቀድሞ ፡ የተነሡ ፡ ከኛም ፡ በኋላ ፡ የሚነሡ ፡
ሰዎች ፡ ምን ፡ ያደርጋሉ ፡ አልሁት ።
በዘመን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ያሉት ፡ እንዳይዘገዩ ፡ የቀ ፵፪፡
ደሙትም ፡ ፈጥነው ፡ እንዳይነሡ ፡ ፍርዴን ፡
እንደ ፡ ቀለበት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አደረግኋት ፡
አለኝ ።
ፍርድህን ፡ ፈጥነህ ፡ ታሳይ ፡ ዘንድ ፡ በዘመን ፡ ፵፫፡
የቀደሙትን ፡ በዘመን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ያሉትን ፡
አሁንም ፡ ያሉትን ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ አድ
ርገህ ፡ መፍጠር ፡ በውኑ ፡ ባልተቻለህም ፡ ነበ
ርን ፡ አልሁት ።
ሥራ ፡ ከሠሪው ፡ ፈጽሞ ፡ የሚቸኩል ፡ አይደ ፵፬፡
ለም ፡ ዓለምም ፡ በውስጧ ፡ የተፈጠሩትን ፡ ፍጥ
ረታት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢፈጠሩ ፡ ባልቻለቻቸ
ውም ፡ ነበር ፡ አለኝ ።
በየጊዜው ፡ የፈጠርሃቸውን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እን ፵፭፡
ድታስነሣቸው ፡ አቤቱ ፡ ለኔ ፡ ለባሪያህ ፡ ለምን ፡
ነገርኸኝ ፡ አልሁት ፡ በየጊዜው ፡ የፈጠርካቸው
ንስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥነህ ፡ የምታስነሣቸው ፡

ከሆነ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ይጨነቃል ፡ ይህም ፡ ባይ
ሆን ፡ ዛሬ ፡ ካሉት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ የሚኖሩትን ፡
ሰዎች ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ማስገኘት ፡ ባልተቻለ
ውም ፡ ነበር ።
፵፮፤ የምትወልድ ፡ ሴት ፡ ማኅፀንን ፡ እስኪ ፡ እሺ ፡
አሰኛት ፡ ዓሥር ፡ ልጆች ፡ ስትወልጂ ፡ አንድ ፡
ጊዜ ፡ አትወልጂምን ፡ በመት ፡ በመት ፡ ለምን ፡
ትወልጃለሽ ፡ በላት ።
፵፯፤ በመት ፡ በመቱ ፡ ትወልዳለች ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡
ጊዜ ፡ መውለድ ፡ አትችልምና ፡ ዓሥሩን ፡ ልጆ
ቿን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ትሰጥ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንግ
ዲህ ፡ ጠይቃት ።
፵፰፤ የወላድ ፡ ማኅፀንም ፡ ዓሥሩን ፡ ልጆቿን ፡ ፈጽማ ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ ማስገኘት ፡ እንዳትችል ፡ ያረጀች ፡
የሆነች ፡ ይህችም ፡ ዓለም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ማስ
ገኘት ፡ አይቻላትም ፡ እኔም ፡ እንደዚሁ ፡ የፈጠ
ርሁትን ፡ ይህንን ፡ ዓለም ፡ በየጊዜው ፡ አዘጋ
ጀሁት ፡ አለኝ ።
፵፱፤ በፊትህ ፡ በምናገር ፡ ግንዛብ ፡ ምክንያት ፡ ሰጥ
ተኸናልና ፡ እነሆ ፡ በውነት ፡ አንተ ፡ ቆንጆ ፡
የነበረች ፡ እናታችሁ ፡ ይህች ፡ ዓለም ፡ ዛሬ ፡
ፈጽማ ፡ አረጀች ፡ አልከኝ ፡ ኃይላችን ፡ እንደ ፡
ቀደሙት ፡ ሰዎች ፡ ያልሆነልን ፡ ለምንድን ፡
ነው ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።
፶፡ መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ልጅ ፡ የወለደች ፡
ሴትን ፡ ጠይቃት ፡ ትነግርሃለች ።
፶፩፤ በኃይል ፡ ይደክማሉ ፡ እንጂ ፡ ዛሬ ፡ የወለድሻ
ቸው ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ወለድሻቸው ፡ ለምን ፡
አልሆኑም ፡ በላት ።
፶፪፤ በቆንጅና ፡ የተወለደ ፡ ልጅ ፡ ልዩ ፡ ኃይል ፡ ነው ፡
በርጅና ፡ የተወለደው ፡ ልዩ ፡ ደካማ ፡ ነው ፡
ትልሃለች ።
፶፫፤ እንዲህ ፡ ትለኛለህ ፡ እንጂ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከቀደ
ሙት ፡ ሰዎች ፡ እናንተ ፡ በኃይል ፡ እንድታንሱ ፡
አንተም ፡ ታውቀዋለህ ።
፶፬፤ ከናንተም ፡ በኋላ ፡ የሚወለዱ ፡ ሰዎች ፡ በኃ
ይል ፡ እንዲያንሱ ፡ ታውቀዋለህ ፡ እንደዚሁ ፡
ቀድሞ ፡ ተፈጥሮ ፡ የነበረ ፡ የሚኖር ፡ ይህም ፡
ዓለም ፡ የሕፃንነት ፡ ዘመን ፡ ከለፈ ፡ ወዲያ ፡ እን
ዲደክም ፡ ኋላም ፡ የተፈጠረው ፡ ኃይሉ ፡ ይደ
ክማል ፡ አለኝ ።
፶፭፤ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ እሺ ፡ በለኝ ፡ በፊትህ ፡ በለሟ
ልነትን ፡ ከገኘሁ ፡ ለኔ ፡ ለባርያህ ፡ ንገረኝ ፡ ይህን ፡
ዓለም ፡ በማን ፡ አድረህ ፡ ትጐበኘዋለህ ፡ አል
ሁት ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩፤ መጀመሪያ ፡ በነቢያት ፡ አድሬ ፡ ኋላ ፡ እኔ ፡ ሰው ፡
ሁኜ ፡ ሥጋ ፡ ለብሼ ፡ አስተምራለሁ ፡ አለኝ ፡
ምድርና ፡ ሰማይ ፡ ሳይፈጠሩ ፡ መንደር ፡ መንድ
ረው ፡ የሚኖሩትም ፡ ሳይፈጠሩ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡
ሥራም ፡ ሳይፀና ፡ የነፋሳት ፡ አካልም ፡ ሳይፈ
ጠሩ ።
፪፤ የነጐድጓድ ፡ ድምፅም ፡ ሳይሰማ ፡ የፀሐይ ፡ ብር
ሃንም ፡ ሳይፈጠር ፡ የገነትም ፡ ምድር ፡ ሳይፈ
ጠር ።
ያበባውም ፡ ደም ፡ ግበት ፡ ሳይታይ ፡ የጠፈር ፡ ፫፤
ኃይልም ፡ ሳይፀና ፡ ነገደ ፡ መላእክትም ፡ ሳይ
ቈጠሩ ።
የሰማይም ፡ ምጥቀቱ ፡ ሳይታይ ፡ ሰበቱ ፡ ሰማያ ፬፤
ትም ፡ ሳይቈጠሩ ።
የሚመጣው ፡ ዓለም ፡ የመንግሥት ፡ ሰማይ ፡ ፭፤
ምሥጢር ፡ ሳይታወቅ ፡ ሃይማኖትን ፡ የሚያፀ
ኗት ፡ ሰዎች ፡ በልባ ፡ ሥላሴ ፡ ሳይቈጠሩ ።
የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፍጡር ፡ ያይደለሁ ፡ እኔ ፡ ይህን ፡ ፮፤
ዓለም ፡ እጐበኝ ፡ ዘንድ ፡ አሰቤአለሁና ፡ ቀድሞ ፡
በነቢያት ፡ አድሬ ፡ ኋላ ፡ እኔ ፡ ሰው ፡ ሁኜ ፡ ሥጋ ፡
ለብሼ ፡ አስተምራለሁ ፡ አለኝ ።
ምልክቱም ፡ ምንድነው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ጊዜው ፡ ፯፤
መጨረሻው ፡ መቼ ፡ ነው ፡ የሁለተኛው ፡ ዓለም ፡
መንግሥት ፡ ሰማይስ ፡ የሚሰጥበት ፡ ጊዜው ፡
መቼ ፡ ነው ፡ ብየ ፡ ጠየቅሁት ።
አብርሃም ፡ ይስሐቅን ፡ ወለደ ፡ ኤሳውና ፡ ያዕ ፰፤
ቆብ ፡ ከሱ ፡ ተወልደዋልና ።
ያዕቆብ ፡ የሁለተኛው ፡ ዓለም ፡ የመንግሥት ፡ ፱፤
ሰማይ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።
የሰው ፡ መጨረሻው ፡ አከሉ ፡ ወደታች ፡ እግሩ ፡ ፲፤
ነውና ፡ ወደ ፡ ላይም ፡ ራሱ ፡ ነውና ፡ ያዕቆብ ፡
የኤሳውን ፡ እግር ፡ ይዞ ፡ ሲወለድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡
እንደሆነ ፡ በመካከሉ ፡ ሌላ ፡ እንደሌለ ፡ መንግ
ሥት ፡ ሰማያት ፡ ስትሰጥ ፡ ይህች ፡ ዓለም ፡
ስታልፍ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።
ነገር ፡ ግን ፡ ዕዝራ ፡ አትመርምር ፡ አለኝ ፡ መለ ፲፩፤
ስሁለት ፡ እንዲህ ፡ አልሁት ፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡
በፊትህ ፡ በለሟልነትንስ ፡ ከገኘሁ ።
በቀኝ ፡ እዠል ፡ በንድ ፡ ወገን ፡ ሁኜ ፡ ሳለሁ ፡ ባለ ፲፪፤
ፈው ፡ ሌሊት ፡ አስቀድሞ ፡ የነገርኸኝን ፡ የዚህ ፡
የምልክቱን ፡ መጨረሻ ፡ ለኔ ፡ ለባርያህ ፡ ንገ
ረኝ ፡ ብዬ ፡ መለስሁለት ።
መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ተነሥተህ ፡ በእግ ፲፫፤
ርህ ፡ ቁም ፡ ጩኸት ፡ የተመላበትን ፡ ቃል ፡
እነግርሃለሁ ።
መነዋወጥ ፡ አንተ ፡ የቆምህበት ፡ ቦታ ፡ ቢነዋ ፲፬፤
ወፅ ፡ መነዋወፁ ፡ የኅልፈት ፡ ምልክት ፡ ነውና ፡
በነገርሁህ ፡ ጊዜ ፡ አትደንግጥ ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ የምድር ፡ መሠረቶች ፡ የኅልፈትን ፡ ፲፭፤
ምልክት ፡ ያስረዳሉ ።
መነዋወጡ ፡ ስለነሳቸው ፡ ነውና ፡ ይንቀጠቀ ፲፮፤
ጣሉ ፡ ይነዋወጣሉ ፡ በመጨረሻቸው ፡ ያልፉ ፡
ዘንድ ፡ አላቸውና ፡ ይነዋወፃሉ ፡ አለኝ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቼ ፡ ፲፯፤
በእግሮቼ ፡ ቆምኩ ፡ የሚናገረውን ፡ ቃል ፡ እነሆ ፡
ሰማሁ ፡ ድምፁም ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውሀ ፡ ድምፅ ፡
ነው ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይጎ ፲፰፤
በኛቸው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡
የሚጎበኝበት ፡ ዘመን ፡ እነሆ ፡ ይመጣል ፡ ይላል ።
ኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊት ፡ በምትታነፅበት ፡ ጊዜ ፡ ፲፱፤

የበደሉኝን፡ ሰዎች፡ኃጢአታቸውን፡እመረም
ራቸው ፡ ዘንድ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አለኝ ።
፳፤ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ መንግሥት ፡ ሰማይ ፡
በተሰጠ ፡ ጊዜ ፡ የማደርገው ፡ ምልክት ፡ ይህ ፡
ነው ፡ በሰማይ ፡ ብሉያት ፡ ሐዲሳት ፡ ይነበቡሉ ፡
መልኬንም ፡ ሁሉ ፡ ያየኛል ።
፳፩፤ ተወልደው ፡ ዓመት ፡ የሆናቸው ፡ ሕፃናት ፡ ፈጽ
መው ፡ ይናገራሉ ፡ ከፀነሱ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ አንድ ፡
ወር ፡ ሲሆናቸው ፡ የሞቱ ፡ ሴቶች ፡ ከልጆቻ
ቸው ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ ይነሣሉ ።
፳፪፤ የማትታይ ፡ መንግሥት ፡ ሰማይ ፡ ጻድቃን ፡
ወርሰዋት ፡ ተዘርተውባት ፡ ትታያለች ፡ በጥ
ንት ፡ በኸርማት ፡ የተመሉ ፡ መቃብራት ፡ በዱ
ቸውን ፡ ይቀራሉ ።
፳፫፤ ረቂቅ ፡ ነጋሪት ፡ ይሰማል ፡ የሰማውም ፡ ሁሉ ፡
ይደነግጣል ።
፳፬፤ በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ወዳጆች ፡ ከወዳጆቻቸው ፡
ጋራ ፡ እስበሳቸው ፡ እንደ ፡ ጠላት ፡ ይጣላሉ ።
ምድርም ፡ በውስጧ ፡ የሚኖሩባትን ፡ ሰዎች ፡
ታስደነግጣቸዋለች ፡ የውሀው ፡ ፈሳሾችም ፡
ይገታሉ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ አይፈ
ሱም ።
፳፭፤ ከዚህ ፡ ከነገርሁህ ፡ ሁሉ ፡ የቀረ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
የሚድን ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ትድግናየን ፡ የዘመኔንም ፡
ፍጻሜ ፡ የሚያይ ፡ እሱ ፡ ነው ።
፳፮፤ ወደ ፡ ገነት ፡ የወጡ ፡ ከተወለዱም ፡ ጀምሮ ፡
ሞትን ፡ ያልቀመሱ ፡ እነዚህን ፡ ሄኖክንና ፡ ኤል
ያስን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ያይዋቸዋል ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎችም ፡ ልቡና ፡ በውቀት ፡ ይለወ
ጣል ፡ አዋቂ ፡ ልቡናም ፡ ይሰጣቸዋል ።
፳፯፤ ክፋት ፡ ትጠፋለችና ፡ ተንኮልም ፡ ትጠፋለችና ።
፳፰፤ ሃይማኖት ፡ ትጸናለች ፡ ሞት ፡ ድል ፡ ይነሣል ፡
ዋጋ ፡ ሳታሰጥ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ የነበረች ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ዋጋ ፡ በማሰጠት ፡ ትገለጣ
ለች ።
፳፱፤ በተናገረኝም ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ እያለ ፡
እኔ ፡ የቆምሁበት ፡ ቦታ ፡ ይነዋወጣል ።
፴፤ ባለፈችው ፡ ሌሊት ፡ እነግርህ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡
መጣሁ ፡ ይህን ፡ ምልክት ፡ እነግርህ ፡ ዘንድ ፡
መጣሁ ፡ አለኝ ።
፴፩፤ ዳግመኛ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ የጾምህ ፡ የጸለይክ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ልመናህ ፡
ተሰምቷልና ።
፴፪፤ ከሕፃንነትህ ፡ ጀምሮ ፡ የሠራኸው ፡ የውነተኛ
ነትህ ፡ ሥራ ፡ ተገልጧልና ፡ ከዚህ ፡ ከነገርኩህ ፡
ነገር ፡ የሚበልጥ ፡ ዳግመኛ ፡ እነግርሃለሁ ።
፴፫፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እነግርህ ፡ ዘንድ ፡
እግዚአብሔር ፡ ላከኝ ።
፴፬፤ እመን ፡ አትፍራ ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ እንዳትጠራ
ጠር ፡ ስለቀደመው ፡ ስለክፉውም ፡ አሳብህ ፡
አትቸኩል ፡ አለኝ ።
፴፭፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የነገረኝ ፡ ሦስቱን ፡ ሱባዔ ፡ እጨ
ርስ ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ እያለቀስኩ ፡
ጾምኩ ።
ሰውነቴ ፡ ፈጽማ ፡ ትናደዳለችና ፡ ልቡናየም ፡ ፴፮፤
ትነዋወጣለችና ።
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እናገር ፡ ጀመርሁ ። ፴፯፤
አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ በመጀመሪያው ፡ መፍጠርህ ፡ ፴፰፤
በመጀመሪያይቱ ፡ ቀን ፡ ምድርና ፡ ሰማይ ፡
ይፈጠር ፡ አልክ ፡ እንዳልክ ፡ ተፈጥሬአለሁ ፡
ቃልህም ፡ ፍጥረትን ፡ ይፈጥር ፡ ነበር ።
የአራዊት ፡ የእንስሳ ፡ ድምፅ ፡ የለም ፡ ነበርና ፡ ፴፱፤
ዳግመኛ ፡ የሰው ፡ ድምፅ ፡ አልነበረምና ፡ ነፋሱ ፡
በውሀው ፡ ላይ ፡ ይዋኝ ፡ ነበር ፡ ጨለማም ፡ በዓ
ለሙ ፡ የተመላ ፡ ነበር ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ነበር ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ ብርሃን ፡ ከባሕርይህ ፡ ይገኝ ፡ አልህ ፡ ፵፤
ፍጥረትህም ፡ ይገለጥ ፡ አልህ ።
ዳግመኛም ፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ በሰማይ ፡ ያለ ፡ ፵፩፤
ነፋስን ፡ ፈጠርክ ፡ እኩሌታው ፡ ወደላይ ፡ ይወጣ ፡
ዘንድ ፡ እኩሌታውም ፡ በታች ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡
በውሀው ፡ መካከል ፡ ወሰን ፡ ይለይ ፡ ዘንድ ፡ አዘ
ዝከው ።
በሦስተኛይቱ ፡ ቀን ፡ ውሀውን ፡ በሰባተኛይቱ ፡ ፵፪፤
ዕጣ ፡ በምድር ፡ ይወሰን ፡ ዘንድ ፡ አዘዝከው ፡
ያርሱ ፡ ዘንድ ፡ ዘርም ፡ ይዘሩ ፡ ዘንድ ፡ በፊትህም ፡
ፀንተው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ የምድር ፡ ስድስተኛ
ይቱ ፡ ዕጣ ፡ ደረቅ ፡ ሁኖ ፡ ይቅር ፡ አልህ ።
ቃልህም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ፍጥረት ፡ ይፈጠር ፡ ፵፫፤
ነበር ።
የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ መዓ ፵፬፤
ዛው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ያበባውም ፡
መልኩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነው ፡ ሁሉ ፡ የእንጨቱ ፡
መልኩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ መዓዛውም ፡
ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ተፈጠረ ።
ባራተኛይቱ ፡ ቀን ፡ ሊያበሩ ፡ የጨረቃና ፡ የፀ ፵፭፤
ሐይ ፡ ብርሃን ፡ ይፈጠር ፡ ዘንድ ፡ የከዋክብትም ፡
ብርሃን ፡ ይፈጠር ፡ ዘንድ ፡ አዘዝህ ።
ይፈጠር ፡ ዘንድ ፡ ነቢይ ፡ አዳምን ፡ ያገለግሉ ፡ ፵፮፤
ዘንድ ፡ አዘዝሃቸው ።
በምስተኛይቱም ፡ ቀን ፡ የናጌብ ፡ ውሃ ፡ ያለበ ፵፯፤
ትን ፡ ይኸን ፡ ሰባተኛውን ፡ እጅ ፡ ደመ ፡ ነፍስ ፡
ደጓነኛ ፡ የሚሆኑ ፡ ዓሣዎቹንና ፡ ወፎችን ፡ ያስ
ገኝ ፡ ዘንድ ፡ አዘዝከው ።
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ጌትነትህን ፡ ፵፰፤
ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ የማይናገር ፡ ደመ ፡ ነፍስ ፡ የሌ
ለው ፡ ያ ፡ ውሀ ፡ ደመ ፡ ነፍስ ፡ ያለውን ፡ አስገኘ ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ የፈጠርሃቸው ፡ ሁለቱን ፡ እንስሳት ፡ ፵፱፤
አኖርክ ፡ ያንዱን ፡ ስሙን ፡ ብሔሞት ፡ አልከው ፡
የሁለተኛውንም ፡ ስሙን ፡ ሌዋታን ፡ አልከው ።
የናጌብ ፡ ውሀ ፡ ያለበት ፡ ይህ ፡ ሰባተኛው ፡ እጅ ፡ ፶፤
ብሔሞትና ፡ ሌዋታንን ፡ መወሰን ፡ አይችል
ምና ፡ ብሔሞትና ፡ ሌዋታንን ፡ ለየብቻቸው ፡
ለየሃቸው ።
አራቱ ፡ ተራሮች ፡ ባሉበት ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ እሱ ፡ ፶፩፤
በውስጡ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ለብሔሞት ፡ ከስድ
ስተኛው ፡ እጅ ፡ አንዱን ፡ እጅ ፡ የብስን ፡ ሰጠ
ኸው ።
ሰባተኛዋንም ፡ እጅ ፡ ባሕሩን ፡ ለሌዋታን ፡ ሰጠ ፶፪፤

ከሆነ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ይጨነቃል ፡ ይህም ፡ ባይ
ሆን ፡ ዛሬ ፡ ካሉት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ የሚኖሩትን ፡
ሰዎች ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ማስገኘት ፡ ባልተቻለ
ውም ፡ ነበር ።
፵፮ የምትወልድ ፡ ሴት ፡ ማኅፀንን ፡ እስኪ ፡ እሺ ፡
አሰኛት ፡ ዓሥር ፡ ልጆች ፡ ስትወልጂ ፡ አንድ ፡
ጊዜ ፡ አትወልጂምን ፡ በመት ፡ በመት ፡ ለምን፡
ትወልጃለሽ ፡ በላት ።
፵፯ በመት ፡ በመቱ ፡ ትወልዳለች ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡
ጊዜ ፡ መውለድ ፡ አትችልምና ፡ ዓሥሩን ፡ ልጆ
ቿን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ትሰጥ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንግ
ዲህ ፡ ጠይቃት ።
፵፰ የወላድ ፡ ማኅፀንም ፡ ዓሥሩን ፡ ልጆቿን ፡ ፈጽማ ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ ማስገኘት ፡ እንዳትችል ፡ ያረጀች ፡
የሆነች ፡ ይህችም ፡ ዓለም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ማስ
ገኘት ፡ አይቻላትም ፡ እኔም ፡ እንደዚሁ ፡ የፈጠ
ርሁትን ፡ ይህንን ፡ ዓለም ፡ በየጊዜው ፡ አዘጋ
ጀሁት ፡ አለኝ ።
፵፱ በፊትህ ፡ በምናገር ፡ ግንዛብ ፡ ምክንያት ፡ ሰጥ
ተኸናልና ፡ እነሆ ፡ በውነት ፡ አንተ ፡ ቆንጆ ፡
የነበረች ፡ እናታችሁ ፡ ይህች ፡ ዓለም ፡ ዛሬ ፡
ፈጽማ ፡ አረጀች ፡ አልከኝ ፡ ኃይላችን ፡ እንደ ፡
ቀደሙት ፡ ሰዎች ፡ ያልሆነልን ፡ ለምንድን ፡
ነው ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።
፶ መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ልጅ ፡ የወለደች ፡
ሴትን ፡ ጠይቃት ፡ ትነግርሃለች ።
፶፩ በኃይል ፡ ይደክማሉ ፡ እንጂ ፡ ዛሬ ፡ የወለድሻ
ቸው ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ወለድሻቸው ፡ ለምን ፡
አልሆኑም ፡ በላት ።
፶፪ በቆንጆና ፡ የተወለደ ፡ ልጅ ፡ ልዩ ፡ ኃይል ፡ ነው ፡
በርጅና ፡ የተወለደው ፡ ልዩ ፡ ደካማ ፡ ነው ፡
ትልሃለች ።
፶፫ እንዲህ ፡ ትለኛለህ ፡ እንጂ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከቀደ
ሙት ፡ ሰዎች ፡ እናንተ ፡ በኃይል ፡ እንድታንሱ ፡
አንተም ፡ ታውቀዋለህ ።
፶፬ ከናንተም ፡ በኋላ ፡ የሚወለዱ ፡ ሰዎች ፡ በኃ
ይል ፡ እንዲያንሱ ፡ ታውቀዋለህ ፡ እንደዚሁ ፡
ቀድሞ ፡ ተፈጥሮ ፡ የነበረ ፡ የሚኖር ፡ ይህም ፡
ዓለም ፡ የሕፃንነቱ ፡ ዘመን ፡ ከለፈ ፡ ወዲያ ፡ እን
ዲደክም ፡ ኋላም ፡ የተፈጠረው ፡ ኃይሉ ፡ ይደ
ክማል ፡ አለኝ ።
፶፭ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ እሺ ፡ በለኝ ፡ በፊትህ ፡ ባለሟ
ልነትን ፡ ካገኘሁ ፡ ለኔ ፡ ለባርያህ ፡ ንገረኝ ፡ ይህን ፡
ዓለም ፡ በማን ፡ አድረህ ፡ ትጐበኘዋለህ ፡ አል
ሁት ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

፩ መጀመሪያ ፡ በነቢያት ፡ አድሬ ፡ ኋላ ፡ እኔ ፡ ሰው ፡
ሁኜ ፡ ሥጋ ፡ ለብሼ ፡ አስተምራለሁ ፡ አለኝ ፡
ምድርና ፡ ሰማይ ፡ ሳይፈጠሩ ፡ መንደር ፡ መንድ
ረው ፡ የሚኖሩትም ፡ ሳይፈጠሩ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡
ሥራም ፡ ሳይፀና ፡ የነፋሳት ፡ አካልም ፡ ሳይፈ
ጠሩ ።
፪ የነጐድጓድ ፡ ድምፅም ፡ ሳይሰማ ፡ የፀሐይ ፡ ብር
ሃንም ፡ ሳይፈጠር ፡ የገነትም ፡ ምድር ፡ ሳይፈ
ጠር ።
ያበባውም ፡ ደም ፡ ግብት ፡ ሳይታይ ፡ የጠፈር ፡ ፫
ኃይልም ፡ ሳይፀና ፡ ነገደ ፡ መላእክትም ፡ ሳይ
ቈጠሩ ።
የሰማይም ፡ ምጥቀቱ ፡ ሳይታይ ፡ ሰበቱ ፡ ሰማይ ፬
ትም ፡ ሳይቈጠሩ ።
የሚመጣው ፡ ዓለም ፡ የመንግሥት ፡ ሰማይ ፡ ፭
ምሥጢር ፡ ሳይታወቅ ፡ ሃይማኖትን ፡ የሚያፀ
ኑት ፡ ሰዎች ፡ በልብ ፡ ሥላሴ ፡ ሳይቈጠሩ ።
የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፍጡር ፡ ያይደለሁ ፡ እኔ ፡ ይህን ፡ ፮
ዓለም ፡ እጐበኝ ፡ ዘንድ ፡ አስቤአለሁና ፡ ቀድሞ ፡
በነቢያት ፡ አድሬ ፡ ኋላ ፡ እኔ ፡ ሰው ፡ ሁኜ ፡ ሥጋ ፡
ለብሼ ፡ አስተምራለሁ ፡ አለኝ ።
ምልክቱም ፡ ምንድነው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ጊዜው ፡ ፯
መጨረሻው ፡ መቼ ፡ ነው ፡ የሁለተኛው ፡ ዓለም ፡
መንግሥት ፡ ሰማይስ ፡ የሚሰጥበት ፡ ጊዜው ፡
መቼ ፡ ነው ፡ ብየ ፡ ጠየቅሁት ።
አብርሃም ፡ ይስሐቅን ፡ ወለደ ፡ ኤሳውና ፡ ያዕ ፰
ቆብ ፡ ከሱ ፡ ተወልደዋልና ።
ያዕቆብ ፡ የሁለተኛው ፡ ዓለም ፡ የመንግሥት ፡ ፱
ሰማይ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።
የሰው ፡ መጨረሻው ፡ እከሉ ፡ ወደታች ፡ እግሩ ፡ ፲
ነውና ፡ ወደ ፡ ላይም ፡ ራሱ ፡ ነውና ፡ ያዕቆብ ፡
የኤሳውን ፡ እግር ፡ ይዞ ፡ ሲወለድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡
እንደሆነ ፡ በመካከሉ ፡ ሌላ ፡ እንደሌለ ፡ መንግ
ሥት ፡ ሰማያት ፡ ስትሰጥ ፡ ይህች ፡ ዓለም ፡
ስታልፍ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።
ነገር ፡ ግን ፡ ዕዝራ ፡ አትመርምር ፡ አለኝ ፡ መለ ፲፩
ስሁለት ፡ እንዲህ ፡ አልሁት ፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡
በፊትህ ፡ ባለሟልነትንስ ፡ ካገኘሁ ።
በቀኝ ፡ እኩል ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሁኜ ፡ ሳለሁ ፡ ባለ ፲፪
ፈው ፡ ሌሊት ፡ አስቀድሞ ፡ የነገርኸኝን ፡ የዚህ ፡
የምልክቱን ፡ መጨረሻ ፡ ለኔ ፡ ለባርያህ ፡ ንገ
ረኝ ፡ ብዬ ፡ መለስሁለት ።
መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ተነሥተህ ፡ በእግ ፲፫
ርህ ፡ ቁም ፡ ጩኸት ፡ የተመላበትን ፡ ቃል ፡
እነግርሃለሁ ።
መነዋወጥ ፡ አንተ ፡ የቆምህበት ፡ ቦታ ፡ ቢነዋ ፲፬
ወፅ ፡ መነዋወፁ ፡ የኋልፈት ፡ ምልክት ፡ ነውና ፡
በነገርሁህ ፡ ጊዜ ፡ አትደንግጥ ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ የምድር ፡ መሠረቶች ፡ የኋልፈትን ፡ ፲፭
ምልክት ፡ ያስረዳሉ ።
መነዋወጡ ፡ ስለነሳቸው ፡ ነውና ፡ ይንቀጠቀ ፲፮
ጣሉ ፡ ይነዋወጣሉ ፡ በመጨረሻቸው ፡ ያልፉ ፡
ዘንድ ፡ አላቸውና ፡ ይነዋወፃሉ ፡ አለኝ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቼ ፡ ፲፯
በእግሮቼ ፡ ቆምኩ ፡ የሚናገረውን ፡ ቃል ፡ እነሆ ፡
ሰማሁ ፡ ድምፁም ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውሃ ፡ ድምፅ ፡
ነው ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይጎ ፲፰
በኛቸው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡
የሚጎበኝበት ፡ ዘመን ፡ እነሆ ፡ ይመጣል ፡ ይላል ።
ኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊት ፡ በምትታነፅበት ፡ ጊዜ ፡ ፲፱

የበደሉኝን፡ሰዎች፡ኃጢአታቸውን፡እመረም
ራቸው ፡ ዘንድ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አለኝ ።
፳ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ መንግሥት ፡ ሰማይ ፡
በተሰጠ ፡ ጊዜ ፡ የማደርገው ፡ ምልክት ፡ ይህ ፡
ነው ፡ በሰማይ ፡ ብሉያት ፡ ሐዲሳት ፡ ይነበባሉ ፡
መልኩንም ፡ ሁሉ ፡ ያየኛል ።
፳፩ ተወልደው ፡ ዓመት ፡ የሆናቸው ፡ ሕፃናት ፡ ፈጽ
መው ፡ ይናገራሉ ፡ ከፀነሱ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ አንድ ፡
ወር ፡ ሲሆናቸው ፡ የሞቱ ፡ ሴቶች ፡ ከልጆቻ
ቸው ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ ይነሣሉ ።
፳፪ የማትታይ ፡ መንግሥት ፡ ሰማይ ፡ ጻድቃን ፡
ወርሰዋት ፡ ተዘርተውባት ፡ ትታያለች ፡ በጥ
ንት ፡ በኸርማት ፡ የተመሉ ፡ መቃብራት ፡ በዷ
ቸውን ፡ ይቀራሉ ።
፳፫ ረቂቅ ፡ ነጋሪት ፡ ይሰማል ፡ የሰማውም ፡ ሁሉ ፡
ይደነግጣል ።
፳፬ በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ወዳጆች ፡ ከወዳጆቻቸው ፡
ጋራ ፡ እስበሳቸው ፡ እንደ ፡ ጠላት ፡ ይጣላሉ ።
ምድርም ፡ በውስጧ ፡ የሚኖሩባትን ፡ ሰዎች ፡
ታስደነግጣቸዋለች ፡ የውሀው ፡ ፈሳሾችም ፡
ይገታሉ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ አይፈ
ሱም ።
፳፭ ከዚህ ፡ ከነገርሁህ ፡ ሁሉ ፡ የቀረ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
የሚድን ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ትድግናየን ፡ የዘመኔንም ፡
ፍጻሜ ፡ የሚያይ ፡ እሱ ፡ ነው ።
፳፮ ወደ ፡ ገነት ፡ የወጡ ፡ ከተወለዱም ፡ ጀምሮ ፡
ሞትን ፡ ያልቀመሱ ፡ እነዚህን ፡ ሄኖክንና ፡ ኤል
ያስን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ያይዋቸዋል ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎችም ፡ ልቡና ፡ በውቀት ፡ ይለወ
ጣል ፡ አዋቂ ፡ ልቡናም ፡ ይሰጣቸዋል ።
፳፯ ክፋት ፡ ትጠፋለችና ፡ ተንኮልም ፡ ትጠፋለችና ።
፳፰ ሃይማኖት ፡ ትጸናለች ፡ ሞት ፡ ድል ፡ ይነሣል ፡
ዋጋ ፡ ሳታሰጥ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ የነበረች ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ዋጋ ፡ በማሰጠት ፡ ትገለጣ
ለች ።
፳፱ በተናገረኝም ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ እያለ ፡
እኔ ፡ የቆምሁበት ፡ በታ ፡ ይነዋወጣል ።
፴ በለፈችው ፡ ሌሊት ፡ እነግርህ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡
መጣሁ ፡ ይህን ፡ ምልክት ፡ እነግርህ ፡ ዘንድ ፡
መጣሁ ፡ አለኝ ።
፴፩ ዳግመኛ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ የጾምህ ፡ የጸለይክ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ልመናህ ፡
ተሰምቷልና ።
፴፪ ከሕፃንነትህ ፡ ጀምሮ ፡ የሠራኸው ፡ የውነተኛ
ነትህ ፡ ሥራ ፡ ተገልጧልና ፡ ከዚህ ፡ ከነገርኩህ ፡
ነገር ፡ የሚበልጥ ፡ ዳግመኛ ፡ እነግርሃለሁ ።
፴፫ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እነግርህ ፡ ዘንድ ፡
እግዚአብሔር ፡ ላከኝ ።
፴፬ እመን ፡ አትፍራ ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ እንዳትጠራ
ጠር ፡ ስለቀደመው ፡ ስለክፉውም ፡ አሳብህ ፡
አትቸኩል ፡ አለኝ ።
፴፭ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የነገረኝ ፡ ሦስቱን ፡ ሱባዔ ፡ እጨ
ርስ ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ እያለቀስኩ ፡
ጾምኩ ።

ሰውነቱ ፡ ፈጽማ ፡ ትናደዳለችና ፡ ልቡናየም ፡ ፴፮
ትነዋወጣለችና ።
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እናገር ፡ ጀመርሁ ። ፴፯
አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ በመጀመሪያው ፡ መፍጠርህ ፡ ፴፰
በመጀመሪያይቱ ፡ ቀን ፡ ምድርና ፡ ሰማይ ፡
ይፈጠር ፡ አልክ ፡ እንዳልክ ፡ ተፈጥሬአለሁ ፡
ቃልህም ፡ ፍጥረትን ፡ ይፈጥር ፡ ነበር ።
የአራዊት ፡ የእንስሳ ፡ ድምፅ ፡ የለም ፡ ነበርና ፡ ፴፱
ዳግመኛ ፡ የሰው ፡ ድምፅ ፡ አልነበረምና ፡ ነፋሱ ፡
በውሀው ፡ ላይ ፡ ይዋኝ ፡ ነበር ፡ ጨለማም ፡ በዓ
ለሙ ፡ የተመላ ፡ ነበር ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ነበር ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ ብርሃን ፡ ከበሕርይህ ፡ ይገኝ ፡ አልህ ፡ ፵
ፍጥረትህም ፡ ይገለጥ ፡ አልህ ።
ዳግመኛም ፡ በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ በሰማይ ፡ ያለ ፡ ፵፩
ነፋስን ፡ ፈጠርክ ፡ እኩሌታው ፡ ወደላይ ፡ ይወጣ ፡
ዘንድ ፡ እኩሌታውም ፡ በታች ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡
በውሀው ፡ መካከል ፡ ወሰን ፡ ይለይ ፡ ዘንድ ፡ አዘ
ዝከው ።
በሦስተኛይቱ ፡ ቀን ፡ ውሀውን ፡ በሰባተኛይቱ ፡ ፵፪
ዕጣ ፡ በምድር ፡ ይወሰን ፡ ዘንድ ፡ አዘዝከው ፡
ያርሱ ፡ ዘንድ ፡ ዘርም ፡ ይዘሩ ፡ ዘንድ ፡ በፊትህም ፡
ፀንተው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ የምድር ፡ ስድስተኛ
ይቱ ፡ ዕጣ ፡ ደረቅ ፡ ሁኖ ፡ ይቅር ፡ አልህ ።
ቃልህም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ፍጥረት ፡ ይፈጠር ፡ ፵፫
ነበር ።
የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ መዓ ፵፬
ዛው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ያበበውም ፡
መልኩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነው ፡ ሁሉ ፡ የእንጨቱ ፡
መልኩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ መዓዛውም ፡
ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ተፈጠረ ።
በራተኛይቱ ፡ ቀን ፡ ሊያበሩ ፡ የጨረቃና ፡ የፀ ፵፭
ሐይ ፡ ብርሃን ፡ ይፈጠር ፡ ዘንድ ፡ የከዋክብትም ፡
ብርሃን ፡ ይፈጠር ፡ ዘንድ ፡ አዘዝህ ።
ይፈጠር ፡ ዘንድ ፡ ነቢይ ፡ አዳምን ፡ ያገለግሉ ፡ ፵፮
ዘንድ ፡ አዘዝሃቸው ።
በምስተኛይቱም ፡ ቀን ፡ የናኄብ ፡ ውሃ ፡ ያለበ ፵፯
ትን ፡ ይኸን ፡ ሰባተኛውን ፡ እጅ ፡ ደመ ፡ ነፍስ ፡
ደኅነኛ ፡ የሚሆኑ ፡ ዓሣዎቹንና ፡ ወፎችን ፡ ያስ
ገኝ ፡ ዘንድ ፡ አዘዝከው ።
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ጌትነትህን ፡ ፵፰
ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ የማይናገር ፡ ደመ ፡ ነፍስ ፡ የሌ
ለው ፡ ያ ፡ ውሀ ፡ ደመ ፡ ነፍስ ፡ ያለውን ፡ አስገኘ ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ የፈጠርሃቸው ፡ ሁለቱን ፡ እንስሳት ፡ ፵፱
አኖርክ ፡ ያንዱን ፡ ስሙን ፡ ብሔሞት ፡ አልከው ፡
የሁለተኛውንም ፡ ስሙን ፡ ሌዋታን ፡ አልከው ።
የናኄብ ፡ ውሀ ፡ ያለበት ፡ ይህ ፡ ሰባተኛው ፡ እጅ ፡ ፶
ብሔሞትና ፡ ሌዋታንን ፡ መወሰን ፡ አይችል
ምና ፡ ብሔሞትና ፡ ሌዋታንን ፡ ለየብቻቸው ፡
ለየሃቸው ።
አራቱ ፡ ተራሮች ፡ ባሉበት ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ እሱ ፡ ፶፩
በውስጡ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ለብሔሞት ፡ ከስድ
ስተኛው ፡ እጅ ፡ አንዱን ፡ እጅ ፡ የብስን ፡ ሰጠ
ኸው ።
ሰባተኛዋንም ፡ እጅ ፡ በሕሩን ፡ ለሌዋታን ፡ ሰጠ ፶፪

ኸው ፡ ለምትወዳቸው ፡ ለጻድቃን ፡ ምግብ ፡
ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ሌዋታንና ፡ ብሔሞትን ፡ ጠበቅ
ሃቸው ።
፶፫፡ በስድስተኛይቱም ፡ ቀን ፡ በሬትህ ፡ እንስሳን ፡
የሰማይ ፡ ወፎችንና ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አውሬዎ
ችን ፡ ታስገኝ ፡ ዘንድ ፡ ምድርን ፡ አዘዝኻት ።
፶፬፡ በዚህም ፡ በፍጥረትህ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አዳምን ፡
ሾምከው ፡ አስቀድመህ ፡ በፈጠርከው ፡ ፍጥ
ረት ፡ ሁሉ ፡ ሹም ፡ ሆኖ ፡ ገዛ ፡ ስለሱ ፡ የመረጥ
ከን ፡ እኛ ፡ ወገኖችህ ፡ በመከራ ፡ ባሕር ፡ እንሰ
ጥማለን ።
፶፭፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ለናንተ ፡ ፈጠርኩት ፡ ብለሃልና ፡
አቤቱ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ በሬትህ ፡ ተናገርሁ ።
፶፮፡ ከአዳም ፡ የተወለዱ ፡ ሌሎች ፡ አሕዛብ ፡ ግን ፡
እንደ ፡ ኢምንት ፡ ናቸው ፡ ምራቅም ፡ እንዲ
ናቅ ፡ እንደዚያ ፡ የተናቁ ፡ ናቸው ፡ በእፍሳት ፡
ላይ ፡ የወደቀ ፡ ጠብታ ፡ እንዲናቅ ፡ የተናቁ ፡
ናቸው ፡ ተድላ ፡ ደስታቸውም ፡ እንደ ፡ ኢም
ንት ፡ ነው ፡ አለህ ።
፶፯፡ አሁንም ፡ እነሆ ፡ እንደ ፡ ኢምንት ፡ ናቸው ፡ ያል
ካቸው ፡ እነዚያ ፡ አሕዛብ ፡ እነሆ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡
ሠለጠኑ ፡ አጠፉን ።
፶፰፡ የምወደው ፡ መጀመሪያ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ የሞተ
ልን ፡ እኛ ፡ ወገኖችህ ፡ ግን ፡ በአሕዛብ ፡ እጅ ፡
ተማረክን ።
፶፱፡ ነገር ፡ ግን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ስለኛ ፡ ከፈ
ጠርኸው ፡ ዓለማችን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡
ለምን ፡ አንወርስም ፡ ይህስ ፡ አለመውረሳችን ፡
እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ተናግሬ ፡ በጨረ
ስሁ ፡ ጊዜ ፡ ባለፈችው ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ አስ
ቀድሞ ፡ ወደኔ ፡ የመጣ ፡ ያ ፡ መልአክ ፡ ወደኔ ፡
ተላከ ።
፪፡ ዕዝራ ፡ ተነሥተህ ፡ እነግርህ ፡ ዘንድ ፡ ወዳንተ ፡
የመጣሁ ፡ የኔን ፡ ቃል ፡ ስማ ፡ አለኝ ።
፫፡ ጌታዬ ፡ በል ፡ ንገረኝ ፡ አልሁት ፡ ውስጧ ፡ እጅግ ፡
ሰፊ ፡ የሆነ ፡ አገር ፡ አለች ፡ አለኝ ፡ ያችም ፡ አገር ፡
ፈጽማ ፡ ሰፊ ፡ ናት ።
፬፡ የመግቢያዋም ፡ መንገድ ፡ ጠባብ ፡ ነው ፡ እንደ ፡
መስኖ ፡ ውሀ ፡ በይም ፡ ነው ።
፭፡ ያያት ፡ ያገኛት ፡ ዘንድ ፡ ወደዚያች ፡ አገር ፡ ሊገባ ፡
የወደደ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ይህንን ፡ ጠባቡን ፡ መግ
ቢያዋን ፡ ካላለፈ ፡ ወደ ፡ አደባባይዋ ፡ መግባት ፡
እንደምን ፡ ይችላል ።
፮፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የተሠራች ፡ ከበረከቱ ፡ ሁሉ ፡
የተመላች ፡ ሌላም ፡ አገር ፡ አለች ።
፯፡ የመግቢያዋም ፡ መንገድ ፡ ጠባብ ፡ ነው ፡ ያችም ፡
ወደ ፡ ገደል ፡ የምትወስድ ፡ ናት ፡ በቀኟ ፡ እሳት ፡
በግራዋ ፡ ጥልቅ ፡ ውሀ ፡ አለ ።
፰፡ አንዲቱ ፡ መንገዷ ፡ በውሀና ፡ በእሳት ፡ መካከል ፡
ናት ፡ ጎዳናዋም ፡ ካንድ ፡ ሰው ፡ እግር ፡ ጫማ ፡
በቀር ፡ አትችልም ።
፱፡ ይህችን ፡ አገር ፡ ይወርሳት ፡ ዘንድ ፡ የተሰጠ
ችው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ጠባቡን ፡ መንገድ ፡ ካላ
ለፈ ፡ ርስቱን ፡ እንደምን ፡ ይወርሳል ፡ አለኝ ።
፲፡ አቤቱ ፡ አሁን ፡ እንደተናገርከው ፡ ነው ፡ አል
ሁት ።
፲፩፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ስለነሳቸው ፡ ፈጥሬዋለ
ሁና ፡ የእስራኤል ፡ አገራቸው ፡ እድል ፡ ፈንታ
ቸውም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፡ አለኝ ።
፲፪፡ አዳም ፡ ትእዛዜን ፡ በፈረሰ ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡
ጎዳናው ፡ ጉድጓድ ፡ ነው ፡ ጠባብ ፡ ያነሰ ፡ የከፋ ፡
መከራው ፡ የበዛ ፡ ፃር ፡ ጋር ፡ የተመላ ፡ ሆነ ።
፲፫፡ የዚያ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማይስ ፡ ጎዳናው ፡ ቃላቅ ፡
ነው ፡ ሰፊ ፡ ነው ፡ የበራ ፡ ነው ፡ ሞት ፡ የሌለበት ፡
የሕይወት ፡ ፍሬንም ፡ ያፈራል ።
፲፬፡ ደጎነኞች ፡ የምትሆኑ ፡ እናንተ ፡ ያን ፡ ጉድጓድ ፡
ያን ፡ ኃጢአት ፡ ካላለፋችሁት ፡ የተዘጋጀላችሁ ፡
መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ መውረስ ፡ አትችሉም ።
፲፭፡ አሁንስ ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ የምትሆን ፡ አንተ ፡
ለምን ፡ ትታወከለህ ፡ ሟች ፡ የምትሆን ፡ አንተ ፡
ለምን ፡ እንደ ፡ ተልባ ፡ ትፈናጠራለህ ።
፲፮፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለውን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚመ
ጣውን ፡ ዓለም ፡ በልቡናህ ፡ ለምን ፡ አታስብም ፡
አለኝ ።
፲፯፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ እነሆ ፡ ጻድቃን ፡ ይህን ፡ መን
ግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ እንዲወርሱት ፡ ኃጥአን ፡
ግን ፡ እንዲጠፉ ፡ አንተ ፡ በሕግህ ፡ ለአሪት ፡ ተና
ገርህ ፡ አልሁት ።
፲፰፡ ያማሩ ፡ የተወደዱ ፡ ጻድቃን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማ
ይን ፡ ተስፋ ፡ እያደረጉ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ መከራ ፡
ይታገሡታልና ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይወ
ርሳሉ ፡ ኃጥአን ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ተድላ ፡
ደስታ ፡ ይታመኑታልና ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያ
ትን ፡ አይወርሱም ፡ አልሁት ።
፲፱፡ ካንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አንተ ፡ በፍርድ ፡ የም
ትሻል ፡ አይደለም ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ አንተ ፡
የምትራቀቅ ፡ አይደለህም ።
፳፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩትን ፡ ሕጉን ፡ ሠርተው ፡
በሕይወት ፡ እንዲድኑ ።
፳፩፡ እግዚአብሔር ፡ አዟቸዋልና ፡ እግዚአብሔር ፡
የሠራው ፡ ሕጉን ፡ የናቁ ፡ እኒህ ፡ ኃጥአን ፡ ይጥፉ ፡
ሕጉን ፡ ግን ፡ ቢጠብቁ ፡ ባልተፈረደባቸውም ፡
ነበር ።
፳፪፡ እግዚአብሔርንም ፡ ክዱት ፡ በአምልኮትም ፡
ተጠቂ ፡ ክፉ ፡ አሳብንም ፡ አሰቡ ።
፳፫፡ ክደትን ፡ በደልንም ፡ ገንዘብ ፡ አደረጉ ፡ ከዚህም ፡
ሁሉ ፡ ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ እግዚአብሔር ፡
የለም ፡ አሉ ፡ ሕጉንም ፡ ተጠ ።
፳፬፡ ሕጉንም ፡ ካዱ ፡ መሐላውንም ፡ ቸል ፡ አሉ ፡
በሕጉም ፡ አልታመኑም ፡ ሥራውንም ፡ ናቁ ፡
አምልኮቱንም ፡ አላሰቡ ።
፳፭፡ አምልኮቱን ፡ ስለ ፡ አላሰቡ ፡ ከተድላ ፡ ከደስታ ፡
ባዶ ፡ የሆነ ፡ ገሃነም ፡ ከምግባር ፡ ከሃይማኖት ፡
ባዶ ፡ ለሆኑ ፡ ኃጥአን ፡ ነው ፡ ጺጋ ፡ ክብር ፡ የተ
መላ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ግን ፡ ምግባር ፡ ትሩ

ሩት ፡ ለተመሉ ፡ ለጻድቃን ፡ ነው ።
፳፮፡ እኔ ፡ የነገርኩህ ፡ ምልክት ፡ በሚገለጽ ፡ ጊዜ ፡
እነሆ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ወራት ፡ ይመጣልና ፡ ዛሬ ፡
የምትታይ ፡ ዓለም ፡ ታልፋለችና ፡ ዛሬ ፡ የተሠ
ወረች ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ ትገለጻለችና ።
፳፯፡ እኔ ፡ ከነገርኩህ ፡ ከክፉ ፡ ሥራ ፡ የዳነ ፡ ሁሉ ፡
ክብሬን ፡ የሚያይ ፡ እሱ ፡ ነው ።
፳፰፡ ልጄ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ካሉ ፡ ከጻድቃን ፡
ጋራ ፡ ይገለጣልና ፡ የተነሡ ፡ ጻድቃንን ፡ ደስ ፡
ይላቸዋል ።
፳፱፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጄ ፡ ክርስቶስ ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡
የጀመረውን ፡ አገልግሎት ፡ ይፈጽማል ፡ አእ
ምሮ ፡ ያለው ፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ክብሩን ፡ ይፈጽ
ማል ።
፴፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡
ዝም ፡ ያለውን ፡ ያህል ፡ ወደ ፡ ቀድሞ ፡ አነዋ
ወሩ ፡ ይመለሳል ፡ ያልፋል ፡ የሚቀር ፡ የለም ።
፴፩፡ ከሰባት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ተነሥቶ ፡ የማያውቅ ፡
ምውት ፡ ይነሣል ፡ ሟች ፡ ሰው ፡ ወርሶት ፡ የነ
በረ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ያልፋል ።
፴፪፡ ምድርም ፡ የተቀበሩባትን ፡ ሰዎች ፡ ታስገኛ
ለች ፡ መሬትም ፡ በውስጡ ፡ የተቀበሩትን ፡
ሰዎች ፡ ያስገኛል ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አብያተ ፡ ነፍ
ስም ፡ በውስጣቸው ፡ ያሉ ፡ ነፍሳትን ፡ ይመል
ሳሉ ።
፴፫፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፈጠረው ፡ በዙ
ፋኑ ፡ ይገለጣል ፡ ቸርነቱ ፡ ትደረጋለች ፡ ይቅር ፡
አይልም ፡ አይታገሥም ።
፴፬፡ ቍርጽ ፡ ፍርድ ፡ ብቻ ፡ ይቀራል ፡ የሰው ፡ ምግ
ባሩ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ዋጋ ፡ በማሰጠት ፡ ትጸናለች ።
፴፭፡ ሰውን ፡ ሥራው ፡ ይከተለዋል ፡ ዋጋውም ፡ ይገ
ለጣል ፡ ቅንነትም ፡ ትገለጻለች ፡ ኃጥኡን ፡ ሰው ፡
ኃጢአቱ ፡ እሳት ፡ ሁና ፡ ስትፈጀው ፡ አታንቀላ
ፋም ።
፴፮፡ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ ያለበት ፡ ገሃነም ፡ እሳት ፡ ዕረ
ፍት ፡ በለበት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አንፃር ፡
ይገለጣል ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ባለበት ፡ በመንግ
ሥተ ፡ ሰማይ ፡ አንፃር ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ይገለ
ጣል ።
፴፯፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተነሡ ፡ አሕዛብን ፡
እነሆ ፡ እዩ ፡ የካዳችሁትም ፡ ማንም ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ እወቁ ፡ ያልተገዛችሁለትስ ፡ ለማነው ፡ የና
ቃችሁትስ ፡ የማንን ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ።
፴፰፡ በቀኝ ፡ ያለውን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ መንግሥተ ፡
ሰማያት ፡ በግራ ፡ ያለውን ፡ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ ገሃ
ነመ ፡ እሳት ፡ እነሆ ፡ በፊታችሁ ፡ እዩ ፡ አላቸው ።
፴፱፡ እግዚአብሔር ፡ በቍርጽ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ አሕዛ
ብን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ የቍርጽ ፡ ፍርድ ፡ ቀንስ ፡
እንዲህ ፡ ናት ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ የሰማይ ፡ ከዋ
ክብትም ፡ የሉም ።
፵፡ ደመናም ፡ ነጐድጓድና ፡ መብረቅም ፡ ውሀና ፡
ነፋስም ፡ ሰማይም ፡ ጨለማም ፡ መዓልትና ፡
ሌሊት ፡ የለባትም ።
፵፩፡ ክረምት ፡ በጋ ፡ መከርና ፡ ውርጭ ፡ ቀቅ ፡ ጥቅል ፡
ነፋስ ፡ በረድ ፡ ውርጭ ፡ ፍም ፡ ዝናም ፡ ጠል ፡
የለባትም ።
ጢትና ፡ ማታ ፡ ብልጭልጭታና ፡ ብርሃን ፡ ፵፪፡
ፋናና ፡ ብርሃን ፡ እሱን ፡ ደጅ ፡ የሚጠና ፡ ሰው ፡
ሁሉ ፡ በሱ ፡ ብርሃንን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአ
ብሔር ፡ ከጌትነቱ ፡ ብርሃን ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡
ሁሉ ፡ የለም ።
የዚያች ፡ ሰዓት ፡ ብዛቷ ፡ እንደ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ፵፫፡
ትሆናለች ።
በኃጥኡ ፡ የሚፈረድበት ፡ ለጻድቁ ፡ የሚፈረድ ፵፬፡
ለት ፡ ፍርድ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ላንተ ፡ ብቻ ፡ ይህን ፡
ነገርኩ ።
አሁንም ፡ አቤቱ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ፵፭፡
ትእዛዝህንም ፡ የጠበቁ ፡ ሰዎች ፡ ንዑዳን ፡ ክቡ
ራን ፡ ናቸው ፡ ብዬ ፡ መለስሁለት ።
ነገር ፡ ግን ፡ ስለጠየቅሁህ ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ፵፮፡
ካሉ ፡ ሰዎች ፡ የማይበድል ፡ ማነው ፡ ከሴቶች ፡
ከተወለደስ ፡ ወገን ፡ ሕግህን ፡ ያላፈረሰ ፡ ማነው ።
አሁንም ፡ በሚመጣው ፡ ዓለም ፡ በመንግሥተ ፡ ፵፯፡
ሰማያት ፡ ደስ ፡ ታሰኛቸው ፡ ዘንድ ፡ ያለህ ፡ ጻድ
ቃን ፡ ጥቂት ፡ እንደሆኑ ፡ የሚፈረድባቸው ፡
ኃጥአንም ፡ ሁሉ ፡ ብዙዎች ፡ እንደሆኑ ፡ አያ
ለሁ ።
ከዚህ ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ያሳተን ፡ ለመቃ ፵፰፡
ብር ፡ ወደሚያበቃ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ የመራን ፡ ወደ ፡
ሞት ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ጐዳና ፡ የወሰደን ፡ ከዛሬ ፡
ጀምሮ ፡ ከኛ ፡ ሕይወትን ፡ ያራቃት ፡ ፈታዊ ፡
ልቡና ፡ በኛ ፡ ፀንቷልና ፡ የሚፈረድባቸው ፡
ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፡ ይህ ፡ ሞት ፡ ከአዳም ፡
በተወለደ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በጻድ
ቃን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ አልሁት ።
መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ስማኝ ፡ ልንገርህ ፡ ፵፱፡
ዳግመኛ ፡ ላስተምርህ ።
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁለት ፡ ዓለምን ፡ ፶፡
ፈጠረ ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ዓለምን ፡ ብቻ ፡ አልፈ
ጠረም ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ።
አንተ ፡ ግን ፡ የጻድቃን ፡ ቍጥራቸው ፡ ጥቂት ፡ ፶፩፡
ነው ፡ ብለሃልና ፡ ቍጥራቸውም ፡ ብዙ ፡ አይደ
ለም ፡ ብለሃልና ።
እርሳሱን ፡ ከሸክላ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አድርገህ ፡ ፶፪፡
ሥራ ።
አቤቱ ፡ ይህ ፡ እንዴት ፡ ይቻለኛል ፡ አልሁት ። ፶፫፡
የምትጠይቀኝ ፡ ይህን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ምድ ፶፬፡
ርን ፡ ጠይቃት ፡ ትነግርሃለች ፡ ተናገራት ፡ ትመ
ልስልሃለች ።
እነሆ ፡ ወርቅን ፡ ብርንና ፡ ስንን ፡ ብረትንና ፡ ፶፭፡
እርሳስን ፡ ሸክላን ፡ አንቺ ፡ ታስገኛለሽ ፡ በላት ።
ከወርቅ ፡ ብር ፡ ከብር ፡ ናስ ፡ ከናስ ፡ ብረት ፡ ከብ ፶፮፡
ረት ፡ እርሳስ ፡ ከርሳስ ፡ ሸክላ ፡ ይበዛል ፡ ትል
ሃለች ።
እንግዲህ ፡ አንተው ፡ ራስህ ፡ እውቅ ፡ ማን ፡ ይከ ፶፯፡
ብራል ፡ ማን ፡ ይወደዳል ፡ የሚበዛው ፡ ይከብ
ራልን ፡ ይወደዳል ፡ ወይስ ፡ የሚያንሰው ፡ ይከ
ብራል ፡ ይወደዳል ፡ አለኝ ።

፶፰ መለስሁለት ፡ እንዲህ ፡ አልሁት ፡ ጌታዬ ፡ የሚያንሰው ፡ ይከብራል ፡ የሚበዛው ፡ ይዋረዳል ፡ አልሁት ።
፶፱ መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ያሰብከትን ፡ አንተ ፡ ራስህ ፡ መርምራት ፡ ብዙ ፡ ናስ ፡ ብዙ ፡ ብረት ፡ ከለው ፡ ጥቂት ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ ያለው ፡ ደስ ፡ እንዲለው ፡ ከኔ ፡ የሚገኝ ፡ የጻድቃን ፡ ደስታቸው ፡ እንደዚህ ፡ ነው ።
፷ ስሜ ፡ በነሳቸው ፡ ስለ ፡ ተመሰገነ ፡ እነሳቸው ፡ ክብሬን ፡ ይወርሳሉና ፡ ስለሚድኑ ፡ ስለ ፡ ጥቂቶች ፡ ጻድቃን ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።
፷፩ እነሳቸው ፡ ዛሬ ፡ በእሳት ፡ ተመስለዋልና ፡ እንደ ፡ እሳትም ፡ ሆነዋልና ፡ እንደ ፡ ጢስም ፡ ታይተው ፡ ጠፍተዋልና ፡ ስለሚጠፉ ፡ ስለ ፡ ብዙዎች ፡ ኃጥአን ፡ ልቡናዬን ፡ አላሳዝንም ፡ አለኝ ።
፷፪ መለስሁለት ፡ እንዲህ ፡ አልሁት ፡ ምድር ፡ ሆይ ፡ እንዳንቺ ፡ ያለ ፡ ቦዝ ፡ ፍጥረት ፡ አዳም ፡ ከመሬትነትሽ ፡ ለምን ፡ ተገኘ ።
፷፫ ነገር ፡ ግን ፡ ፈታዊ ፡ ልቡና ፡ ተፈጥሮ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ሲኖር ፡ ጥንቱን ፡ ፈታዊ ፡ ልቡና ፡ ባይፈጠርልን ፡ በተሻለን ፡ ነበር ።
፷፬ ሳናውቅ ፡ እንጎዳለንና ፡ ስለሱ ፡ ይፈረድብናል ።
፷፭ የአዳም ፡ ልጆች ፡ ያልቅሱ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ያሉ ፡ አውሬዎች ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፤ ከአዳም ፡ የተወለዱ ፡ ሁሉ ፡ ያልቅሱ ።
፷፮ የሚጠብቃቸው ፡ ቁርጥ ፡ ፍርድ ፡ ስላልኖረ ፡ ገሃነምንም ፡ የማያውቁት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከሞት ፡ በኋላ ፡ መነሣትን ፡ ተስፋ ፡ የማያደርጉ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እነሳቸው ፡ ከኛ ፡ ፈጽመው ፡ ይሻላሉና ፡ የእንስሳ ፡ ወገኖች ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ።
፷፯ የምንነሣው ፡ ትንሣኤ ፡ ምን ፡ ይጠቅመናል ፡ ምን ፡ ይረባናል ።
፷፰ ከአዳም ፡ የተወለድን ፡ ሁሉ ፡ በባሕረ ፡ ኃጢአት ፡ ተሰጠምን ፡ በደልንም ፡ ተመላን ፡ ኃጢአታችንም ፡ በና ።
፷፱ ከሞትን ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ በንሄድ ፡ በተሻለን ፡ ነበር ፡ አልኩት ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩ መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ በፈጠረው ፡ ጊዜ ፡ አዳምንም ፡ በፈጠረው ፡ ጊዜ ፡ ከሱ ፡ የተወለዱትንም ፡ ሁሉ ፡ በፈጠራቸው ፡ ጊዜ ፡ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ ገና ፡ ገሃነምን ፡ አስቀድሞ ፡ አዘጋጀ ።
፪ አሁንም ፡ ፈታዊ ፡ ልቡና ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ በንቶ ፡ ይኖራል ፡ ብለሃልና ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ስለሱ ፡ ይፈረድባቸዋል ፡ ብለሃልና ፡ ከጠየቅኸኝ ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፡ የምመልስልህን ፡ ልብ ፡ አድርግ ።
፫ አእምሮ ፡ ሳላቸው ፡ ይበድላሉና ፡ ሕጉን ፡ በልቡናቸው ፡ አውቀው ፡ ሥራቱን ፡ አልጠበቁምና ፡ ሕጉንም ፡ ተምረው ፡ የተቀበሉት ፡ ሕጉን ፡ ትእዛዙን ፡ አልጠበቁምና ።
፬ እንግዲህ ፡ ቍርጽ ፡ ፍርድ ፡ በሚደረግበት ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ይመልሱ ፡ ዘንድ ፡ አላቸው ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመንስ ፡ ምን ፡ ይናገራሉ ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎችን ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ታገሣቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ስምንት ፡ ሺህ ፡ ይኑር ፡ ብሎ ፡ ስለወሰነው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለነሳቸው ፡ አይደለም ፡ አለኝ ። ፭
መለስሁለት ፡ እንዲህ ፡ አልሁት ፡ በፊትህ ፡ ባለሟልነትን ፡ ካገኘሁ ፡ ለኔ ፡ ለባርያህ ፡ ይህንን ፡ ንገረኝ ፡ በሞትን ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡ ያንዳንዱም ፡ ያንዳንዱም ፡ ነፍሳችን ፡ ከሥጋችን ፡ በምትለይበት ፡ ጊዜ ፡ ቍርጽ ፡ ፍርድንም ፡ በደረግ ፡ ጊዜ ፡ ምጽዓት ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ መላእክት ፡ በተድላ ፡ ይከባከቡናልን ፡ ወይስ ፡ ከዚህ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ይፈረድብናል ፡ ብዬ ፡ ጠየቅሁት ። ፮
መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ይህንን ፡ እነግርሃለሁ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ በዕለተ ፡ ምጽዓት ፡ እስክገለጽልህ ፡ ድረስ ፡ በሠራኸው ፡ ሥራ ፡ በልዑል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ። ፯
የተዘጋጀ ፡ ዋጋ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አለህና ፡ ከተፈረደባቸው ፡ ከመናፍቃን ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አትሆንም ፡ ከሚፈረድባቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ አትቈጠርም ። ፰
የሞትስ ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ከልዑል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የትእዛዝ ፡ ቃል ፡ ከመጣ ፡ በኋላ ፡ እገሌ ፡ ይሙት ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ነፍሱ ፡ ከሥጋው ፡ ትለያለች ፡ ለሥጋ ፡ ሰጪት ፡ ወደነበረ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትመለሳለች ፡ ለልዑል ፡ ጌትነትም ፡ አስቀድማ ፡ ትሰግዳለች ። ፱
የልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ካልጠበቁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ከቃለሉ ፡ አምልኮቱን ፡ ከላሰቡ ፡ ከመናፍቃን ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ ግን ። ፲
እነዚያ ፡ የኃጥአን ፡ ነፍሳት ፡ በአንፃር ፡ ይዞራሉ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ጻድቃን ፡ ማደሪያ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ አይገቡም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መከራ ፡ ይቀበላሉ ፡ ይጨነቃሉ ፡ ያዝናሉ ፡ ሰባቱንም ፡ ሥርዓታት ፡ ያሳያቸዋል ። ፲፩
መጀመሪያይቱ ፡ ሥራት ፡ ይህች ፡ ናት ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ክደዋልና ፡ ሕጉን ፡ ከዳችሁ ፡ ይሏቸዋል ። ፲፪
ሁለተኛይቱም ፡ ሥራት ፡ እንዲህ ፡ ናት ፡ ከሥጋ ፡ ጋራ ፡ ተዋህደው ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ሠርተው ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ መመለስ ፡ አይቻላቸውምና ፡ መመለስ ፡ አትችሉም ፡ ይሏቸዋል ። ፲፫
ሦስተኛይቱም ፡ ሥራት ፡ እንዲህ ፡ ናት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሥራት ፡ ላመኑ ፡ ጻድቃን ፡ የተዘጋጀላቸው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ያዩሉና ፡ እናንተም ፡ ምግባር ፡ ብትሠሩ ፡ ይህን ፡ ትወርሱ ፡ ነበር ፡ ይሏቸዋል ። ፲፬
ዓራተኛይቱም ፡ ሥራት ፡ እንዲህ ፡ ናት ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ የሚጠብቃቸው ፡ ገሃነምን ፡ ያዩሉና ፡ ዛሬም ፡ በሲኦል ፡ መከራ ፡ ትቀበላላችሁ ፡ ኋላም ፡ ገሃነም ፡ ትወርዳላችሁ ፡ ይሏቸዋል ። ፲፭

፲፮፤ አምስተኛይቱም፡ሥራት፡እንዲህ፡ናት፡መላ
እክት፡የጻድቃንን፡ነፍስ፡በገነት፡በብዙ፡
ተድላ፡ደስታ፡ሲከባከቧቸው፡ያያሉና፡እና
ንተም፡ሥራ፡ሠርታችሁ፡ቢሆን፡እንዲህ፡
ይከባከቧችሁ፡ነበር፡ይሏቸዋል ።
፲፯፤ ስድስተኛይቱም፡ሥራት፡እንዲህ፡ናት፡ከዛሬ፡
ጀምሮ፡የሚያገኛቸውን፡መከራ፡እያዘሩ፡ያሳ
ዩዋቸዋልና፡ዛሬም፡መከራ፡ትቀበላላችሁ፡
ኋላም፡ገሃነመ፡እሳት፡ትወርዳላችሁ፡ይሏቸ
ዋል ።
፲፰፤ ከነገርሁህ፡ሁሉ፡ከስድስቱ፡ሥርዓታት፡የም
ትበልጥ፡ሰባተኛይቱ፡ሥርዓት፡እንዲህ፡ናት፡
በፊቱ፡ይፈረድባቸው፡ዘንድ፡ያላቸው፡ዛሬ፡
በሕይወታቸው፡ሳሉ፡እሱን፡የበደሉ፡ኃጥ
አን፡በፊታቸው፡የልዑልን፡ጌትነት፡በዩ፡
ጊዜ፡በኃሣረ፡ነፍስና፡በኃፍረተ፡ነፍስ፡ተይ
ዘው፡እንደ፡ሰም፡ይቀልጣሉ፡እንደ፡ቅጠል፡
ይጠወልጋሉ፡እንደ፡ቅጠል፡ጠወለጋችሁ፡
ይሏቸዋል ።
፲፱፤ የልዑል፡የእግዚአብሔርን፡ሕግ፡የጠበቁ፡የጻ
ድቃን፡ሥራታቸው፡ግን፡እንዲህ፡ናት፡ፈራሽ፡
ከሚሆን፡ሥጋቸው፡ይለዩ፡ዘንድ፡ባላቸው፡
ጊዜ ።
፳፤ በዚህ፡ዓለም፡በኖረበት፡ዘመን፡ሁሉ፡ያስተ
ማራቸው፡የልዑልን፡ሕግ፡ይፈጽሙ፡ዘንድ፡
መከራቸውን፡ታግሠው፡ሁልጊዜ፡በድካም፡
ለእግዚአብሔር፡ተገዝተውለታልና ።
፳፩፤ ስለዚህ፡ነገር፡የጻድቃን፡ነገራቸው፡እንዲህ፡
ነው ።
፳፪፤ መጀመሪያው፡የሚቀበላቸው፡የእግዚአብ
ሔር፡ጌትነቱን፡በብዙ፡ተድላ፡ደስታ፡ያያሉ፡
ሰባቱን፡ሥርዓታት፡ወደ፡ማሰየት፡ይወስዷ
ቸዋል ።
፳፫፤ መጀመሪያይቱ፡ሥራት፡እንዲህ፡ናት፡ዛሬ፡
በሕይወታቸው፡ሳሉ፡በኃጢአታቸው፡እንዳ
ያስታቸው፡በነሳቸው፡ያለ፡ፈታዊ፡ልቡናን፡
ድል፡ይነሱ፡ዘንድ፡በብዙ፡ድካም፡ተጋድለ
ዋልና፡በብዙ፡ድካም፡ተጋደላችሁ፡ይሏቸ
ዋል ።
፳፬፤ ሁለተኛይቱም፡ሥራት፡እንዲህ፡ናት፡የሚ
ዘሩ፡የኃጥአንን፡ነፍሳት፡በሲኦል፡ያይዋቸዋ
ልና፡የሚጠብቃቸው፡ገሃነምንም፡ያያሉና፡
እናንተም፡ምግባር፡ብትሠሩ፡ዛሬም፡በሲኦል፡
ኋላም፡በገሃነም፡መከራ፡ትቀበሉ፡ነበር፡ይሏ
ቸዋል ።
፳፭፤ ሦስተኛይቱም፡ሥራት፡እንዲህ፡ናት፡በሕይ
ወት፡ሳሉ፡አምነው፡የተቀበሉት፡ሕጉን፡
እንደ፡ጠበቁ፡የፈጠራቸው፡እግዚአብሔር፡
ምስክር፡ይሆናቸዋልና፡ምስክር፡ይሆናች
ኋል፡ይሏቸዋል ።
፳፮፤ አራተኛይቱም፡ሥራት፡እንዲህ፡ናት፡መላ
እክት፡በብዙ፡ተድላ፡ደስታ፡እየተከባከቧ
ቸው፡በአብያተ፡ነፍስ፡በገነት፡ከዛሬ፡ጀምሮ፡
የሚያገኙትን፡ተድላ፡ደስታ፡ያያሉና፡ኋላም፡
የሚቆያቸውን፡ክብር፡ያያሉና፡ዛሬም፡በገ
ነት፡ትኖራላችሁ፡ኋላም፡መንግሥተ፡ሰማያ
ትን፡ትወርሳላችሁ፡ይሏቸዋል ።
አምስተኛይቱም፡ሥራት፡እንዲህ፡ናት፡ዛሬ፡ ፳፯፤
ያለ፡ሞትን፡ድል፡እንደነሱት፡ኋላ፡ያገኙት፡
ዘንድ፡ያላቸው፡መንግሥተ፡ሰማይንም፡እንደ፡
ወረሱ፡አይተው፡ደስ፡ይላቸዋልና፡ዳግመ
ኛም፡ድካም፡የተመላ፡ይህን፡ዓለም፡እንደ፡
ናቁት፡ያንን፡መንግሥተ፡ሰማይንም፡እንዲ
ያገኙት፡ሞት፡በሌለበት፡መንግሥተ፡ሰማያ
ትም፡ደስ፡እንዲላቸው፡ያያሉና፡ሞትን፡
ድል፡ነሳችሁት፡ይሏቸዋል ።
ስድስተኛይቱም፡ሥርዓት፡እንዲህ፡ናት፡ፊታ ፳፰፤
ቸው፡እንደ፡ፀሐይ፡እንዲያበራ፡ክብራቸ
ውም፡እንደ፡ከዋክብት፡እንዲያበራ፡ያሳይዋ
ቸው፡ዘንድ፡አላቸውና፡ከዚያም፡በኋላ፡አይ
ሞትምና፡እንደ፡ፀሐይ፡አበራችሁ፡ይሏቸ
ዋል ።
ከሁሉ፡የምትበልጥ፡ሰባተኛይቱም፡ሥራት፡ ፳፱፤
እንዲህ፡ናት፡በሱ፡ዘንድ፡ዋጋ፡ያገኙ፡ይከ
ብሩ፡ዘንድ፡ያላቸው፡ጻድቃን፡በሕይወት፡
ሳሉ፡የተገዙለት፡የእግዚአብሔርን፡ፊት፡
ያዩ፡ዘንድ፡የሚቸኩሉ፡ስለ፡ሆነ፡ሳይፈሩ፡
በብዙ፡ተደላ፡ደስታ፡አምነው፡ፊት፡ለፊት፡
ይመክሉና፡ፊቱን፡ለማየት፡ትቸኩላላችሁ፡
ይሏቸዋል ።
ከዛሬ፡ጀምሮ፡ያገኙ፡ዘንድ፡ያላቸው፡የጻድ ፴፤
ቃን፡ክብራቸው፡ሥራታቸው፡ይህ፡ነው፡ከሀ
ድያን፡መከራ፡በሚቀበሉ፡ገንዘብ፡የነገር
ኩህ፡የኃጥአን፡ሥራታቸው፡ቍርጥ፡ፍርዳ
ቸው፡ይህ፡ነው፡አለኝ ።
መለስኩለት፡እንዲህ፡አልሁት፡ከሥጋዋ፡ ፴፩፤
ከተለየች፡በኋላ፡ይህን፡የነገርኸኝን፡ታይ፡
ዘንድ፡ለነፍስ፡ቀን፡ይሰጣታልን፡አልኩት ።
በነዚያም፡በሰባቱ፡ቀኖች፡የነገርሁህን፡ይህን፡ ፴፪፤
ሁሉ፡ሥራታቸውን፡ያዩ፡ዘንድ፡ሰባት፡ቀን፡
ነፃ፡ናቸው፡ከዚያ፡በኋላ፡ወደ፡ቦታቸው፡
ይመለሳሉ፡አለኝ ።
መለስኩለት፡እንዲህ፡አልሁት፡አቤቱ፡ጌታዬ፡ ፴፫፤
በፊትህ፡ባለሟልነትን፡ካገኘሁ፡ለኔ፡ለባሪያህ፡
ዳግመኛ፡ይህንንም፡ንገረኝ፡ቍርጥ፡ፍርድ፡
በሚደረግበት፡ቀን፡በልዑል፡ዘንድ፡ጻድ
ቃን፡ለኃጥአን፡ማማለድ፡ይችላሉን ።
አበቶች፡ለልጆቻቸው፡ልጆች፡ላባቶቻቸው፡ ፴፬፤
ወንድሞች፡ለወንድሞቻቸው፡ዘመዶች፡ለዘ
መዶቻቸው፡ወዳጆች፡ለወዳጆቻቸው፡ማማ
ለድ፡ይችላሉን፡ብዬ፡ጠየቅሁት ።
መለሰልኝ፡እንዲህ፡አለኝ፡በፊቴ፡ባለሟልነ ፴፭፤
ትን፡አግኝተሃልና፡ይህንንም፡እነግርሃለሁ፡
ቍርጥ፡ፍርድ፡የሚደረግበት፡ቀንስ፡አንድ፡
ጊዜ፡ናት፡በፍጹም፡ትእዛዝ፡የውነተኛ፡
ማኅተሙን፡አብሮ፡ያሳያቸዋል ።
ዛሬ፡አባት፡ልጁን፡ስለሱ፡ይታመም፡ዘንድ ፴፮፤
እንዳይልከው፡ልጅም፡አባቱን፡ስለሱ፡ይታ

መም ፡ ዘንድ ፡ እንዳይልክው ፡ ጌታም ፡ ባሪያ
ውን ፡ ስለሱ ፡ ይታመም ፡ ዘንድ ፡ እንዳይል
ከው ፡ ወዳጅም ፡ ወዳጁን ፡ ስለሱ ፡ ታሞ ፡ ይተኛ ፡
ዘንድ ፡ እንዳይልከው ፡ ስለሱ ፡ በልቶ ፡ ጠጥቶ ፡
ደስ ፡ ይለው ፡ ዘንድ ፡ ከደዌውም ፡ ይፈወስ ፡
ዘንድ ፡ እንዳይልከው ።
፴፯፤ እንደዚሁ ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ መለመን ፡ ፈጽሞ ፡
የሚችል ፡ የለም ፡ ሁሉ ፡ ዋጋውን ፡ ይቀበላ
ልና ፡ ሥራውም ፡ እየራሱ ፡ ነውና ፡ ማንም ፡
ማን ፡ የራሱን ፡ ጭንቅ ፡ ወደ ፡ ባልንጀራው ፡
የሚመልስ ፡ የለም ፡ አለኝ ።
፴፰፤ መለስኩለት ፡ እንዲህ ፡ አልኩት ፡ ቀድሞ ፡ አብ
ርሃም ፡ ስለ ፡ ሰዶምና ፡ ስለ ፡ ገሞራ ፡ ሰዎች ፡
እንደ ፡ ለመነ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ተጽፎ ፡ አገኘን ፡
ሙሴም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በበደሉ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡
አባቶቻችን ፡ እንደለመነ ።
፴፱፤ ኢያሱም ፡ በአካን ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡
እንደ ፡ ለመነ ፡ ሳሙኤልም ፡ ሳኦል ፡ በነገሠበት ፡
ወራት ፡ እንደ ፡ ለመነ ።
፵፤ ዳዊትም ፡ ስለቸነፈር ፡ እንደለመነ ፡ ሰሎሞንም ፡
ስለ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንደለመነ ፡ ኤልያስም ፡
ስለዝናምና ፡ ስለሞቱ ፡ ሰዎችም ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ፡
እንደለመነ ።
፵፩፤ ሕዝቅያስም ፡ በሰናክሬም ፡ ዘመን ፡ ለሕዝቡ ፡
እንደለመነ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ስለብዙ ፡ እንደለ
መኑ ፡ እንደምን ፡ ተጽፎ ፡ አገኘን ፡ አልሁት ።
፵፪፤ ይህ ፡ አላፊው ፡ ዘመን ፡ ፀንቶ ፡ ስለ ፡ ኀጢአ
ትም ፡ በገዛ ፡ ስለጻድቃን ፡ ስለ ፡ ኃጥአን ፡ ከለ
መኑ ፡ ጻድቃንስ ፡ ለኃጥአን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እንደ
ምን ፡ አይለምኑም ፡ አልሁት ።
፵፫፤ መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ዛሬ ፡ የሚታይ ፡
የዚህ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜው ፡ ገና ፡ ነውና ፡ ለዘለ
ዓለም ፡ ፀንቶ ፡ የሚኖር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጌት
ነቱ ፡ ገና ፡ አልተገለጸምና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ዕሩ
ዓን ፡ አእምሮ ፡ ጻድቃን ፡ ለደኩማን ፡ አእምሮ ፡
ኃጥአን ፡ ለመኑ ።
፵፬፤ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ የሚደረግበት ፡ ዕለት ፡ ምጽአ
ትስ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ በሚያልፍ ፡ የማያልፍ ፡ መን
ግሥት ፡ ሰማይ ፡ በሚተካ ፡ ገንዘብ ፡ የዚህ ፡
ዓለም ፡ መጨረሻ ፡ የሚመጣ ፡ የዚያ ፡ ዓለም ፡
መጀመሪያ ፡ ናት ።
፵፭፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ድካመ ፡ ሥጋ ፡ ይጠፋል ፡ ፀብ ፡
ክርክርም ፡ ይጠፋል ፡ ሕግ ፡ ዋጋ ፡ ትሰጣለች ፡
በቅንነት ፡ የተሠራች ፡ ሥራ ፡ ትፀናለች ።
፵፮፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ በሚደረግበት ፡
ቀን ፡ በኀጢአት ፡ ድል ፡ የተነሣ ፡ ሰውን ፡ ይቅር ፡
ማለት ፡ የሚቻለው ፡ የለም ፡ ኀጢአትን ፡ ድል ፡
የነሣ ፡ ሰውንም ፡ መከራ ፡ የሚያፀናበት ፡ የለም ።
፵፯፤ መለስኩለት ፡ እንዲህ ፡ አልሁት ፡ ነገሬ ፡ እንደ
ቀደመው ፡ ነገሬ ፡ ነው ፡ አሁንም ፡ እንዲህ ፡
እላለሁ ፡ በሚበድል ፡ ገንዘብ ፡ ከታስገኘው ፡
ከታስተምረው ፡ ምድር ፡ አዳምን ፡ ባታስገኘው ፡
በተሻለ ፡ ነበር ።
፵፰፤ በኀዘን ፡ እንኖራለንና ፡ ከሞትን ፡ በኋላ ፡ ዳግ
መኛ ፡ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ ይቆዩናልና ፡ ሁላችን ፡
የምንነሣው ፡ ትንሣኤ ፡ ምን ፡ ይረባናል ፡ አል
ሁት ።
አዳም ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ በደልንህ ፡ አንተ ፡ የበደ ፵፱፤
ልህ ፡ ባይሆን ፡ ይህች ፡ መከራ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡
ባልመጣችብንም ፡ ነበር ።
ሞት ፡ የሌለበት ፡ የሚመጣው ፡ ዓለም ፡ መንግ ፶፤
ሥት ፡ ሰማይን ፡ እሰጣቸዋለሁ ፡ ብለህ ፡ የሰጠ
ኸን ፡ ተስፋ ፡ ምን ፡ ይረባናል ፡ እኛ ፡ ግን ፡ የእ
ንስሳን ፡ ሥራን ፡ ሠራን ።
የነገሩንን ፡ በጎውን ፡ አለኝታ ፡ አልሠራንም ፡ ፶፩፤
እኛ ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ሥራን ፡ ሠራን ፡ ክፋትን ፡ ተን
ከልን ።
ኀዘን ፡ ደዌ ፡ የሌለበት ፡ ለኛ ፡ የተዘጋጀ ፡ መን ፶፪፤
ግሥት ፡ ሰማያትን ፡ የምንወርስበት ፡ በጎ ፡
ሥራን ፡ አልተከተልንም ፡ እኛ ፡ ግን ፡ ኀጢአ
ትን ፡ ሠራን ።
ያጸናቸው ፡ መከራ ፡ የተቀበሉ ፡ ጻድቃን ፡ የል ፶፫፤
ዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጌትነቱን ፡ ይወርሱ ፡
ዘንድ ፡ አላቸውና ፡ እነሳቸው ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፡
እኛ ፡ ግን ፡ በኀጢአታችን ፡ ፀንተን ፡ ኖርን ።
የማያልፍ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ይሰጣልና ፡ ፶፬፤
በገነትም ፡ የሚገኝ ፡ ፍሬው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡
ሕይወት ፡ ነውና ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ።
በማንመሰገንበት ፡ ገንዘብ ፡ የማንመሰገንበትን ፡ ፶፭፤
ሥራ ፡ ስለ ፡ ሠራን ፡ እኛ ፡ ግን ፡ መንግሥት ፡
ሰማያት ፡ አንገባም ።
ትዕግሥትን ፡ አፅንተው ፡ የያዙት ፡ የጻድቃን ፡ ፶፮፤
ፊታቸው ፡ ይበራልና ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፡ የኛ ፡
ግን ፡ ፊታችን ፡ ከጨለማ ፡ ይልቅ ፡ ይጠቍራል ።
እነሆ ፡ ከሞትን ፡ በኋላ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ፶፯፤
ምን ፡ እንዳለ ፡ ሳናውቅ ፡ እንኖራለን ፡ አልሁት ።
መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ተወልዶ ፡ በዚህ ፡ ፶፰፤
ዓለም ፡ ለሚኖር ፡ በምግባር ፡ በሃይማኖት ፡ ለሚ
ጋደል ፡ ሰው ፡ የታሰበለት ፡ ይህ ፡ ነው ።
ኀጢአትን ፡ ድል ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ ያልሁ ፶፱፤
ትን ፡ ያገኛል ፡ ብዬ ፡ ተናገርሁ ፡ የታሰበለትን ፡
በኀጢአት ፡ ድል ፡ የተነሣ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ አንተ ፡
ያልከውን ፡ ያገኛል ።
ትድኑ ፡ ዘንድ ፡ ሕይወትን ፡ ምረጡት ፡ ብሎ ፡ ፷፤
ሙሴ ፡ ለእስራኤል ፡ የነገራቸው ፡ ከሱም ፡ በኋላ ፡
የተነሡ ፡ ነቢያት ፡ የተናገሩት ።
ለኔም ፡ ተገለጠልኝ ፡ የተናገርኋቸው ፡ ይህች ፡ ፷፩፤
ሥራ ፡ ናትና ፡ አንተ ፡ ያልከውን ፡ ያገኛል ፡ በጻ
ድቃን ፡ ድኅነት ፡ ደስ ፡ እንዲለኝ ፡ የኃጥአንም ፡
ጥፋት ፡ አያሳዝነኝም ፡ አለኝ ።
መለስኩለት ፡ እንዲህ ፡ አልኩት ፡ አቤቱ ፡ ሁል ፷፪፤
ጊዜ ፡ እንደ ፡ ኢምንት ፡ የሆኑ ፡ ኃጥአንን ፡ ባላ
ቸው ፡ ጊዜ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ዛሬ ፡
ይቅር ፡ ባይ ፡ እንዲባል ፡ ፈጽሜ ፡ አውቃለሁ ።
በድለው ፡ ወደ ፡ ሕጉ ፡ የተመለሱ ፡ ኃጥአንም ፡ ፷፫፤
ይቅር ፡ ባላቸው ፡ ጊዜ ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ እንዲባል ።
እንደ ፡ ጥቂቶችና ፡ እንደ ፡ ልጆች ፡ ጻድቃን ፡ ፷፬፤
የበደሉትን ፡ ሰዎች ፡ ይታገሣቸዋልና ፡ ታጋሢ ፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



እንዲባል ፡ አውቃለሁ ።
፻፴፮ ስለ ፡ ሥራቸው ፡ እንደሚገባቸው ፡ መጠን ፡ ለነገርሁህ ፡ ለኃጥአን ፡ ዋጋቸውን ፡ ይሰጣቸዋልና ፡ ለጋስ ፡ እንዲባል ፡ አውቃለሁ ።
፻፴፯ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላሉ ፡ ኃጥአን ፡ በሕጉም ፡ ለማይታዘዙ ፡ ይመስገኑ ፡ ዘንድ ፡ ላላቸው ፡ ቸርነቱን ፡ ፈጽሞ ፡ ያበዛልና ፡ ቸርነቱ ፡ የበዛ ፡ እንዲባል ፡ አውቃለሁ ።
፻፴፰ ቸርነቱ ፡ ፈጽሞ ፡ ካልበዛ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ፀንቶ ፡ ባልኖረ ፡ ነበረና ፡ በሱም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ፀንተው ፡ ባልኖሩ ፡ ነበርና ፡ ቸርነቱ ፡ የበዛ ፡ እንዲባል ፡ አውቃለሁ ።
፻፴፱ ኃጥአን ፡ ከኃጢአታቸው ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ከቸርነቱ ፡ ካልሰጣቸው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሁሉም ፡ ባልዳነ ፡ ነበርና ፡ ለጋሥ ፡ እንዲባል ፡ አውቃለሁ ።
፻፵ ፈራጅ ፡ የሚሆን ፡ እሱ ፡ የፈጠረውን ፡ ፍጥረት ፡ ካልጠበቀ ፡ የኃጥአን ፡ ብዛታቸው ፡ ከብዙ ፡ ቍጥራቸውም ፡ ይጠፉ ፡ ነበርና ፡ አይቀርም ፡ ነበርና ፡ ያም ፡ ባይሆን ፡ ጥቂት ፡ ስንኳን ፡ ባልቀረም ፡ ነበርና ፡ ለጋስ ፡ እንዲባል ፡ አውቃለሁ ፡ አልሁት ።

## ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩ መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ይህንስ ፡ ዓለም ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለብዙዎች ፡ ኃጥአን ፡ ፈጠረው ፡ የሚመጣውን ፡ ዓለም ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ጥቂቶች ፡ ጻድቃን ፡ ፈጠረው ።
፪ ዕዝራ ፡ እነሆ ፡ በፊትህ ፡ ምሳሌን ፡ እተረጕምልሃለሁ ፡ ምድርን ፡ ጠይቃት ፡ ትነግርሃለች ፡ ሸክላ ፡ ከሱ ፡ የሚገኝ ፡ መሬትን ፡ ታስገኛለችና ፡ ወርቅ ፡ ከሱ ፡ የሚገኝበት ፡ መሬትንም ፡ ታስገኛለችና ፡ ጠይቃት ፡ ትነግርሃለች ፡ ወርቅ ፡ ከሚሆነው ፡ ሸክላ ፡ የሚሆነው ፡ ይበልጣል ፡ ትልሃለች ።
፫ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የተፈጠሩ ፡ ኃጥአን ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ፡ የሚድኑ ፡ ጻድቃን ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ናቸውና ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ሥራው ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ አለኝ ።
፬ መለስሁለት ፡ እንዲህ ፡ አልሁት ፡ ከጥበብ ፡ የተነሣ ፡ ልብ ፡ ደስ ፡ ይበላት ፡ ጆሮም ፡ ነገርን ፡ ከመስማት ፡ የተነሣ ፡ ደስ ፡ ይበላት ።
፭ ጆሮ ፡ ለመስማት ፡ ልብም ፡ ለማወቅ ፡ ተፈጥሯልና ፡ ሰው ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ እንጂ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሳይሰጠው ፡ ባልወደደው ፡ ኃጢአት ፡ ይኖራል ።
፮ አቤቱ ፡ ለኔ ፡ ለባሪያህ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ለመነጋገር ፡ መብት ፡ ካለኝ ፡ አንዲት ፡ ነገር ፡ እጠይቅሃለሁ ፡ የጅህ ፡ ፍጥረት ፡ የምንሆን ፡ እኛ ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ተናገርህ ።
፯ ሁላችን ፡ የተከከልን ፡ ነንና ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ በሚሸከመው ፡ ገንዘብ ፡ የሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ መኖርን ፡ ይቻላቸው ፡ ዘንድ ፡ እንዲያፈራልን ፡ በምንዘራ ፡ በምናርስ ፡ ገንዘብ ፡ የእንስሳ ፡ እውቀትን ፡ ብትሰጠን ፡ በተሻለን ፡ ነበር ።
ዛሬ ፡ በናቱ ፡ ማኅፀን ፡ ትፈጥረዋለህና ፡ ሥጋንም ፡ ታዋሕደዋለህና ፡ ሕዋሳትንም ፡ ትቀርጽለታለህና ፡ ዕውቀትንም ፡ ትሰጠዋለህና ፡ በውሀነት ፡ በእሳትነት ፡ ሳለ ፡ ትጠብቀዋለህና ፡ ያን ፡ የፈጠርከውን ፡ ሕፃኑንም ፡ በናቱ ፡ ማኅፀን ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ትሸከመዋለህና ፡ በንተ ፡ ትእዛዝ ፡ ተጠብቆ ፡ ይኖራልና ። ፰
ዳግመኛ ፡ ተወልዶ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሊኖር ፡ ከተፈጠረ ፡ በኋላ ። ፱
የሚጠባበትን ፡ ወራት ፡ እስኪጨርስ ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ባሪያህ ፡ ሕፃኑ ፡ ያድግ ፡ ዘንድ ። ፲
ከሰውነቷ ፡ በላይ ፡ካለ ፡ ከጡቷ ፡ የጡት ፡ ፍሬ ፡ ወተት ፡ ይፈስለት ፡ ዘንድ ፡ ታዝለታለህና ፡ በቸርነትህም ፡ ታሳድገዋለህና ። ፲፩
በቸርነትህም ፡ ትመግበዋለህና ፡ ሕግህንም ፡ ታስተምረዋለህ ፡ በጥበብህም ፡ ትገሥፀዋለህና ። ፲፪
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አደረግህ ፡ ፈጥረህ ፡ ያሳደግኸውን ፡ ባሪያህን ፡ ትገለዋለህና ። ፲፫
ፈጥረህ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ያኖርከውን ፡ ያንን ፡ ባሪያህን ፡ የምትገለው ፡ ከሆነ ፡ ጥንቱን ፡ ለምን ፡ ፈጠርከው ። ፲፬
አሁንም ፡ ነገርህ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አንተ ፡ ታውቃለህ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ አዘን ፡ የማዝን ፡ ስለ ፡ ርስትህ ። ፲፭
ስለ ፡ ኢየሩሳሌምና ፡ ስለ ፡ ወገኖችህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ይህንን ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ያተጋኝ ፡ ለኔ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ፲፮
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ የሚመጣውን ፡ የመንግሥት ፡ ሰማያትን ፡ ሕጉን ፡ እየሰማን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የምንኖር ፡ የእኛን ፡ መሰነካከል ፡ አያለሁ ፡ ይህንን ፡ በፊትህ ፡ እማልድህ ፡ የጀመርሁ ፡ ስለኔም ፡ ስለነዚያም ፡ ነው ። ፲፯
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ነገሬን ፡ ስማ ፡ በፊትህ ፡ የምናገረው ፡ ልመናዬንም ፡ ስማ ፡ አድምጠኝም ፡ አልኩ ። ፲፰
መላእክት ፡ ወደ ፡ ብሔረ ፡ ሕያዋን ፡ ሳይወስዱት ፡ ዕዝራ ፡ ኋላ ፡ ከሚጸልየው ፡ ጸሎት ፡ አስቀድሞ ፡ የጸለየው ፡ ጸሎት ፡ ይህ ፡ ነው ። ፲፱
ለዘላለሙ ፡ የምትኖር ፡ አቤቱ ፡ በልዑል ፡ አርያም ፡ ሁነህ ፡ ሁሉን ፡ የምታይ ፡ በሰማይ ፡ ያለህ ። ፳
ሥልጣንህ ፡ የማይሸነፍ ፡ መንግሥትህ ፡ የማያልፍ ፡ አገልጋዮችህ ፡ መላእክት ፡ ፈርተው ፡ የሚቆሙልህ ። ፳፩
ነፋስ ፡ እሳት ፡ በትእዛዝህ ፡ የተፈጠሩ ፡ አቤቱ ፡ ቃልህ ፡ ዕሩ ፡ የሆነ ፡ የተናገርከው ፡ ፀንቶ ፡ የሚኖር ። ፳፪
ሥራትህ ፡ ዕሩ ፡ የሆነ ፡ ትእዛዝህም ፡ የሚያስፈራ ፡ ትእዛዝህም ፡ ጥልቆችን ፡ የሚያደርቅ ፡ ቍጣህም ፡ ተራራዎችን ፡ የሚያሳልፍ ፡ አምልኮትህ ፡ እውነት ፡ የሆነ ። ፳፫
እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ የምታደርግ ፡ አቤቱ ፡ የኔን ፡ የባርያህን ፡ ቃል ፡ ስማ ፡ የምነግርህን ፡ ነገሬንም ፡ አድምጥ ። ፳፬

፳፭፤ እኔ፡ በሕይወቴ፡ ሳለሁ፡ እነግርሃለሁ፡ ልቡና
የም፡ እንዳሰበ፡ መጠን፡ እመልስልሃለሁ።
፳፮፤ ላንተ፡ የተገዙልህን፡ የጻድቃንን፡ በጎ፡ ሥራ
ቸውን፡ ተመልከት፡ እንጂ፡ የወገኖችህን፡ ኃጢ
አት፡ አትመልከት።
፳፯፤ ሕግህን፡ የጠበቁ፡ የጻድቃንን፡ መከራቸውን፡
ተመልከት፡ እንጂ፡ የኃጥአንን፡ ክፉ፡ ሥራቸ
ውን፡ አትመልከት።
፳፰፤ በፍጹም፡ ልቡናቸው፡ እምነው፡ በሕግህ፡ የፀ
ኑትን፡ አስብ፡ እንጂ፡ በፊትህ፡ ክፉ፡ ሥራን፡
ስለሠሩ፡ አትቈጣ።
፳፱፤ ሕግህን፡ በዋዊ፡ ልቡና፡ የፀኗት፡ ጻድቃንን፡
አስበቸው፡ ተመልከታቸው፡ እንጂ፡ በሥራ
ቸው፡ እንደ፡ እንስሳ፡ የሆኑ፡ ሰዎችን፡ ጥፋት፡
አትፈልግ።
፴፤ ሁልጊዜ፡ በጌትነትህ፡ የታመኑ፡ ሰዎችን፡ ውደ
ዳቸው፡ እንጂ፡ እንደ፡ አራዊት፡ የክፉ፡ ሰዎ
ችን፡ አትቈጣቸው።
፴፩፤ ነገር፡ ግን፡ እኛም፡ ከኛ፡ አስቀድሞ፡ የነበሩ፡
ሰዎችም፡ የእንስሳ፡ ሥራን፡ ሠራን።
፴፪፤ አንተ፡ ግን፡ በጎ፡ ሥራ፡ የሌለን፡ እኛን፡ ይቅር፡
ብትለን፡ ያን፡ ጊዜ፡ ይቅር፡ ባይ፡ ትባላለህና፡
ስለበደሉ፡ ሰዎችና፡ ስለኛ፡ ይቅር፡ ባይ፡ ሁን።
፴፫፤ ብንተ፡ የተዘጋጀ፡ በጎ፡ ሥራ፡ ያላቸው፡ ጻድ
ቃንን፡ ግን፡ በሥራቸው፡ ይቅር፡ ትላቸዋለህ።
፴፬፤ ትቆጣው፡ ዘንድ፡ ሰው፡ ምን፡ ቁም፡ ነገር፡ ነው፡
ስለሱስ፡ ታዝን፡ ዘንድ፡ የእንስሳ፡ ወገን፡ ምን
ድነው።
፴፭፤ አሁንም፡ ከሴት፡ ከተወለደ፡ ወገን፡ የማይበ
ድል፡ እንደሌለ፡ እውነት፡ እናገራለሁ።
፴፮፤ ነገር፡ ግን፡ በጎ፡ ሥራ፡ የሌላቸው፡ ኃጥአንን፡
ይቅር፡ ብትላቸው፡ ስለዚህ፡ ነገር፡ ቸርነትህ፡
ፈጽሞ፡ ይታወቃል፡ አልኩ።
፴፯፤ መለሰልኝ፡ እንዲህ፡ አለኝ፡ በኔ፡ ዘንድ፡ እው
ነት፡ ነገርን፡ ተናገርህ፡ እንደዚሁ፡ አንተ፡ እን
ደተናገርከው፡ ነው።
፴፰፤ ለሚበድሉ፡ ሰዎች፡ ሞተ፡ ነፍስንና፡ ገሃነምን፡
ጉስቍልናንም፡ እውነት፡ አልወድላቸውም።
፴፱፤ የሚድኑ፡ ዋጋቸውንም፡ የሚያገኙ፡ እነሱቸው፡
ናቸውና፡ ነገር፡ ግን፡ ስለ፡ ጻድቃን፡ ደስ፡ ይለ
ኛል።
፵፤ እንደዚሁ፡ እንደተናገርከው፡ ነው።
፵፩፤ ገበሬ፡ ብዙ፡ ዘር፡ እንዲዘራ፡ ብዙ፡ ተክልንም፡
እንዲተክል፡ ጊዜውም፡ ቢሆን፡ የተዘራው፡
ዘር፡ ሁሉ፡ የሚበቅል፡ አይደለም፡ የተተከለ
ውም፡ ተክል፡ ሁሉ፡ ሥር፡ የሚሰድ፡ አይደ
ለም፡ እንደዚሁ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ያሉ፡ ሰዎ
ችም፡ ሁሉ፡ የሚድኑ፡ አይደለም፡ አለኝ።
፵፪፤ መለስኩለት፡ እንዲህ፡ አልኩት፡ በፊትህ፡ ባለ
ሟልነትንስ፡ ካገኘሁ፡ እነግርሃለሁ።
፵፫፤ የገበሬ፡ ዘርስ፡ ባይበቅል፡ ወይ፡ እንሆ፡ ዝናም፡
ባይገኝ፡ ነው፡ ስለዚህ፡ ነገር፡ ጠፉ፡ ይሉታል።
፵፬፤ ነገር፡ ግን፡ በሥልጣንህ፡ የፈጠርኸው፡ በምሳ
ልህም፡ የመሰልከው፡ ሰው፡ አምሳልህ፡ ነውና፡
ስለሱም። ሁሉን፡ ፈጥረሀልና፡ እንግዲህ፡
ከሆነ፡ ሰውን፡ በተክል፡ ስምን፡ ትመስለዋለህ፡
እንደ፡ ገበሬ፡ ዘርስ፡ ስምን፡ ታደርገዋለህ።
ፍጥረትህን፡ ይቅር፡ ትለዋለህና፡ ለወገኖችህ፡ ፵፭፤
ራራ፡ ርስትህ፡ ኢየሩሳሌምንም፡ ይቅር፡ በል፡
እንጂ፡ አቤቱ፡ በገበሬ፡ ዘር፡ ትመስላቸው፡
ዘንድ፡ እንጃ፡ አገባብህም፡ አይደለም፡ አል
ኩት።
መለሰልኝ፡ እንዲህ፡ አለኝ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ፵፮፤
ያለው፡ ዘር፡ ተክል፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ላሉ፡ ኃጥ
እን፡ ምሳሌያቸው፡ ነው፡ የወዲያው፡ ዓለም፡
ግን፡ በወዲያው፡ ዓለም፡ ለሚኖሩ፡ ጻድቃን፡
ምሳሌያቸው፡ ነው።
ነገር፡ ግን፡ ከኔ፡ ይልቅ፡ ፍጥረቱን፡ ፈጽመህ፡ ፵፯፤
ትወደው፡ ዘንድ፡ ዕውቀት፡ ያንሥህ፡ ይልቁ
ንም፡ አንተ፡ ኃጥእ፡ ሳትሆን፡ በብዙ፡ ወገን፡
ኃጥእ፡ ትመስላለህ።
ነገር፡ ግን፡ ራስህን፡ አዋርደሃልና፡ እንደ፡ ጻድ ፵፰፤
ቃን፡ ፈጽመህ፡ ትመሰገን፡ ዘንድ።
እንደሚገባህም፡ ራስህን፡ አላከበርህምና፡ በል ፵፱፤
ዑል፡ በእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ስለዚህ፡ ነገር፡
ትመሰገናለህ።
አሁንም፡ በዚህ፡ ዓለም፡ የሚኖሩ፡ የጐሰቈሉ፡ ፶፤
ሰዎች፡ በብዙ፡ ትዕቢት፡ ፀንተው፡ ኖረዋልና፡
በኋላ፡ ዘመን፡ ብዙ፡ መከራ፡ ይቀበላሉ።
አንተ፡ ግን፡ ለራስህ፡ ዕወቅ፡ እንዳንተ፡ ያሉ፡ ፶፩፤
ሰዎች፡ የከበሩትንም፡ ክብር፡ መርምር፡ ገነት፡
ለናንተ፡ ትከፈታለችና፡ ዕፀ፡ ሕይወትም፡ ተተ
ክሏልና።
የሚመጣውም፡ ዓለም፡ ተዘጋጅቷልና፡ ተድላ፡ ፶፪፤
ደስታም፡ ተዘጋጅቷልና፡ ጸጋ፡ ክብርም፡ ተዘ
ጋጅቷልና፡ በጎ፡ በረከትም፡ ፀንታለችና፡ የሕግ፡
ዋጋዋ፡ ተሰጥቷልና፡ እንዳንተ፡ ያሉ፡ ሰዎች፡
የከበሩትን፡ ክብር፡ መርምር።
እንግዲህ፡ ወዲህ፡ ደዌ፡ ነፍስ፡ ደዌ፡ ሥጋም፡ ፶፫፤
ጠፋ፡ ሞተ፡ ሥጋ፡ ሞተ፡ ነፍስም፡ ጠፋ፡ መቃ
ብር፡ መቀበሉን፡ ሞት፡ መግደሉን፡ ተወ።
መከራ፡ ተዘነጋ፡ የሕይወት፡ መገኛ፡ መንግ ፶፬፤
ሥት፡ ሰማይት፡ ተገለጠ።
እንግዲህ፡ ወዲህ፡ ዳግመኛ፡ ስለሚጠፉ፡ ስለ፡ ፶፭፤
ኃጥአን፡ ብዙት፡ አትመራመር።
እነሳቸው፡ ዕውቀት፡ አግኝተው፡ ልዑል፡ ፶፮፤
እግዚአብሔርን፡ ንቀውታልና፡ ሕጉንም፡ ቸል፡
ብለዋልና፡ ሥራቱንም፡ አፍርሰዋልና።
ወዳጆቹ፡ ጻድቃንንም፡ መከራ፡ አፅንተውባቸ ፶፯፤
ዋልና።
እያወቁ፡ በልቡናቸው፡ እግዚአብሔርን፡ አንፈ ፶፰፤
ልገውም፡ ብለዋልና።
ስለዚህ፡ ነገር፡ ይህ፡ መንግሥት፡ ሰማይ፡ ላንተ፡ ፶፱፤
እንደ፡ ተዘጋጀ፡ እንደዚሁ፡ ለነሳቸውም፡ ይህ፡
ገሃነመ፡ እሳት፡ ተዘጋጅቶላቸዋል፡ እነሳቸው፡
በሕጉ፡ ሊኖሩ፡ ከተፈጠሩ፡ በኋላ፡ የፈጣሪያቸ
ውን፡ ስም፡ አሳድፈውታልና።
መንግሥተ፡ ሰማይን፡ ያዘጋጀላቸው፡ እግዚአ ፷፤

ብሔርን ፡ አላመሰገኑትምና ፡ በክፉ ፡ ሥራ ፡ ስለ
ፀኑ ፡ ገሃነም ፡ ተዘጋጅቶላቸዋል ።
፰፩ አሁንም ፡ ካንተ ፡ በቀር ፡ እንዳንተም ፡ ካሉ ፡
ከጥቂቶች ፡ ሰዎች ፡ በቀር ።
፰፪ ሉብዙ ፡ ሰዎች ፡ ያልነገርሃቸው ፡ ገሃነም ፡ ይደር
ስባቸዋል ፡ አለኝ ።
፰፫ መለስሁለት ፡ እንዲህ ፡ አልሁት ፡ አቤቱ ፡ እነሆ ፡
እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ታደርገው ፡
ዘንድ ፡ ያለህ ፡ ብዙ ፡ ምልክትን ፡ ነገርኸኝ ፡ ነገር ፡
ግን ፡ የሚደረገበት ፡ ጊዜው ፡ መቸም ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ አልነገርኸኝም ፡ አልሁት ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

፩ መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ አንተ ፡ ራስህ ፡ ገም
ግመው ፡ እኔ ፡ ከነገርሁህ ፡ ምልክት ፡ የተደረገ ፡
ብታይ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠረውን ፡
ይህን ፡ ዓለም ።
፪ ይጎበኝበት ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ጊዜው ፡ እንደ ፡
ደረሰ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በሱ ፡ እወቅ ።
፫ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በየሀገሩ ፡ ሽብር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡
አሕዛብም ፡ በታወኩ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡም ፡ በተጋ
ፈፉ ፡ ጊዜ ፡ አለቆችም ፡ በተዋጉ ፡ ጊዜ ፡ መሳ
ፍንቱም ፡ በደነገጡ ፡ ጊዜ ።
፬ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከጊ
ዜው ፡ አስቀድሞ ፡ እንደተናገረ ፡ ጊዜ ፡ እወቅ ።
፭ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደሆነው ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡
በነቢያት ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ኋላ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡
ሥጋ ፡ ሉብሰ ፡ እንደ ፡ ታየ ።
፮ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ዓለምም ፡
እንደዚሁ ፡ ነው ፡ መጀመሪያ ፡ በሄኖክ ፡ በኤል
ያስ ፡ አድሮ ፡ ድውይ ፡ በመፈወስ ፡ ሙት ፡ በማ
ንሣት ፡ ያስተምራል ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ በሥራ ፡ በግ
ርማ ፡ መለኮት ፡ ይገለጻል ።
፯ በመነበት ፡ በሃይማኖቱ ፡ በምግባሩ ፡ ከኃጢአት ፡
አምልጦ ፡ መዳን ፡ የተቻለው ፡ ሰው ፡ ከነገር
ሁሀ ፡ መከራ ፡ የሚድን ፡ እሱ ፡ ነው ።
፰ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ከለየኋት ፡ በርስቴ ፡ በጉልቴ ፡
በመንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ሕይወትን ፡ ያያል ።
፱ ዛሬ ፡ ትእዛዜን ፡ ቸል ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡
መከራ ፡ ይቀበላሉ ፡ እኔን ፡ መፍራት ፡ የተወ ፡
የናቁኝ ።
፲ እኔ ፡ እየረዳኋቸው ፡ በሕይወት ፡ ሳሉ ፡ በአም
ልኮት ፡ የማያውቁኝም ፡ ሁሉ ፡ በገሃነም ፡ ይፃ
ፃራሉ ።
፲፩ እነሱ ፡ ከሞት ፡ ነጻ ፡ ሆነው ፡ ሳሉ ።
፲፪ የልቡናየም ፡ ትእግሥት ፡ ብዙ ፡ ሆኖላቸው ፡
ሳለ ፡ በሕጉ ፡ የታበዩ ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ልብ ፡
ያላደረጉኝ ፡ ናቁኝ ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ከሞቱ ፡
በኋላ ፡ በገሃነም ፡ ያውቁኝ ፡ ዘንድ ፡ አላቸው ።
፲፫ አንተ ፡ ግን ፡ የሚመጣው ፡ ዓለም ፡ መንግሥት ፡
ሰማያት ፡ ስለነሳቸው ፡ ነውና ፡ ጻድቃን ፡ በዓለ
ማቸው ፡ በመንግሥት ፡ ሰማይ ፡ እንዲድኑ ፡
መርምር ፡ እንጂ ፡ ኃጥአን ፡ እንዲፈረድላቸው ፡
አትመርምር ፡ አለኝ ።

መለስሁለት ፡ እንዲህ ፡ አልሁት ። ፲፬
ከካፊያ ፡ ዝናም ፡ እንዲበዛ ፡ ኋላ ፡ ከሚድኑ ፡ ፲፭
ጻድቃን ፡ የሚጠፉ ፡ ኃጥአን ፡ እንዲበዙ ።
ቀድሞም ፡ ተናገርሁ ፡ ዛሬም ፡ እናገራለሁ ፡ አል ፲፮
ሁት ፡ መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ።
ዘሩ ፡ በርሻው ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሰውም ፡ ፲፯
ፍርዱ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ነው ፡ ጻድቃን ፡ በው
ስጡ ፡ የሚኖሩበት ፡ መንግሥት ፡ ሰማይ ፡ ለጻድ
ቃን ፡ ሳይሰጥ ።
ዛሬ ፡ በዘር ፡ በተክል ፡ ያዘጋጀሁት ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ፲፰
በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ያልፋልና ፡ አጫጁም ፡ አራሹ ፡
እንደ ፡ ገመተው ፡ ነው ፡ አለኝ ፡ ዓለምን ፡ ስፈ
ጥር ፡ ማንም ፡ ማን ፡ አልነበረምና ፡ ኃጥአን ፡
ይውጡ ፡ ጻድቃን ፡ መንግሥት ፡ ሰማይ ፡ ይግቡ ፡
ብልኩ ፡ ጊዜ ፡ የሚከራከረኝ ፡ የለም ።
አሁንም ፡ የሞት ፡ ፍለጋ ፡ በሌለበት ፡ በሕግ ፡ ፲፱
ለዘለዓለም ፡ ፀንተው ፡ ሊኖሩ ፡ በአትክልት ፡
በአዝርእት ፡ በተዘጋጀ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከተፈ
ጠሩ ፡ በኋላ ።
በክፉ ፡ ሥራቸው ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ሲታወክ ፡ በየ ፳
ሁት ፡ ጊዜ ፡ እነሱም ፡ እነሆ ፡ በክፉ ፡ ሥራቸው ፡
ሲጠፉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በተሠራው ፡ ሥራቸው ፡
እነሆ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ሲፃፃር ፡ በየሁት ፡ ጊዜ ።
ሄጂ ፡ ጥቂት ፡ እሸትን ፡ አሸሁ ፡ ከብዙም ፡ ዘለላ ፡ ፳፩
እኔ ፡ ጥቂት ፡ ዘለላን ፡ አዳንኩ ፡ (ጥቂቶች ፡ ጻድ
ቃን ፡) ከብዙም ፡ ዛፍ ፡ አንደ ፡ ተክል ፡ መረ
ጥሁ ፡ (ከአበው ፡ አብርሃምን ፡) ።
ከንቱ ፡ ሊሆን ፡ የተፈጠሩ ፡ የኃጥአን ፡ ብዛታ ፳፪
ቸው ፡ ይጠፋል ፡ በብዙ ፡ ሥራ ፡ የፀናች ፡ ዘለ
ላዬ ፡ ተክሌ ፡ ትጠበቃለች ፡ (በምግባር ፡ በሃይ
ማኖት ፡ የፀናች ፡ አብርሃም ።)
አንተ ፡ ግን ፡ ዳግመኛ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ብትጾም ፡ ፳፫
ብትጸልይ ።
ግምብ ፡ ባልተሠራበት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ የሄድህ ፡ ፳፬
የእንጨት ፡ ፍሬ ፡ ብቻ ፡ ብትበላ ፡ ሥጋም ፡ ያል
በላህ ፡ ወይንም ፡ ያልጠጣህ ፡ ከእንጨቱ ፡ ፍሬ ፡
ብቻ ፡ በቀር ፡ ሥጋ ፡ ባትበላ ፡ ወይን ፡ ባትጠጣ ።
ወደ ፡ ልዑል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁልጊዜ ፡ ፳፭
ብትጸልይ ፡ መጥቼ ፡ እነግርሃለሁ ፡ አለኝ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘኝ ፡ ስሙ ፡ ፳፮
አርፋድ ፡ ወደሚባል ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሄድሁ ።
በማር ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጥሁ ፡ የምድረ ፡ በዳንም ፡ ፳፯
ፍሬ ፡ ተመገብሁ ፡ የበላሁትም ፡ ፍሬ ፡ ያጠግ
በኝ ፡ ነበር ።
ከዚህ ፡ ከሰባተኛው ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በማር ፡ መከ ፳፰
ከል ፡ ተኝቼ ፡ ሳለሁ ፡ እንደቀድሞው ፡ ልቡናዬ ፡
ታወከብኝ ።
አንደበቴን ፡ አቅንቼ ፡ በልዑል ፡ በእግዚአብ ፳፱
ሔር ፡ ፊት ፡ እናገር ፡ ጀመርኩ ።
አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ ተክል ፡ እህል ፡ በሌለበት ፡ ፴
ምድረ ፡ በዳ ፡ ፈጽመህ ፡ ታየህ ፡ አልኩ ።
አንተ ፡ እስራኤል ፡ ስማኝ ፡ በመካከላችሁ ፡ ፴፩
እነሆ ፡ እኔ ፡ ሕጌን ፡ እሠራለሁና ፡ ሕጌንም ፡
ብትጠብቁት ፡ ዋጋ ፡ ያስጣችኋልና ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianortho dox.org



፴፪ ለዘለዓለሙም ፡ ትክብሩበታላችሁና ፡ ቃሌን ፡
አድምጡኝ ፡ አልክ ።
፴፫ አባቶቻችንም ፡ ሕግህን ፡ ተቀብለው ፡ አልጠበ
ቁም ፡ በሥራትህም ፡ አልፀኑም ፡ ያንተ ፡ ገን
ዘብ ፡ ስለሆነ ፡ ይጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አይቻልምና ፡
ከሕግህ ፡ ወገን ፡ ግን ፡ አልጠፋም ።
፴፬ ሕግ ፡ ያንተ ፡ ገንዘብ ፡ ስለሆነች ፡ የሠራላቸውን ፡
ሕግ ፡ አልጠበቁምና ፡ ሕግህን ፡ ተቀብለው ፡ ያል
ጠበቁ ፡ ሰዎች ፡ ጠፉ ።
፴፭ ምድርም ፡ ዘርተውበት ፡ በታበቅል ፡ ባሕርም ፡
መርከቡን ፡ ከጫኑበት ፡ በኋላ ፡ ብታሰጥም ።
፴፮ ያን ፡ ጊዜ ፡ የዚያ ፡ የዘሩ ፡ ጊዜው ፡ ቢሆን ፡ የዚ
ያም ፡ የመርከቡ ፡ ጊዜው ፡ ቢሆን ፡ የዚያም ፡ የመ
ብሉ ፡ የመጠጡ ፡ ጊዜው ፡ ቢሆን ፡ ምድርን ፡
ዳግመኛ ፡ እንዳይዘሩበት ፡ ባሕርንም ፡ ዳግመኛ ፡
መርከብን ፡ እንዳይጭኑበት ፡ በዕቃውም ፡ ዳግ
መኛ ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ እንዳይዘጋጅበት ፡
ሕግን ፡ ተቀብለው ፡ ያፈረሱ ፡ ሰዎች ፡ እንደ
ዚሁ ፡ ይጠፋሉ ።
፴፯ አቅንቼ ፡ በየሁ ፡ ጊዜ ፡ በቀኝ ፡ በኩል ፡ የምታለ
ቅስ ፡ ሴትን ፡ አየሁ ፡ ቃሏን ፡ አሰምታ ፡ ትጮ
ሃለች ፡ ሰውነቷም ፡ ፈጽማ ፡ ታዝናለች ፡ ልብሷ
ንም ፡ ቀዳለች ፡ በራሷም ፡ አመድ ፡ ነስንሳለች ።
፴፰ ያ ፡ ቀድሞ ፡ የማስበው ፡ አሳቤም ፡ ተለየኝ ፡
ወደሷ ፡ ተመልሼ ፡ ምን ፡ ያስለቅስሻል ፡ ልቡና
ሽን ፡ ለምን ፡ ታሳዝኛለሽ ፡ አልኋት ።
፴፱ ጌታዬ ፡ በራሴ ፡ በመጣብኝ ፡ መከራ ፡ አለቅስ ፡
ዘንድ ፡ ተወኝ ፡ ፈጽሜ ፡ እኔ ፡ አዝኛለሁና ፡
ልቡናየም ፡ አዝናለችና ፡ በመከራዬ ፡ ላይ ፡
መከራ ፡ እጨምራለሁ ፡ አለችኝ ።
፵ ምን ፡ ሆንሽ ፡ ንገሪን ፡ አልኋት ።
፵፩ እኔ ፡ ባሪያህ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ መካን ፡ ነኝ ፡
ሠላሳ ፡ ዘመን ፡ ከባሌ ፡ ጋራ ፡ ስኖር ፡ ልጅ ፡ አል
ወለድሁም ።
፵፪ እኔ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ በሠላሳው ፡ ዘመን ፡ በየጊ
ዜው ፡ በየሰዓቱ ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡
ወደ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ እጸልይ ፡ ነበር ።
፵፫ ከዚህ ፡ ከሠላሳ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ የባሪያውን ፡
ልመና ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማ ፡ ኀዘኔንም ፡ ሰማኝ ፡
መከራዬንና ፡ ድካሜንም ፡ አይቶ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡
ሰጠኝ ፡ በሱም ፡ እኔን ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡
ባሌንም ፡ ደስ ፡ አለው ፡ ያገሬንም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
ደስ ፡ አላቸው ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገ
ነው ።
፵፬ በብዙ ፡ ድካምም ፡ አሳደግሁት ።
፵፭ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡
ሚስት ፡ አጋባሁት ፡ ሠርግን ፡ ሠረግሁለት ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

፩ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጫጉላው ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡
ወድቆ ፡ ሞተ ።
፪ ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ፋናችንን ፡ መብራታችንን ፡
አጥፍተን ፡ እናለቅስ ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጥን ፡ ያገ
ሮቹ ፡ ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ ተነሥተው ፡ ይመክሩኝ ፡
ያረጋጉኝ ፡ ጀመሩ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በማግሥቱ ፡
ቀን ፡ እስከሰከተለችው ፡ ሌሊት ፡ ድረስ ፡ ዝም ፡
አልኩ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁሉም ፡ ዝም ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ እኔን ፡ ፫
ማረጋጋት ፡ እኔን ፡ መምከር ። በተወ ፡ ጊዜ ፡
እኔ ፡ ሌሊት ፡ ተነሥቼ ፡ ሸሸሁ ፡ ወደዚህም ፡
ምድረ ፡ በዳ ፡ መጣሁ ።
ለዘላለሙ ፡ በዚህ ፡ እኖራለሁ ፡ እንጂ ፡ እንግ ፬
ዲህ ፡ ወዲህ ፡ ወደ ፡ አገሬ ፡ እንዳልመለስ ፡ ቈረ
ጥሁ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እጾማለሁ ፡ እስክሞት ፡ ድረስ ፡
አለቅሳለሁ ፡ እንጂ ፡ እህል ፡ አልበላም ፡ ወሀም ፡
አልጠጣም ፡ አልሁ ።
ያ ፡ የማስበው ፡ አሳብም ፡ ተወኝ ፡ መለስኩላት ፡ ፭
እንዲህ ፡ አልኋት ፡ ከሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡
አንቺ ።
አላዋቂ ፡ ነሽ ፡ ስለ ፡ ጽዮን ፡ ያገኘችንን ፡ የኛን ፡ ፮
ልቅሶ ።
አታይምን ፡ ሁላችን ፡ በኀዘን ፡ እንዳለን ፡ መከ ፯
ራንም ፡ ፈጽመን ፡ እንደተቀበልን ፡ አታይምን ።
እኛ ፡ ሁላችንም ፡ ያዘን ፡ ያለቀስን ፡ ነንና ፡ አሁ ፰
ንም ፡ በውነት ፡ ታዝኚ ፡ ታለቅሺ ፡ ዘንድ ፡ ይገ
ባሻል ፡ እኛ ፡ ስለ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ እናዝናለን ፡
አንቺ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ልጅሽ ፡ ታዝኛለሽ ፡
ታለቅሻለሽ ።
ምድርን ፡ ጠይቂያት ፡ ትነግርሻለች ፡ ሁላቸው ፡ ፱
ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ በሷ ፡ የተፈጠሩ ፡ ብዙ ፡ ልጆ
ቿን ፡ እነሆ ፡ አሕዛብ ፡ መጥተው ።
ፈጽሞ ፡ ለማጥፋት ፡ ማርከው ፡ ወሰደዋቸዋልና ፡ ፲
ይልቁንም ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ያጠፉባት ፡ ምድር ፡
ልታለቅስ ፡ ይገባታል ።
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ፈጽሞ ፡ ያለቅስ ፡ ዘንድ ፡ ፲፩
የሚገባው ፡ ማነው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ብዙ ፡ የጠ
ፋባት ፡ ያለቅስ ፡ ዘንድ ፡ ይገባልን ፡ ወይስ ፡ አንቺ ፡
ስለ ፡ አንድ ፡ ልጅሽ ፡ ታለቅሺ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ።
ወይስ ፡ የኔ ፡ ልቅሶ ፡ እንደ ፡ ምድር ፡ ልቅሶ ፡ አይ ፲፪
ደለም ፡ ትያለሽን ፡ በፃዕር ፡ በገዓር ፡ አምጬ ፡
የወለድኩት ፡ ልጄን ፡ አጥቻለሁና ።
ምድር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ አሕዛብ ፡ ወደሷ ፡ እንደ ፲፫
መጡ ፡ ልጆቿ ፡ እንደዚሁ ፡ ተማርከው ፡ ሄደዋ
ልና ፡ የኔ ፡ ልቅሶ ፡ እንደ ፡ ምድር ፡ ልቅሶ ፡ አይ
ደለም ፡ ትያለሽን ።
ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ እልሻለሁ ፡ አንቺ ፡ ፲፬
አምጠሽ ፡ ወልደሽ ፡ እንዳሰደግሽው ፡ ምድርም ፡
እንደዚሁ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ በሷ ፡ ለተፈጠሩ ፡
ሰዎች ፡ ፈጣሪዋ ፡ የሰጣት ፡ ፍሬዋን ፡ ሰጠቻ
ቸው ።
አሁንም ፡ ይህንን ፡ ኀዘንሽን ፡ ካንቺ ፡ አርቂ ፡ ፲፭
ያገኘችሽንም ፡ ቅጣትና ፡ መከራ ፡ የታገሺ ፡
ሁኚ ።
እግዚአብሔርን ፡ ብታመሰግኚው ፡ ይረዳሻልና ፡ ፲፮
ልጅሽንም ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ታገኚዋለሽና ፡ በት
ንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ በሴቶችም ፡ ዘንድ ፡ መከራን ፡
የታገሽ ፡ ትባያለሽና ፡ ይህንን ፡ ኀዘንሽን ፡ አርቂ ።
አሁንም ፡ ወደሀገርሽ ፡ ግቢ ፡ ወደባልሽም ፡ ሒጂ ፡ ፲፯

አልኋት ።
፲፰፤ እንዲህ ፡ አላደርግም ፡ በዚህ ፡ እሞታለሁ ፡
እንጂ ፡ ወዳገርም ፡ አልገባም ፡ አለችኝ ።
፲፱፤ ዳግመኛም ፡ ጠየቅኋት ፡ ተናገርኋት ።
፳፤ ይህንን ፡ ነገር ፡ አታድርጊ ፡ እሺ ፡ በይኝ ፡ ራስሽ
ንም ፡ እንደ ፡ ጽዮን ፡ መከራ ፡ አድርጊ ፡ የኢየ
ሩሳሌምንም ፡ መከራ ፡ አይተሽ ፡ ተረጋጊ ፡ አል
ኋት ።
፳፩፤ ቤተ ፡ መቅደሳችን ፡ እንደ ፡ ፈረሰ ፡ አታይምን ።
፳፪፤ ግናይቱ ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ ምስጋናችን ፡ እንደ ፡ ቀረ ፡
ዘመራ ፡ ዘውዳችን ፡ እንደወደቀ ፡ ተድላ ፡ ደስታ
ችን ፡ እንደጠፋ ፡ የሕጋችን ፡ ማደሪያ ፡ ታቦተ ፡
ጽዮን ፡ እንደ ፡ ተማረከች ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ እን
ዳደፈ ፡ ምልክታችን ፡ እንደ ፡ ቀረ ፡ ጌቶቻችን ፡
እንደጐሰቈሉ ፡ ካህናቱ ፡ እንደ ፡ ተቃጠሉ ፡ ሌዋ
ውያን ፡ እንደ ፡ ተማረኩ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችን ፡
እንደሞቱ ፡ ሚስቶቻችንን ፡ እንደቀሙን ፡ መም
ሮቻችን ፡ እንደ ፡ ተገጐተቱ ፡ ጐልማሶቻችን ፡ እን
ደ ተገዙ ፡ ወንዶች ፡ ልጆቻችን ፡ እንደ ፡ ተቀሙ ፡
አርበኞቻችን ፡ እንደ ፡ ደከሙ ፡ አታይምን ።
፳፫፤ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ታቦተ ፡ ጽዮን ፡
እንደ ፡ ጠፋች ፡ ቀረች ፡ ክቧም ፡ ንዋየ ፡ ቅድ
ሳቷ ፡ ተማርኮ ፡ ሄደ ፡ በጠላቶቻችን ፡ በባቢሎን ፡
ሰዎች ፡ እጅ ፡ ወደቅን ።
፳፬፤ አንቺም ፡ ብዙ ፡ ኀዘንሽን ፡ ተይ ፡ ኃያል ፡ የሚ
ሆን ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ይልሽ ፡
ዘንድ ፡ ከድካምሽም ፡ ፈጽሞ ፡ ያሳርፍሽ ፡ ዘንድ ፡
ይህንን ፡ ብዙ ፡ ኀዘንሽን ፡ አርቂ ፡ አልኋት ።
፳፭፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይኽን ፡ ስናገራት ፡ ድንገት ፡ ፊቷ ፡
ከፀሐይ ፡ ይልቅ ፡ በራ ፡ መልኳም ፡ እንደ ፡ መብ
ረቅ ፡ መልክ ፡ ሆነ ፡ ወደሷ ፡ መቅረብን ፡ ፈራሁ ፡
ልቡናዬም ፡ ደነገጠብኝ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡
ምንም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሳስብ ፡ አስደነገጠችኝ ።
፳፮፤ አሰምታ ፡ ተናገረች ፡ ከነጋገሯ ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡
እስክትነዋወጥ ፡ ድረስ ፡ ድምጿ ፡ እጅግ ፡ የሚ
ያስፈራ ፡ ሆነ ።
፳፯፤ በየኋትም ፡ ጊዜ ፡ የከበረች ፡ የታነጸች ፡ አገር ፡
ናት ፡ እንጂ ፡ እነሆ ፡ ሴት ፡ አይደለችም ፡ ታላቅ ፡
የሆነ ፡ የመሠረቶቿን ፡ በታ ፡ አየሁ ፡ ፈርቼም ፡
ቃሴን ፡ አሰምቼ ፡ ጮኹ ።
፳፰፤ አስቀድሞ ፡ ወደኔ ፡ የመጣህ ፡ መልአኩ ፡ አንተ ፡
ዑርኤል ፡ ወዴት ፡ ነህ ፡ ለምን ፡ እንዲህ ፡ አደረ
ግኸኝ ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ ምርምር ፡ እገባ ፡ ዘንድ ፡
ፍጻሜዬም ፡ ለጕስቍልና ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ልመ
ናዬም ፡ ለተግዳሮት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡
ለምን ፡ አደረግኸኝ ፡ አልሁ ።
፳፱፤ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ስናገር ፡ እነሆ ፡ ቀድሞ ፡
ወደኔ ፡ የመጣ ፡ ያ ፡ መልአክ ፡ ወደኔ ፡ መጣ ።
፴፤ እንደ ፡ ሬሳ ፡ ተኝቼ ፡ አገኘኝ ፡ አእምሮዬም ፡
ከኔ ፡ ጋራ ፡ አልነበረም ፡ ቀኝ ፡ እጄን ፡ ይዞ ፡ አነ
ሣኝ ፡ በእግሮቼም ፡ አቅንቶ ፡ አቆመኝ ።
፴፩፤ መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ምን ፡ ሆንህ ፡ ምን ፡
ያስደነግጥሃል ፡ አእምሮህስ ፡ ከንተ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡
ምን ፡ የለም ፡ አለኝ ።

ጥለሽኛልና ፡ ተለይተሽኛልና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ ፴፪፤
እኔም ፡ እንደ ፡ ነገርሽኝ ፡ ወደዚህ ፡ ምድረ ፡
በዳ ፡ መጣሁ ፡ ወደዚህም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በመ
ጣሁ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ ማወቅ ፡ የማይቻለኝን ፡
አየሁ ፡ አልሁት ።
እንግዲህስ ፡ እነግርህ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ባለ ፡ አእ ፴፫፤
ምሮ ፡ ሰው ፡ ቁም ፡ አለኝ ።
ያላየሁትን ፡ አይቻለሁና ፡ የማላውቀውንም ፡ ፴፬፤
ሰምቻለሁና ፡ ድንገት ።
እንዳልሞት ፡ እንግዲህ ፡ አትለየኝ ፡ እንጂ ፡ ፴፭፤
አቤቱ ፡ በል ፡ ተናገር ፡ አልሁት ።
ነገር ፡ ግን ፡ ተለይተኸኝ ፡ ልቡናዬ ፡ ይዘነጋ ፡ ፴፮፤
ይሆንን ፡ ሰውነቴስ ፡ ትጨነቅ ፡ ይሆንን ።
አሁንም ፡ አቤቱ ፡ በጅ ፡ በለኝ ፡ የዚህን ፡ ነገር ፡ ፴፯፤
ትርጓሜ ፡ ለኔ ፡ ለባሪያህ ፡ ንገረኝ ፡ አልሁት ።
መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ይህ ፡ የተሠወረ ፡ ፴፰፤
ምሥጢር ፡ ስለሆነ ፡ ለወገኖችህ ፡ ብዙ ፡ ታዝ
ናለህና ፡ ስለ ፡ ጽዮንም ፡ ፈጽመህ ፡ ትቈረቈራ
ለህና ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖትህን ፡ በየ ፡ ጊዜ ።
ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ገልጦልሃልና ፡ ስለም ፴፱፤
ትፈራው ፡ ነገር ፡ አስተምርህ ፡ ዘንድ ፡ ስማኝ ፡
አለኝ ።
ነገሩ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ቀድሞ ፡ ስታለቅስ ፡ ያየሃት ። ፵፤
ታረጋጋትም ፡ ዘንድ ፡ የጀመርህ ፡ ይች ፡ ሴት ። ፵፩፤
አሁን ፡ ግን ፡ የታነጸች ፡ ሀገር ፡ ትሆንብሃለች ፡ ፵፪፤
እንጂ ፡ አንተ ፡ እንዳየሃት ፡ ሴት ፡ ያልሆነች ።
የልጅዋን ፡ መከራ ፡ ነግራሃለችና ፡ ልታረጋጋት ፡ ፵፫፤
የጀመርክ ።
ይች ፡ ያየሀት ፡ ሴት ፡ ዛሬ ፡ የታነጸች ፡ አገር ፡ ፵፬፤
ሁና ፡ የምታያት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ናት ።
ይህ ፡ ሠላሳ ፡ ዘመን ፡ መካን ፡ ሆንኩ ፡ ያለችህም ፡ ፵፭፤
መሥዋዕት ፡ ሳይሰዉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡
ሰዎች ፡ ሦስት ፡ ሺ ፡ ዘመን ፡ ኑረዋልና ፡ መሥ
ዋዕት ፡ ባይሠዉ ፡ ሦስት ፡ ሺ ፡ ዘመን ፡ ኑረዋ
ዋልና ፡ ይህ ፡ ነው ።
ከሦስት ፡ ሺህ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ሰሎሞን ፡ ቤተ ፡ ፵፮፤
መቅደስን ፡ ሠራ ፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ መሥዋዕትን ፡
ሠዋ ፡ ያች ፡ መካን ፡ ሴት ፡ የወለደችውም ፡
ልጅ ።
ይህም ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ አሳደግሁት ፡ ያለችህ ፡ ፵፯፤
ኢየሩሳሌም ፡ መሥዋዕት ፡ ሳይሠዋባት ፡ የኖረ
ችው ፡ ዘመን ፡ ነው ።
ይህም ፡ ልጅዋ ፡ ወደ ፡ ጫጕላው ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ፵፰፤
ወድቆ ፡ ሞተ ፡ ይችም ፡ መከራዋ ፡ አገኘችኝ ፡ ያለ
ችህ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ጥፋቷ ፡ ነው ።
እነሆ ፡ ለልጆቿ ፡ ታለቅስላቸው ፡ ዘንድ ፡ እንዳ ፵፱፤
ለች ፡ ያየሃት ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ከመከራዋ ፡ ታረጋ
ጋት ፡ ዘንድ ፡ የጀመርህ ፡ ያች ፡ ሴት ፡ ኢየሩሳ
ሌም ፡ ናት ።
አሁንም ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በፍጹም ፡ ፶፤
ሰውነትህ ፡ እንድታዝን ፡ በፍጹም ፡ ልቡናህም ፡
እንድትቈረቈር ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ የተሠወረ ፡ ምሥ
ጢር ፡ ነው ፡ የተድላ ፡ የደስታዋን ፡ ጌጥ ፡ የጌ
ትነትዋንም ፡ መገለጽ ፡ ስለሷ ፡ አሳየህ ።

፶፩፤ እግዚአብሔር ፡ ያሳይህ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡
አውቂያለሁና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ።
፶፪፤ ቤት ፡ በሌተሠራበት ፡ በዚህ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡
ትኖር ፡ ዘንድ ፡ እነግርሃለሁ ።
፶፫፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሥጢር ፡ ይገልጽ
በት ፡ ዘንድ ፡ በሰው ፡ በታ ።
፶፬፤ የሰው ፡ ሥራ ፡ ሊኖር ፡ አይቻልምና ፡ ስለዚህ ፡
ነገር ፡ የግምብ ፡ መሠረት ፡ ወደሌለበት ፡ ወደ
ዚህ ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ እነግርሃለሁ ።
፶፭፤ አንተ ፡ ግን ፡ እንግዲህ ፡ አትፍራ ፡ ገብተህ ፡ ተድ
ላዋን ፡ ድስታዋን ፡ የሥራዋንም ፡ጽናት ፡ እይ ፡
እንጂ ፡ ልብህም ፡ አይደንግጥ ።
፶፮፤ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይልቅ ፡ አንተ ፡ ራስህን ፡ አስደ
ንቀሃልና ።
፶፯፤ በልዑልም ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ጥቂቶች ፡ ጻድቃን ፡
ጻድቅ ፡ ተብለሃልና ፡ በጆሮህም ፡ የተቻለህን ፡
ያህል ፡ ስማ ።
፶፰፤ ዛሬ ፡ በዚህ ፡ እደር ።
፶፱፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚ
ኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ የሚያደር
ገውን ፡ ራዕይ ፡ ነገ ፡ በሕልም ፡ ያሳይሃል ፡ አለኝ ።
፷፤ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ አደርኩ ፡ እንዳዘዘኝ ፡ በማግ
ሥቱም ፡ አደርኩ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

፩፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሌሊቱ ፡ ማግስት ፡ ንስር ፡ ከባ
ሕር ፡ ሲወጣ ፡ በሕልም ፡ አየሁ ፡ (መንግሥት ፡
ባቢሎን ፡) ክንፎችም ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ናቸው ፡
ራሶቹም ፡ ሦስት ፡ ናቸው ።
፪፤ በክንፉም ፡ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ይበራል ፡ (በሥል
ጣኑ ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ ይገዛል ፡) የሰማይ ፡ነፋሳ
ትም ፡ ሁሉ ፡ ይነፍሱበታል ፡ (መኳንንት ፡) ደመ
ናትም ፡ በሱ ፡ ይሰበሰባሉ ።
፫፤ ከነዚያም ፡ ክንፎቹ ፡ ራሶች ፡ ይበቅላሉ ፡ (ልጆች ፡
ይወልዳሉ ፡) እነዚያም ፡ ራሶች ፡ ቃናናሽ ፡ ክንፍ ፡
ይሆናሉ ፡ ደከሞች ፡ ይሆናሉ ።
፬፤ ራሶቹም ፡ ዝም ፡ ይላሉ ፡ ከነዚያም ፡ ራሶቹ ፡
የመካከለኛው ፡ ራሱ ፡ ይበልጣል ፡ ነገር ፡ ግን ፡
እሱም ፡ ከነሳቸው ፡ ጋራ ፡ ዝም ፡ ይላል ።
፭፤ ያም ፡ ንሥር ፡ ምድርን ፡ ይገዛት ፡ ዘንድ ፡ በም
ድር ፡ ያሉ ፡ ሰዎችንም ፡ ይገዛቸው ፡ ዘንድ ።
፮፤ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ያሉ ፡ ሁሉ ፡ ይገዙለት ፡ ዘንድ ፡
በክንፉ ፡ ይበራል ፡ ያንንም ፡ ንስር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ከተፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ የሚከራከረው ፡ የለም ።
፯፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ንሥር ፡ ተነሥቶ ፡ በጥፍሮቹ ፡
ቆሞ ፡ ቃሉንም ፡ አሰምቶ ፡ ጮኸ ።
፰፤ ክንፎቹንም ፡ ሁላችሁ ፡ ከናንተ ፡ አንዱም ፡ አን
ዱም ፡ በየበታችሁ ፡ ተኙ ፡ እንጂ ፡ ሁላችሁ ፡ አን
ድነት ፡ አትነሡ ፡ በየጊዜው ፡ ትነሣላችሁ ።
፱፤ የኋለኛይቱ ፡ ራሱ ፡ ከሁሉ ፡ ትበልጣለች ፡ አለኝ ፡
(ከፋርስ ፡ በኋላ ፡ የተነሣች ፡ መንግሥተ ፡ ጽርዕ ፡
ከሁሉ ፡ ትበልጣለች ) ።
፲፤ በየሁ ፡ ጊዜ ፡ የሚገዙ ፡ ከዘመዶቹ ፡ የሚወለ
ደው ፡ነው ፡ እንጂ ፡ ከሱ ፡ የሚወለደው ፡ አይ
ደለም ።
የነዚያ ፡ የራሶች ፡ ቍጥርም ፡ ስምንት ፡ ናቸው ፡ ፲፩፤
(የሊህ ፡ የነገሥታት ፡ ቍጥርም ፡ ስምንት ፡
ናቸው ) ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በቀኝ ፡ በኩል ፡ ወጣ ፡ ዓለሙ ፲፪፤
ንም ፡ ሁሉ ፡ ገዛ ፡ አለ ። (ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በባ
ቢሎን ፡ ቀኝ ፡ ያለ ፡ መንግሥት ፡ ሚዶን ፡ ተነሣ ፡
ዓለሙንም ፡ ሁሉ ፡ ገዛ ፡)
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጥፋቱ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በታው ፡ ፲፫፤
የማይታይ ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ እሱም ፡ ጠፋ ፡
አለ ፡ ሁለተኛውም ፡ ወጣ ፡ እሱም ፡ ብዙ ፡
ዘመን ፡ አጽንቶ ፡ ገዛ ፡ አለ ፡ (በልንጀራው ፡
ፋርስ ፡ ተነሣ ፡ ብዙ ፡ ቀንም ፡ አጽንቶ ፡ ገዛ ፡ )
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የሚጠፋበት ፡ ቀን ፡ በደረሰ ፡ ፲፬፤
ጊዜ ፡ እሱም ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ጠፋ ።
ቃል ፡ መጣለት ። ፲፭፤
ምድርን ፡ ይኸን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ አጽንተህ ፡ ፲፮፤
የገዛሃት ፡ አንተ ፡ አምራ ፡ ሳትጠፋ ፡ ይኸን ፡
የምነግርህን ፡ ስማ ፡ አለ ፡ (ዓቢይ ፡ እንጥያኮስ ፡)
ከንቱ ፡ በኋላ ፡ እንዳንተ ፡ የሚጸና ፡ የኩሌታህ
ንም ፡ እኩሌታ ፡ እንዳንተ ፡ የሚገዛ ፡ የለም ፡ ፲፯፤
(አፊፋኖስ ፡)
ሦስተኛውም ፡ ወጣ ፡ እሱም ፡ ከሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ፲፰፤
እንደ ፡ ነበረው ፡ አጽንቶ ፡ ገዛ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡
እሱም ፡ ጠፋ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ ክንፎቹ ፡ (ነገሥታቱ ፡) ፲፱፤
ሁሉ ፡ ወጡ ፡ እያንዳንዳቸውም ፡ ገዙ ፡ ዳግ
መኛ ፡ ሁሉም ፡ ጠፉ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አጽንተው ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ በግራ ፡ ፳፤
በኩል ፡ በየጊዜያቸው ፡ ክንፎቹ ፡ (ነገሥታቱ ፡)
ተነሡ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፈጥነው ፡ ጠፉ ።
ከሳቸውም ፡ የተነሡ ፡ አሉ ፡ ነገር ፡ እነሱ ፡ አል ፳፩፤
ገዙም ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እሊህ ፡ አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ክንፎቹ ፡ ፳፪፤
(ነገሥታቱ ፡) ጠፉ ፡ እሊህም ፡ ሁለቱ ፡ ራሶቹ ፡
(ነገሥታቱ ፡) ጠፉ ።
ዝም ፡ ከሚሉ ፡ ከሦስቱ ፡ ራሶቹ ፡ (ነገሥታቱ ፡) ፳፫፤
በቀር ፡ ከዚህ ፡ አምራ ፡ ወገን ፡ የቀረ ፡ የለም ፡
ከስድስቱ ፡ (ነገሥታቱ ፡) ራሶቹም ፡ በቀር ፡ የቀረ ፡
የለም ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሊህ ፡ ከስድስቱ ፡ ራሶቹ ፡ ሁለቱ ፡ ፳፬፤
ተለይተው ፡ ሄዱ ፡ በቀኝ ፡ በኩል ፡ ባለ ፡ ራሱ ፡
ውስጥ ፡ የተቀመጡ ፡ አራቱ ፡ ግን ፡ በበታቸው ፡
ቀሩ ።
እሊህ ፡ አራቱ ፡ ራሶች ፡ (ነገሥታቱ ፡) ግን ፡ ፳፭፤
ይቆሙ ፡ ዘንድ ፡ አለሱም ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ ተማ
ከሩ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንዱ ፡ ተነሥቶ ፡ ቆመ ፡ ነገር ፡ ፳፮፤
ግን ፡ ፈጥኖ ፡ ጠፋ ።
ሁለተኛውም ፡ እንደሱ ፡ ከፊተኛው ፡ ይልቅ ፡ ፳፯፤
እሱ ፡ ፈጥኖ ፡ ጠፋ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሞት ፡ የቀሩት ፡ እሊህ ፡ ሁለቱ ፡ ፳፰፤
ነግሠው ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ እንደሱ ፡ ተማከሩ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እሊህም ፡ ሲማከሩ ፡ ዝም ፡ የሚሉ ፡ ፳፱፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



ከሦስቱ ፡ ራሶች ፡ መካከለኛ ፡ የሚሆን ፡ አንዱ ፡
ተነሣ ፡ ከነሳቸው ፡ የሚበልጥ ፡ እሱ ፡ ነው ።
፴፩ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እሊህን ፡ ሁለቱን ፡ ራሶች ፡ ከሱ ፡
ጋራ ፡ ወሰዳቸው ።
፴፪ ያም ፡ ራስ ፡ አብረውት ፡ ከሉ ፡ ጋራ ፡ ተመለሰ ፡
ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ የተማከሩ ፡ እሊህን ፡ ሁለቱን ፡
ራሶች ፡ ዋጣቸው ፡ ድል ፡ ነሣቸው ።
፴፫ ያም ፡ ራስ ፡ (አፌፋኖስ ፡ አንጥያኮስ ፡ ) አጽንቶ ፡
ገዛ ፡ በሷም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎችን ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡
መከራ ፡ አጸናባቸው ፡ ከቆሙት ፡ ከሊህ ፡ ክን
ፎች ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ፈጽሞ ፡ ዓለምን ፡ ቀማ ።
፴፬ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መካከለኛው ፡ ራስ ፡ እንደ ፡ እለ
ዚያ ፡ ጠፋ ፡ (አፌፋኖስ ። )
፴፭ ሁለቱ ፡ ራሶች ፡ ቀሩ ፡ (አጀም ፡ ሮም ፡ ) እነሱም ፡
እንደነሱ ፡ ምድርን ፡ ገዟት ፡ በውስጧ ፡ ያሉት
ንም ፡ ገዟቸው ።
፴፮ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ በቀኝ ፡ እኩል ፡ ያለው ፡
ራስ ፡ (በጥሊሞስ ፡ ) በግራ ፡ እኩል ፡ ያለውን ፡
ዋጠው ፡ (አንጥያኮስ ፡ )
፴፯ በፊትህ ፡ ተመልከት ፡ የምታየውንም ፡ እወቅ ፡
ያለኝን ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ።
፴፰ ባየሁም ፡ ጊዜ ፡ እየጮኸ ፡ እነሆ ፡ ከምድረ ፡
በዳ ፡ አንበሳ ፡ ተነሣ ፡ እንደ ፡ ሰውም ፡ ሲናገር ፡
ሰማሁት ፡ ያንም ፡ አሞራ ።
፴፱ የምነግርህን ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያለህን ፡ አንተ ፡
ስማ ።
፵ ምድርን ፡ ይገዟት ፡ ዘንድ ፡ ከፈጠርኳቸው የዘ
መንም ፡ ፍጻሜ ፡ ከሚደርስባቸው ፡ ከሊህ ፡
ከራት ፡ እንስሳ ፡ (ነገሥታት ፡ ) የቀረህ ፡ አንተ ፡
አይደለህምን ፡ ያለህን ፡ ስማ ።
፵፩ አራተኛውም ፡ መጥቶ ፡ ያለፉትን ፡ በብዙ ፡
ድካም ፡ በብዙ ፡ ሕማም ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ የቀሙ
ትን ፡ እለዚያን ፡ እንስሳ ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ ያደርጋ
ቸዋል ፡ ያለህ ፡ አንተ ፡ ስማ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡
ዘመን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በተንኮል ፡ ኖሮ ።
፵፪ ይችን ፡ ዓለም ፡ በጽኑ ፡ አገዛዝ ፡ ገዛት ፡ ያለህ ፡
አንተ ፡ ስማ ።
፵፫ ጻድቃንን ፡ ቀምተሃቸዋልና ፡ ደጋጎቹ ፡ ሰዎች
ንም ፡ በድለሃቸዋልና ፡ ቅኖቹንም ፡ ጠልተህ ፡
አሰተኞቹን ፡ ወደሃቸዋልና ፡ የጻድቃንን ፡ አም
ባቸውን ፡ አፍርሰሃልና ፡ ያልበደሉትን ፡ ሰዎች ፡
ቅጽራቸውን ፡ አፍርሰሃልና ።
፵፬ ኃጢአትህም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ደርሳለ
ችና ፡ ትቢትህም ፡ ወደ ፡ ኃያል ፡ እግዚአብሔር ፡
ደርሷልና ።
፵፭ እግዚአብሔርም ፡ ወገኖቹ ፡ መቃብያንን ፡ በቸ
ርነቱ ፡ ተመልክቷቸኋልና ፡ መቃብያን ፡ መከራ ፡
የሚቀበሉበት ፡ ዘመን ፡ እነሆ ፡ ተፈጽሟልና ።
፵፮ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አንተ ፡ አፌፋኖስ ፡ አንጥያኮስ ፡
ትጠፋለህ ፡ ኃጢአተኞች ፡ ወገኖችህ ፡ የእግዚ
አብሔርን ፡ ሕግ ፡ የዘነጉ ፡ ጥቃቅን ፡ ነገሥታቶ
ችህም ፡ ክፉዎች ፡ የሆኑ ፡ ሠራዊቶችህም ፡ ይጠ
ፋሉ ።
፵፯ ምድርም ፡ ከመከራዋ ፡ ሁሉ ፡ እፎይ ፡ ብላ ፡
ከንተ ፡ ታርፍ ፡ ዘንድ ፡ የፈጣሪዋን ፡ ቸርነቱንና ፡
ፍርዱን ፡ ተስፋ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ በደለኞች ፡
ዘመዶችህም ፡ ይጠፋሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዚያ ፡ ፩
ላሞራ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በነገረው ።
የቀረው ፡ ይህ ፡ ራስ ፡ ጠፋ ፡ (አፌፋኖስ ፡ ጠፋ ፡ ) ፪
ወደሱ ፡ የመጡ ፡ እነዚያም ፡ ክንፎች ፡ (ነገሥ
ታት ) ተነሡ ፡ እሊህም ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ ተነሡ ፡
በጥፍራቸውም ፡ (ሠራዊት ፡ ) ይቃወኩሉ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነሱም ፡ ጠፉ ፡ ሥጋቸውም ፡ ፫
ሁሉ ፡ ተቃጠለ ፡ ምድርም ፡ ፈጽማ ፡ ደነገጠች ፡
እኔም ፡ ከብዙ ፡ ምርምር ፡ የተነሣ ፡ ደነገጥሁ ፡
በጽኑ ፡ ፍርሃትም ፡ ነቃሁ ።
ልቡናዬን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ስትመረ ፬
ምሪ ፡ አንቺ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ አደረግሽኝ ፡ አል
ኋት ።
ሰውነቴ ፡ ደከመች ፡ ልቡናዬም ፡ እጅግ ፡ ተጨነ ፭
ቀች ፡ በብዙ ፡ ፍራት ፡ ተይገኘ ፡ ምንምን ፡ ኃይል ፡
የለኝ ፡ በዚችም ፡ ሌሊት ፡ ደነገጥሁ ።
ስዘላለሙ ፡ ያጸናኝ ፡ ዘንድ ፡ አሁንም ፡ ወደ ፡ ፮
እግዚአብሔር ፡ እለምናለሁ ።
አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ በፊትህ ፡ ባለሟልነትን ፡ ካገ ፯
ኘሁ ፡ በንተ ፡ ዘንድ ፡ ራሴንም ፡ ካስደነቅሁ ፡
ልመናዬም ፡ በፊትህ ፡ ከደረሰች ።
ከመፍራት ፡ አድነህ ፡ አጽናኝ ፡ አልሁት ፡ ልቡ ፰
ናዬ ፡ ፈጽማ ፡ ደስ ፡ ይላት ፡ ዘንድ ፡ የሚያስፈራ ፡
የዚህን ፡ የሕልም ፡ ትርጓሜ ፡ ለኔ ፡ ለባሪያህ ፡
ንገረኝ ፡ አልሁ ።
በኋላ ፡ ዘመን ፡ የሚደረገውን ፡ ስለ ፡ ዓለሙ ፡ ፱
ወራት ፡ ኀልፈትም ፡ ያሳየኸኝ ፡ አንተ ፡ ደግ ፡
ሰው ፡ አድርገሃልና ፡ ና ፡ የሕልምህን ፡ ትርጓሜ ፡
ንገረኝ ፡ አልሁ ።
ያየኸው ፡ የዚህ ፡ የሕልምህ ፡ ትርጓሜ ፡ እን ፲
ዲህ ፡ ነው ፡ አለኝ ።
ከበሕር ፡ ሲወጣ ፡ ያየኸው ፡ ይህ ፡ አሞራ ፡ ለወ ፲፩
ንድምህ ፡ ለዳንኤል ፡ በሕልም ፡ የታየችው ፡
አራተኛዋ ፡ መንግሥት ፡ (እስክንድር ፡ ) ናት ።
ዛሬ ፡ ላንተ ፡ እኔ ፡ እንደተረጎምኩልህ ፡ ነገር ፡ ፲፪
ግን ፡ ለሱ ፡ አልተረጎምሁለትም ።
እነሆ ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፡ በዚህ ፡ ዓለምም ፡ ፲፫
ከሷ ፡ አስቀድሞ ፡ ከነበሩት ፡ መንግሥታት ፡
ይልቅ ፡ የምታስፈራ ፡ መንግሥት ፡ ትነሣለች ።
በሷም ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ነገሥታት ፡ ይነሣሉ ። ፲፬
ዳግመኛ ፡ የሚነግሡውም ፡ ካሥራ ፡ ሁለት ፡ ነገ ፲፭
ሥታት ፡ በዘመኑ ፡ ፈጽሞ ፡ የሚጸና ፡ ነው ።
ያየሃቸው ፡ የሊህ ፡ ያሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ክንፎች ፡ ፲፮
ትርጓሜ ፡ ይህ ፡ ነው ።
ቃልን ፡ ሲናገር ፡ ያየው ፡ ይህም ፡ ከዘመዱ ፡ የተ ፲፯
ወለደ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመንግሥት ፡ ሁለተኛው ፡
የሚሆን ፡ ከሱ ፡ የተወለደ ፡ አይደለም ።
ትርጓሜው ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ከዚያም ፡ መንግ ፲፰
ሥት ፡ አፌፋኖስ ፡ አንጥያኮስ ፡ ይወለዳል ፡ መን

ግሥት ፡ እጠፉ ፡ እጠፉ ፡ ትላለች ፡ በግዛቷ ፡
እጅግ ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ፡ እንጂ ፡ ነገር ፡ ግን ፡
ያን ፡ ጊዜ ፡ አትጠፋም ።
፲፱ ከክንፎቹ ፡ ራሶች ፡ ሲወጡ ፡ ያየሁም ፡ ይህ ።
፳ ትርጓሜው ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ዘመናቸው ፡
የከፋ ፡ ወራታቸው ፡ ያጠረ ፡ ፰ ፡ ነገሥታት ፡
በሷ ፡ ይነግሣሉ ፡ ሁለቱ ፡ ግን ፡ ከነሳቸው ፡ በዘ
መናቸው ፡ መከከል ፡ ፈጥነው ፡ ይጠፋሉ ።
፳፩ ነገር ፡ ግን ፡ ዓራቱ ፡ መንግሥታት ፡ የሚጠፋ
በት ፡ ጊዜ ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ይጠበቃል ፡
ሁለቱ ፡ ነገሥታትም ፡ (አጀም ፡ ሮም ፡) ለብዙ ፡
ዘመን ፡ ይጠበቃሉ ።
፳፪ ገዛም ፡ ብለው ፡ ያየሁቸው ፡ እነዚህም ፡ ሦስቱ ፡
ራሶች ።
፳፫ ትርጓሜው ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡
በኋላ ፡ ዘመን ፡ ሦስቱን ፡ ነገሥታት ፡ ያስነሣል ፡
በውስጧም ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ይሠራሉ ፡ ምድር
ንም ፡ መከራ ፡ ነገር ፡ ያጸኑባታል ።
፳፬ ከሳቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ከነበሩት ፡ ከነገሥታቱ ፡
ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ በውስጧ ፡ የሚኖሩትንም ፡
ሰዎች ፡ በብዙ ፡ ፍሩት ፡ መከራ ፡ ያጸኑባቸዋል ።
፳፭ የመንግሥት ፡ መገኛ ፡ ናቸውና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡
ከነገሥታት ፡ በላይ ፡ ተባሉ ።
፳፮ በመኝታው ፡ የሚሞት ፡ ከሰሳቸው ፡ አንዱ ፡
እሱ ፡ ብቻ ፡ ነውና ፡ ታላቅ ፡ ራሱ ፡ ሲጠፋ ፡ ያየ
ሁው ፡ ይህ ፡ አንዱ ፡ አንጥያኮስ ፡ ነው ፡ ነገር ፡
ግን ፡ ተጨንቆ ፡ ይሞታል ።
፳፯ የቀሩት ፡ እሊህ ፡ ሁለቱ ፡ ግን ፡ በጦር ፡ ይሞታሉ ።
፳፰ አንዱ ፡ በጥሊሞስ ፡ ኋላ ፡ በጦር ፡ ይሞታል ።
፳፱ በየማናዊ ፡ ሥልጣን ፡ ወደጸና ፡ ወደ ፡ በጥሊ
ሞስ ፡ ሲሔዱ ፡ ያየሁቸው ፡ እሊህ ፡ ሁለቱ ፡
(አጀም ፡ ሮም ፡) ናቸው ።
፴ ትርጓሜው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኋላ ፡
ዘመን ፡ የጠበቃቸው ፡ የጥፋት ፡ መጀመሪያ ፡
የሚደረግባቸው ፡ አጀም ፡ ሮም ፡ ናቸው ፡ አንተ ፡
እንዳየሁውም ፡ ብዙ ፡ ጸብ ፡ ክርክር ፡ ይደረጋል ።
፴፩ ከምድረ ፡ በዳ ፡ እያናፋ ፡ ሲመጣ ፡ ያየሁው ፡ ይህ ፡
አንበሳ ፡ ያን ፡ አሞራ ፡ የተናገረው ፡ በኃጢአ
ቱም ፡ የሰደበው ፡ የሰማህ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ።
፴፪ እግዚአብሔር ፡ ለኋላ ፡ ዘመን ፡ የጠበቀው ፡ ከዳ
ዊትም ፡ ወገን ፡ የሚወለድ ፡ ይህ ፡ አንበሳ ፡
(ከደቂቀ ፡ ከስሙናይን ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡
ነው ፡) መጥቶም ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ይነግራቸ
ዋል ፡ ስለበደላቸውም ፡ ይሰድባቸዋል ፡ በፊታ
ቸውም ፡ ፍዳቸውን ፡ ይገልጥባቸዋል ።
፴፫ በደኅንነቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ያቆማቸዋል ፡ ከሰ
ደባቸውም ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ያጠፋቸዋል ።
፴፬ ከክህደት ፡ የቀሩ ፡ መቃብያንን ፡ ግን ፡ በቸርነቱ ፡
በከበረ ፡ አውራጃየ ፡ (ኢየሩሳሌም ፡) ያድናቸ
ዋል ፡ አስቀድሜ ፡ የነገርኩህ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአ
ትም ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ደስ ፡ ያሰኛቸዋል ።
፴፭ ያየሁው ፡ ይህ ፡ ሕልምህ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡
ትርጓሜውም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ።

ይህን ፡ ምሥጢር ፡ ታውቀው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአ ፴፮
ብሔር ፡ ላንተ ፡ ብቻ ፡ እንድታውቀው ፡ አደረ
ገህ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ያየሁውን ፡ ሁሉ ፡ በብራና ፡ ፴፯
ጻፈው ፡ በተሠወረ ፡ በታም ፡ አኑረው ።
ይህን ፡ ምሥጢር ፡ በልቡናቸው ፡ ሰመጠበቅ ፡ ፴፰
እንዲቻላቸው ፡ አንተ ፡ ለምታውቃቸው ፡ ላቀ
ቆች ፡ ሰዎች ፡ አስተምራቸው ።
አንተ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊገልጽልህ ፡ የወ ፴፱
ደደውን ፡ ታይ ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡
በዚህ ፡ ተቀመጥ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተለይቶ ፡ ሄደ ፡ እሊህ ፡ ሰባት ፡ ፵
ቀኖች ፡ እንዳለፉ ፡ እኔም ፡ ወዳገር ፡ እንዳልገ
ባሁ ፡ ሰዎቹ ፡ ሁሉ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ትንሹም ፡
ትልቁም ፡ ወገኖቼ ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ወደኔ ፡
መጡ ።
አንተን ፡ ምን ፡ በደልንህ ፡ እኛን ፡ ትተኸን ፡ ፵፩
በዚህ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፡ ምንስ ፡
አሳዘንህ ።
ከሚለቀሙት ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ፍሬ ፡ እን ፵፪
ዲቀር ፡ በጨለማ ፡ በታ ፡ ውስጥም ፡ ፋና ፡ እን
ዲያበራ ፡ በጥልቅ ፡ ባሕርም ፡ ውስጥ ፡ ወደብ ፡
መርከቡን ፡ ጸጥ ፡ እንዲያደርግ ፡ ከነቢያት ፡ ሁሉ ፡
አንድ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ቀርተኸናልና ፡ አንተን ፡
ምን ፡ በደልንህ ፡ አሉኝ ።
ወይስ ፡ ያገኘችን ፡ መከራ ፡ አልበቃችንምን ። ፵፫
በዚያ ፡ የሞቱትን ፡ ሰዎች ፡ እኛ ፡ የምናሻላቸው ፡ ፵፬
አይደለንምና ፡ አንተስ ፡ የምትለየን ፡ ከሆን ፡
ጽዮን ፡ በተቃጠለች ፡ ጊዜ ፡ በተሻለን ፡ ነበር ፡
አሉት ።
ይኸንን ፡ ተናግረው ፡ ቃላቸውን ፡ አሰምተው ፡ ፵፭
አለቀሱ ።
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ስም ፡ አጠራራችን ፡ ፵፮
አለና ፡ የማይዘነጋን ፡ እሱም ፡ ጽኑ ፡ ነውና ፡
የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ እመኑ ።
የእስራኤልም ፡ ወገኖች ፡ አትዘኑ ፡ ብዬ ፡ መለ ፵፯
ስሁላቸው ።
እኔስ ፡ አልተዋችሁም ፡ ከናንተም ፡ አልርቅም ፡ ፵፰
ነገር ፡ ግን ፡ ወደዚህ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ የመጣሁ ፡
ስለ ፡ ጽዮን ፡ ጥፋት ፡ እለምን ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡
ተድላ ፡ ደስታችንን ፡ ተከትሎ ፡ ስለ ፡ መጣብ
ንም ፡ መከራ ፡ ይቅርታን ፡ እለምን ፡ ዘንድ ፡
ነው ፡ አለ ።
አሁንም ፡ ሁላችሁም ፡ ወደ ፡ ቤታችሁ ፡ ግቡ ፡ ፵፱
እኔም ፡ ወደናንተ ፡ እመጣለሁ ።
ከነዚህም ፡ ወራቶች ፡ በኋላ ፡ በገራችሁ ፡ ወዳለ ፡ ፶
በታችሁ ፡ ግቡ ፡ እንዳልኋቸው ፡ ሕዝቡም ፡ ወደ ፡
ቤታቸው ፡ ገቡ ።
እኔ ፡ ግን ፡ እንዳዘዘኝ ፡ በዚያ ፡ በታ ፡ በምድረ ፡ ፶፩
በዳው ፡ ውስጥ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ተቀመጥሁ ፡ ከም
ድረ ፡ በዳ ፡ ፍሬ ፡ ብቻ ፡ ተመገብሁ ፡ በነዚያም ፡
በሰባቱ ፡ ቀኖች ፡ ከምድረ ፡ በዳው ፡ ቅጠል ፡
በላሁ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

፩፤ ከዚህም ፡ ከሰባተኛው ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በሌሊት ፡
ሕልምን ፡ አየሁ ።
፪፤ እነሆ ፡ ጽኑ ፡ ነፋስ ፡ ከባሕር ፡ ሲወጣ ፡ አየሁ ፡ የባ
ሕርም ፡ ማዕበል ፡ ሞገዱ ፡ ሁሉ ፡ ታወከ ።
፫፤ ያ ፡ ነፋስ ፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ ከባሕር ፡ ሲወጣ ፡
አያለሁ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰማይ ፡ ደመናዎች ፡
ጋራ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወጣ ፡ ፊቱን ፡
መልሶ ፡ በየ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡
ወደሱ ፡ ይመጣል ።
፬፤ ቃሉ ፡ እየወጣ ፡ ሁሉ ፡ ከቃሉ ፡ የተነሣ ፡ ይቀል
ጣል ፡ ሰም ፡ እደሮ ፡ ማር ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ በቀረበ ፡
ጊዜ ፡ እንዲቀልጥ ፡ ቃሉን ፡ የሰሙ ፡ ሰዎች ፡
ሁሉ ፡ ይቀልጣሉ ።
፭፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡ ብዙ ፡
ሰዎችን ፡ ከባሕር ፡ የወጣ ፡ ይኸን ፡ ሰው ፡ ይጣ
ሉት ፡ ዘንድ ፡ ከራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ሲሰበሰቡ ፡
አየሁ ።
፮፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ታላቅ ፡ ተራራ ፡ ሠራ ፡ በላዩም ፡
ላይ ፡ ተቀመጠ ፡ ( መስቀል ። )
፯፤ ከመስቀል ፡ ያደረሰውን ፡ መርምሬ ፡ ላውቅ ፡
ወደድሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ማወቅ ፡ ተሳነኝ ።
፰፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሊይዙት ፡ የተሰበሰቡ ፡ ( አይ
ሁድ ፡ ) ሁሉ ፡ ፈጽመው ፡ ፈሩ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይይ
ዙት ፡ ዘንድ ፡ ደፋፈሩ ።
፱፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በከበቡት ፡ ጊዜ ፡ ወደሱም ፡
በመጡ ፡ ጊዜ ፡ በነሱ ፡ ሥልጣኑን ፡ አላጸናባቸ
ውም ፡ ጦሩንም ፡ አላነሣባቸውም ፡ የበዳ ፡ ፀብ
ቱንም ፡ ምንምን ፡ አላነሣባቸውም ።
፲፤ ከአፉ ፡ የእሳት ፡ ማዕበልን ፡ ከከንፈሩ ፡ የእሳት ፡
ነበልባልን ፡ ከንደበቱም ፡ የእሳት ፡ ፍምን ፡
እንደ ፡ ጥልቅ ፡ ነፋስ ፡ አወጣ ፡ እንጂ ፡ ሥልጣ
ኑን ፡ አልገለጸባቸውም ፡ ያ ፡ የእሳት ፡ ማዕበል ፡
ያ ፡ የእሳት ፡ ነበልባል ፡ ያ ፡ የእሳት ፡ ፍሙም ፡
ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሆነ ፡ በከበቡት ፡ ሊገድሉትም ፡
ዘንድ ፡ በመጡ ፡ በነዚያ ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡
ጥቅል ፡ ነፋስ ፡ ሆኖ ፡ ወረደባቸው ።
፲፩፤ ከአቃጠሏቸው ፡ ጢስ ፡ ካመዳቸው ፡ ትቢያ ፡
በቀር ፡ ከለሳቸው ፡ የሚድን ፡ እስኪታጣ ፡ ድረስ ፡
ሁሉንም ፡ አቃጠላቸው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተነ
ሣሁ ።
፲፪፤ ከተነሣሁም ፡ በኋላ ፡ ያንን ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ሲወ
ርድ ፡ አየሁት ፡ ( ክርስቶስን ፡ ) ስምሞች ፡ የሚ
ሆኑ ፡ ብዙ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎችን ፡ ወደሱ ፡ ጠራ ።
፲፫፤ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ወደሱ ፡ መጡ ፡ ( ሐዋርያት ፡ )
ከነሳቸውም ፡ ደስ ፡ ያላቸው ፡ አሉ ፡ ከለሳቸው ፡
ያዘኑም ፡ አሉ ፡ ከለሳቸው ፡ የታሰሩ ፡ አሉ ፡ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ደንግጬ ፡
ተነሣሁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለመንኩ ።
፲፬፤ ቀድሞ ፡ አንተ ፡ ይህን ፡ ጌትነትህን ፡ ለኔ ፡ ለባር
ያህ ፡ አሳየኸኝ ፡ ልመናዬን ፡ እንድትሰማልኝ ፡
አደረግህልኝ ።
፲፭፤ አሁንም ፡ የዚህ ፡ የሕልሜን ፡ ትርጓሜ ፡ ዳግ
መኛ ፡ ንገረኝ ።
ነገር ፡ ግን ፡ እኔስ ፡ እንደምጠራጠረው ፡ በነዚያ ፡ ፲፮፤
ወራቶች ፡ ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ወዮላቸው ፡ ይልቁ
ንም ፡ ላልነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ወዮላቸው ።
በኋላ ፡ ዘመን ፡ የሚቆዩቸውን ፡ ገና ፡ ያልደረሰ ፲፯፤
ላቸውን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ባለማወቅ ፡
ክደው ፡ ያዝናሉ ፡ ወዮላቸው ።
በሐሳዊ ፡ መሢሕ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ መከራ ፲፰፤
ውን ፡ ፈጽመው ፡ አውቀውታልና ፡ በዘመኑ ፡
ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁላቸው ።
በዚህ ፡ ሕልም ፡ እንዳየህ ፡ ጽኑ ፡ ጭንቅ ፡ ብዙ ፡ ፲፱፤
ድካምን ፡ ያያሉና ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ወዮላቸው ፡
ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ መከራው ፡ ሳይደርስ ፡ መሞት ፡ ፳፤
ይሻላል ፡ ደመና ፡ ታይቶ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እን
ዲጠፉ ፡ ቢሞቱ ፡ ይሻላቸዋል ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡
የምታገኛቸውን ፡ መከራ ፡ አያውቁም ።
መለሰልኝ ፡ እንዲህን ፡ የሕልምህን ፡ ትርጓሜ ፡ ፳፩፤
እነግርሃለሁ ፡ ይህን ፡ የምትጠይቀኝንም ፡ ነገር ፡
እተረጕምልሃለሁ ።
ስለሚቀሩት ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ስለሚኖ ፳፪፤
ሩበትም ፡ ሰዎች ፡ ተናግረሃልና ፡ ትርጓሜው ፡
እንዲህ ፡ ነው ።
በነዚያ ፡ ወራቶች ፡ ያን ፡ መከራ ፡ የሚቀበሉትን ፡ ፳፫፤
ሰዎች ፡ ያም ፡ መከራ ፡ የሚያገኛቸውን ፡ ሰዎች ፡
በእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ሃይማኖትና ፡ በጎ ፡
ምግባር ፡ ጽናትም ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ይጠብቃቸዋል ።
ነገር ፡ ግን ፡ አስቀድመው ፡ ከሞቱ ፡ ሰዎች ፡ በሐ ፳፬፤
ሳዊ ፡ መሢሕ ፡ ሕያዋን ፡ ሁነው ፡ የተገኙ ፡ ሰዎች ፡
ፈጽመው ፡ ክቡራን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ዕወቅ ።
የዚህስ ፡ የሕልምህ ፡ ትርጓሜ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ፳፭፤
ከባሕር ፡ ሲወጣ ፡ ያየኸው ፡ ይህ ፡ ሰው ።
ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ በሱ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ለኋላ ፡ ፳፮፤
ዘመን ፡ አብ ፡ ያዘጋጀው ፡ ይህ ፡ ወልድ ፡ ነው ፡
ከመከራም ፡ የተረፉትን ፡ ሰዎች ፡ እሱ ፡ በተ
ድላ ፡ በደስታ ፡ ያኖራቸዋል ።
እንደ ፡ ጥልቅ ፡ ነፋስ ፡ ሆኖ ፡ ካፉ ፡ እሳት ፡ ነበል ፳፯፤
ባል ፡ የሳት ፡ ፍሕም ፡ ሲወጣ ፡ ያየኸው ።
ጦሩን ፡ ሳያነሣ ፡ የበዳ ፡ ፀብቱን ፡ ሳያነሣ ፡ የከበ ፳፰፤
ቡትን ፡ እሊህን ፡ ብዙዎችን ፡ ያጠፋቸው ፡ ሊገ
ድሉት ፡ የመጡትንም ፡ ሲያጠፋቸው ፡ ያየኸው ፡
ይህ ፡ ትርጓሜው ፡ እንዲህ ፡ ነው ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ ፳፱፤
የሚያድንበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ እስበሳቸው ፡ ይወነጀላሉ ። ፴፤
በከተማ ፡ ያሉቱ ፡ ሰዎች ፡ በከተማ ፡ ካሉት ፡ ፴፩፤
ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ይዋጋሉ ፡ በገጠርም ፡ ያሉቱ ፡
ሰዎች ፡ በገጠር ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ይዋጋሉ ፡
ሠራዊት ፡ ከሠራዊት ፡ ነገሥታት ፡ ከነገሥታቱ ፡
ጋራ ፡ ይዋጋሉ ።
ይህም ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ቀድሞ ፡ ያሳየሁህ ፡ ፴፪፤
ምልክቱም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከባሕር ፡
ሲወጣ ፡ ያየኸው ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ይገለጣል ።
ቃሉንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ አገ ፴፫፤

ሮቻቸውን ፡ አርስበርሳቸውም ፡ የሚጣሉበትን ፡
ጠባቸውንም ፡ ይተዋሉ ።
፴፬ ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ አንድነት ፡ ተሰብ
ስበው ፡ ይበዛሉ ፡ መጥተው ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ፡
አንዱ ፡ ወደዱ ፡ ያየኸው ።
፴፭ ፡ እሱ ፡ ግን ፡ በመስቀል ፡ ይሰቀላል ።
፴፮ ፡ መስቀል ፡ ይዘጋጃል ፡ ለሁሉም ፡ ፈጽሞ ፡ ተዘ
ጋጅቶ ፡ ይታያል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡
ወደ ፡ ተደረገ ፡ በሰው ፡ ፈቃድ ፡ ወዳልተደረገ ፡
ወደ ፡ መስቀል ፡ ሲወጣ ፡ ያየኸው ።
፴፯ ፡ ኃጢአት ፡ ለመሥራት ፡ እንደ ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡
ፈጣን ፡ የሆኑ ፡ አሕዛብን ፡ በኃጢአታቸው ፡
የሚሰድባቸው ፡ ተቀዳሚ ፡ ተከታይ ፡ የሌለው ፡
ይህ ፡ ወልድ ፡ ነው ፡ የኃጢአታቸውንም ፡ ፍዳ ፡
በፊታቸው ፡ ይገልጥባቸዋል ፡ ኃጢአትም ፡
ለመሥራት ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ነበልባል ፡ የሆኑ
ትም ፡ ሰዎች ፡ ጽኑ ፡ ፍዳ ፡ ያመጣባቸዋል ።
፴፰ ፡ ኃጢአት ፡ ለመሥራት ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ፍም ፡
የሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ ድክም ፡ ሳይኖርበት ፡ ከኃጢ
አታቸው ፡ ጋራ ፡ ያጠፋቸዋል ።
፴፱ ፡ ስምምቹ ፡ የሆኑ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ያየሃቸውም ፡
እነዚህ ።
፵ ፡ እኒህ ፡ በፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ በስልምናሶር ፡ ዘመን ፡
ከገራቸው ፡ የተማረኩ ፡ ስልምናሶር ፡ በነገሠ ፡
ጊዜ ፡ የማረካቸው ፡ በፈሳሹ ፡ ውሃ ፡ ማዶ ፡ ያኖ
ራቸው ፡ ዘጠኙ ፡ ነገድ ፡ ተኩል ፡ ናቸው ፡ ወደ ፡
ዕውቀት ፡ ተመለሱ ፡ ለዕውቀትም ፡ ሌላ ፡ ሆኑ ።
፵፩ ፡ የወገናቸውን ፡ ነገድ ፡ ይተዉ ፡ ዘንድ ፡ የሰው ፡
ወገን ፡ ወደማይኖርበት ፡ ሀገርም ፡ ይሄዱ ፡
ዘንድ ።
፵፪ ፡ በሀገራቸው ፡ ሳሉ ፡ ያልጠበቁት ፡ ሕጉን ፡ ይጠ
ብቁ ፡ ዘንድ ፡ እነሣቸው ፡ ይህችን ፡ ምክር ፡ ከል
ቡናቸው ፡ አወጡት ።
፵፫ ፡ መግቢያቸው ፡ ጠባብ ፡ ወደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ኤፍ
ራጥስም ፡ ገቡ ።
፵፬ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምልክት ፡ አደረገላ
ቸው ፡ የፈሳሹም ፡ ምንጭ ፡ እስኪያልፉ ፡ ድረስ ፡
አቆመላቸው ።
፵፭ ፡ አገሩ ፡ ግን ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ያስሄዳል ፡ የሀ
ገሩም ፡ ስም ፡ አዛፍ ፡ ይባላል ።
፵፮ ፡ እስከ ፡ ኋላ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ኖሩ ፡ ከዚ
ህም ፡ ዳግመኛ ፡ ወደየሀገራቸው ፡ ይመለሱ ፡
ዘንድ ፡ ባላ ።
፵፯ ፡ ይሻገሩ ፡ ዘንድ ፡ የፈሳሹም ፡ ምንጭ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ዳግመኛ ፡ ያቆምላቸዋል ።
፵፰ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሥላሴ ፡ ብዙዎችን ፡ ወሰዷቸው ፡
የአየኸው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እነሱም ፡ በከበረ ፡ መን
ግሥት ፡ ሰማያት ፡ ይገኛሉ ።
፵፱ ፡ በሱ ፡ የተሰበሰቡ ፡ እነዚያን ፡ ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡
ባጠፋቸው ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የቀሩትን ፡ ወገ
ኖች ፡ ያጸናቸዋል ።
፶ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ምልክቱን ፡ ያሳያቸዋል ።
፶፩ ፡ እኔም ፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ ይህንን ፡ ንገረኝ ፡ ከባ
ሕር ፡ መካከል ፡ ሰው ፡ ሲወጣ ፡ እኔ ፡ ያየሁት ፡
ስለ ፡ ምንድነው ፡ አልሁት ።
ማንም ፡ ማን ፡ በጥልቅ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፶፪
ውን ፡ ማወቅ ፡ እንዳይችል ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ካሉ ፡
ሰዎችም ፡ ክርስቶስን ፡ እንደዚሁ ፡ ማንም ፡
ማን ፡ ማወቅ ፡ የሚችል ፡ የለም ፡ ሰዓቱ ፡ ቀኑ ፡
በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሱም ፡ ጋራ ፡
ያሉት ፡ ሰዎችም ፡ ማወቅ ፡ አይችሉም ።
ያየኸው ፡ የሕልምህም ፡ ትርጓሜው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ፶፫
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ላንተ ፡ ብቻ ፡ አሳየሁህ ።
ግዳጅህን ፡ ትተህ ፡ የኔን ፡ ግዳጅ ፡ ተከትለሃልና ፡ ፶፬
ሕጌንም ፡ ፈልገሃልና ።
አንጥወርህን ፡ ለውጠሃል ፡ ተዘጋጅተሃልና ፡ ጥበ ፶፭
ብንም ፡ እናት ፡ አድርገሃልና ።
ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እንደዚህ ፡ ገለጥሁልህ ፡ ዋጋህ ፡ ፶፮
በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አለና ፡ እንግዲህስ ፡
ወዲህ ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ወደኔ ፡ ና ፡ የምነ
ግርህ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አለና ፡ ድንቅ ፡ ነገርም ፡ እተ
ረጉምልሃለሁ ፡ ወደኔ ፡ ና ።
እግዚአብሔርን ፡ ፈጽሚ ፡ እያመሰገንሁት ፡ በየ ፶፯
ቀኑ ፡ ስለሚያደርገው ፡ ስለ ፡ ታምራቱ ።
ዘመኖቹንም ፡ እንደሚሠራው ፡ አድርጌ ፡ በየዘ ፶፰
መኑም ፡ እንደሚሠራው ፡ አድርጌ ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ ፈጽሚ ፡ እያመሰገንሁት ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡
በዳ ፡ ሄድኩ ፡ በዚያም ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ አደርሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ከእንጨት ፡ ሥር ፡ ተቀ ፩
ምጬ ፡ ሳለሁ ።
ከዚያች ፡ እንጨት ፡ አፋዛዣ ፡ ቃል ፡ መጣ ፡ ፪
ዕዝራ ፡ ዕዝራ ፡ ብሎ ፡ ጠራኝ ፡ እነሆ ፡ እኔ ፡
አለሁ ፡ አልሁት ፡ ተነሥቼም ፡ ቆምሁ ።
ሙሴን ፡ ፈጽሚ ፡ ታየሁት ፡ ወገኖቼ ፡ እስራ ፫
ኤል ፡ ለግብፅ ፡ ሰዎች ፡ በተገዙ ፡ ጊዜ ፡ ጰጠስ ፡
በሚባል ፡ እንጨት ፡ ሥር ፡ ተናገርሁት ።
ወደ ፡ ግብፅ ፡ ላክሁት ፡ ወገኖቼንም ፡ ከግብፅ ፡ ፬
አወጣኋቸው ፡ ሙሴንም ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡
ወሰድሁት ፡ ብዙ ፡ ዘመንም ፡ በኔ ፡ ዘንድ ፡ አኖ
ርሁት ።
ብዙ ፡ ድንቅ ፡ ነገርን ፡ ነገርሁት ፡ የዘመኑንም ፡ ፭
ምሥጢር ፡ አሳየሁት ፡ የኋላውንም ፡ ዘመን ፡
ፈጽሚ ፡ ነገርሁት ።
ይህን ፡ ነገር ፡ ተናገር ፡ ይህን ፡ ሠውር ፡ ብዬ ፡ ፮
አዘዝሁት ።
አሁንም ፡ ላንተ ፡ የነገርሁህን ፡ ያን ፡ ነገር ፡ ፯
ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ እነግርሃለሁ ።
ያየኸው ፡ ሕልምህን ፡ የሰማኸውን ፡ ትርጓሚ ፰
ውንም ፡ በልቡናህ ፡ ጠብቀው ።
መላእክት ፡ ከሰው ፡ ለይተው ፡ ይወስዱሃልና ፡ ፱
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዓለም ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡
እንዳንተ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ በሉበት ፡ በታ ፡ ከል
ጆች ፡ ጋራ ፡ ትኖራለህና ፡ የሰማኸውን ፡ በልቡ
ናህ ፡ አስተውለው ።
ይህ ፡ ዓለም ፡ የሕፃንነቱ ፡ ወራት ፡ አልፏልና ፡ ፲
ዘመኑም ፡ አርጅቷልና ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org



፲፩፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ የሚያልፍበት ፡ ዘመኑ ፡ ከዓሥር ፡
ተከፍሏልና ፡ እስከ ፡ ዓሥርም ፡ ድረስ ፡ ደርሿ
ልና ።
፲፪፡ የዓሥረኛው ፡ እኩሌታው ፡ ቀርቷልና ።
፲፫፡ አሁን ፡ ቤትህን ፡ አዘጋጅ ፡ ያዘኑትንም ፡ ደስ ፡
አሰኛቸው ፡ አዋቆቻቸውንም ፡ ልብ ፡ አስደርጋ
ቸው ፡ የምታልፍ ፡ ይችንም ፡ ዓለም ፡ ተዋት ።
፲፬፡ የኀዘንን ፡ አሳብ ፡ እንግዲህ ፡ ተው ፡ የፈራኸ ፡
የበሰበሽ ፡ ሰው ፡ አሳብን ፡ ተው ፡ የሚሞት ፡
ሰው ፡ አሳብን ፡ ተው ፡ አለመሞትን ፡ ገንዘብ ፡
አድርግ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡
ፈጥነህ ፡ ትሔድ ፡ ዘንድ ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡
ሥራ ።
፲፭፡ ይች ፡ ያየሃት ፡ መከራ ፡ ዛሬ ፡ ደርሳለችና ፡ እን
ግዲህ ፡ ወዲህም ፡ ዳግመኛ ፡ ከዚ ፡ የምትከፋ ፡
መከራ ፡ ትደረጋለች ።
፲፮፡ ዓለም ፡ እያረጀ ፡ እየደከመ ፡ ይሔዳልና ፡ እንደ
ዚህ ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎችም ፡
ክፋታቸው ፡ ትበዛለች ።
፲፯፡ ይህ ፡ ያየኸው ፡ ሐሰዊ ፡ መሢሕ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡
ስለ ፡ ቸኮለ ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ ትጠፋለችና ፡ አሰ
ትም ፡ ነገር ፡ ትጸናለች ።
፲፰፡ መለስሁለት ፡ እንዲህ ፡ አልሁት ፡ እንግዲህስ ፡
ወዲህ ፡ በፊትህ ፡ እናገራለሁ ።
፲፱፡ አቤቱ ፡ እኔ ፡ እንዳዘዝከኝ ፡ እሔዳለሁና ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ አስተምራ
ቸዋለሁ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ዳግመኛ ፡ የሚወ
ለዱትን ፡ ሰዎች ፡ ማን ፡ ያስተምራቸዋል ።
፳፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ በድንቁርና ፡ አለና ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ዕውቀት ፡ የላቸውም ።
፳፩፡ አሪትህ ፡ ጠፍታለችና ፡ የሠራሃውን ፡ ሥራ ፡
ትሠራው ፡ ዘንድ ፡ ያለህንም ፡ የሚያውቀው ፡
የለም ።
፳፪፡ በፊትህስ ፡ ባለሟልነትን ፡ ካገኘሁ ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስን ፡ ላክልኝና ፡ ከጥንቱ ፡ ጀምሮ ፡ በዚህ ፡
ዓለም ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ልጻፍ ፡ ሊድኑ ፡ የወ
ደዱ ፡ ሰዎች ፡ የደኅንነት ፡ መንገድ ፡ ማግኘት ፡
ሰው ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ በአሪትህ ፡ እንዳለ ፡ አድ
ርጌ ፡ እጽፍ ፡ ዘንድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ላክ
ልኝ ።
፳፫፡ መለሰልኝ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ሒደህ ፡ ወገኖች
ህን ፡ ሰብስባቸው ፡ እስከ ፡ አርባ ፡ ቀንም ፡ ድረስ ፡
እንዳይፈልጉህ ፡ አትፈልጉኝ ፡ በላቸው ።
፳፬፡ አንተ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ብራና ፡ ሰብስብ ፡ እነሳቸው ፡
ለጽፈት ፡ ብልሆች ፡ ናቸውና ፡ ሰርያ ፡ ደርብያን ፡
ሰላምያን ፡ ኢቀናን ፡ አሳኤል ፡ እሊህ ፡ አምስ
ቱን ፡ ሰዎች ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ አምጣቸው ።
፳፭፡ ወደዚህ ፡ ና ፡ በልቡናህ ፡ የጥበብ ፡ ዕውቀትን ፡
አሳድርብሃለሁ ፡ ትጽፍ ፡ ዘንድ ፡ ያለህን ፡ ሁሉ ፡
እስክትጨርስ ፡ ድረስ ፡ እንግዲህ ፡ ያቺ ፡ ዕው
ቀት ፡ አትለይህም ።
፳፮፡ በጨረስህም ፡ ጊዜ ፡ ገልጠህ ፡ የምታደርገው ፡
አለ ፡ የምትሠውርም ፡ ነገር ፡ አለ ፡ ለአዋቂዎ
ችም ፡ ታስተምራቸዋለህ ፡ ነገ ፡ በዚህ ፡ ሰዓት ፡
ትጽፍ ፡ ዘንድ ፡ ትጀምራለህ ፡ አለኝ ።
እንደ ፡ አዘዘኝ ፡ ሔጄ ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰ ፳፯፡
ብሁ ።
እስራኤል ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ስሙ ። ፳፰፡
አባቶቻችሁ ፡ ቀድሞ ፡ ግብፅ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ፳፱፡
ኖሩ ፡ ከግብፅም ፡ አወጣቸው ።
የደኅንነት ፡ ሕግን ፡ ተቀብለው ፡ አልጠበቁም ፡ ፴፡
ከነሳቸውም ፡ በኋላ ፡ ያላችሁት ፡ እናንተም ፡
እግዚአብሔርን ፡ ከዳችሁት ።
ምድረ ፡ ርስትን ፡ ሰጠን ፡ ጽዮን ፡ የምትባል ፡ ፴፩፡
ሀገርንም ፡ አወረሰን ፡ እላንተም ፡ አባቶቻች
ሁም ፡ ከዳችሁት ፡ እርሱንም ፡ መበደል ፡ አል
ተዋችሁም ፡ የአዘዛችሁ ፡ የእግዚአብሔር ፡
ሕጉን ፡ አልጠበቃችሁም ።
እውነተኛ ፡ ዳኛ ፡ ነውና ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ የሰ ፴፪፡
ጣችሁን ፡ ቀማችሁ ።
አሁንም ፡ እናንተ ፡ በዚህ ፡ በባቢሎን ፡ አላችሁ ፡ ፴፫፡
ወንድሞቻችሁ ፡ ግን ፡ ከናንተ ፡ ተለይተው ፡
በኢየሩሳሌም ፡ አሉ ።
ልቡናችሁን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያስገዛችሁት ፡ ፴፬፡
እንደዚሁ ፡ ልቡናችሁን ፡ የገሠፃችሁት ፡ እን
ደሆነ ፡ ሕጉንም ፡ የጠበቃችሁት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
አትሞቱም ።
ከሞት ፡ በኋላ ፡ ቍርጥ ፡ ፍርድ ፡ ያመጣልና ፡ እኛ ፴፭፡
ንም ፡ በሕይወት ፡ አያኖረንምና ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡
የጻድቃን ፡ ስማቸው ፡ ይገለጣል ፡ የኃጢአተ
ኞችም ፡ ሥራቸው ፡ ይገለጣል ።
እናንተ ፡ ወደኔ ፡ የሚመጣ ፡ አይኑር ፡ እስከ ፡ ፴፮፡
አርባ ፡ ቀንም ፡ ድረስ ፡ አትፈልጉኝ ።
እንዳዘዘኝ ፡ እሊህን ፡ አምስቱን ፡ ሰዎች ፡ ይዤ ፡ ፴፯፡
ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳው ፡ ሔደን ፡ በዚያም ፡ ተቀ
መጥን ።
በማግሥቱ ፡ ቃል ፡ ዕዝራ ፡ ዕዝራ ፡ ብሎ ፡ ፴፰፡
ጠርቶ ፡ አፍህን ፡ ክፈት ፡ እኔም ፡ የማጠጣህን ፡
ጠጣ ፡ አለኝ ።
አፌንም ፡ በከፈትሁ ፡ ጊዜ ፡ ውሀ ፡ የተመላ ፡ ፴፱፡
መልኩ ፡ እሳት ፡ የሚመስል ፡ መጠጥን ፡ አጠ
ጣኝ ።
እንሥቼ ፡ ጠጣሁት ፡ ልቡናየም ፡ ፈጽሞ ፡ ዕው ፵፡
ቀትን ፡ ተናገረ ፡ በልቡናየ ፡ ዕውቀት ፡ በዛ ፡ ልቡ
ናየም ፡ ትጠብቀዋለች ፡ ታስበዋለች ።
አፌ ፡ ተከፈተ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ ዕውቀት ፡ ፵፩፡
አልተወሰነብኝም ።
ለነዚያ ፡ ላምስቱ ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕው ፵፪፡
ቀትን ፡ ገለጸላቸው ፡ የማያውቁት ፡ ምልክት ፡
የሆነ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ቀጥለው ፡ ቀጥለው ፡ ጻፉ ፡
በዚያም ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ተቀመጡ ፡ እነሱስ ፡
ቀን ፡ ቀን ፡ ይጽፉሉ ።
ማታ ፡ ማታ ፡ ይመገቡሉ ፡ እንጀራ ፡ ይበላሉ ፡ እኔ ፡ ፵፫፡
ግን ፡ ቀን ፡ እጽፋለሁ ፡ ሌሊትም ፡ ዝም ፡ አል
ልም ።
በነዚያ ፡ በአርባው ፡ ቀኖች ፡ ሐያ ፡ አራት ፡ መጻ ፵፬፡
ሕፍት ፡ ተጻፉ ።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነዚያ ፡ አርባ ፡ ቀኖች ፡ በተፈ ፵፭፡

ጸሙ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናገረኝ ፡ አስ
ቀድሞ ፡ የጻፍኩትን ፡ ያንን ፡ ገልጠህ ፡ አድር
ገው ፡ ያነበው ፡ ዘንድ ፡ የሚገባው ፡ የማይገባ
ው፡ም ፡ ሁሉ ፡ ያንብበው ።
፴፮፤ የውቀት ፡ ምሥጢር ፡ የጥበብም ፡ ምሥጢር ፡
እንደ ፡ ፈሳሽ ፡ ውሀም ፡ ያለ ፡ ዕውቀት ፡ ላላ
ቸው ፡ አለቆች ፡ ስሆኑ ።
፴፯፤ ሰዎች ፡ ታስተምራቸው ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ተመ
ልከት ።
፴፰፤ እንዳዘዘኸኝም ፡ አደረግሁ ፡ በአራተኛውም ፡
ዘመን ፡ ከሚቈጠሩ ፡ ከብዙ ፡ ሱባዔ ፡ በምስተ
ኛው ፡ ሱባዔ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ በተፈጠረ ፡ ከምስት ፡
ሺህ ፡ ዘመን ፡ ኋላ ፡ ጨረቃ ፡ ሠርቅ ፡ በደረገች ፡
ጨለማዋን ፡ በአጣች ፡ በአሥረኛው ፡ ቀን ፡ በሦ
ስተኛው ፡ ወር ።
፴፱፤ በዘጠና ፡ አንደኛው ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ጽፎ ፡ ያን ፡
ጊዜ ፡ መላእክት ፡ ዕዝራን ፡ ይዘው ፡ እንደሱ ፡
ያሉ ፡ ደጋግ ፡ ሰዎች ፡ ወዳሉበት ፡ ወደ ፡ ብሔረ ፡
ሕያዋን ፡ወሰዱት ፡ እሱም ፡ ዕዝራ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡
ድረስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጥበብ ፡ የጻፈ ፡ ተባለ ።

* * *

አነቃቅቶ ፡ ላስጀመረን ፡ አስጀምሮ ፡ ላስፈጸ
መን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእውነት ፡ ለዘላለሙ ፡
ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ዕዝራ ፡ የተናገ
ረው ፡ ነገር ፡ መላ ፡ ተፈጸመ ።
እውነት ፡ ነው ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ይሁን ፡ ይሁን ፡
ይደረግልን ።